መለያችን ኢትዮጵያዊነታችን !

# ግዮን

ግዮን ቅጽ 1 ቁጥር 19 ነሐሴ 2010 ዓ.ም

በየሳምንቱ ቅዳሜ

ዋጋ 14.99




“ብአዴን በትግርኛ እያሰበ በአማርኛ የሚያስተዳድር የህወሓት ክንፍ ነበር”

ጋዜጠኛ ተመስገን ደሳለኝ

በተለይ ለግዮን ብቻ

ልዩ ቃለ ምልልስ



## “ህወሓት ከመንግሥት አካውንት 35 ሚሊዮን ዶላር በመውሰድ ኤፈርትን ደጉሟል”


# አምባሳደር ካሳ ከበደ

ግዮን

14

“ህወሐት ከመንግሥት አካውንት 35 ሚሊዮን ዶላር በመውሰድ ኤፈርትን ደጉሟል”

አምባሳደር ካሳ ከበደ (ልዩ ቃለ ምልልስ)



2 ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ በዚህ ሳምንት

4 የብርሃኑ ነጋና የአንዳርጋቸው ፅጌ ዘመን ተሻጋሪ ትሩፋት!

5 ብሔራዊ መረጃና ደህንነት ከፓርቲ መጨቆኛነት ወደ ህዝብ አገልጋይነት
መላኩ ብርሃኑ

12 የሐሳብ ልዩነት ለዘላለም ይኑር!
ተስፋ (ኢትዮጵያ) አልታሰብ

18 ከልሒቅ እስከ ደቂቅ ከግብታዊነት ቢርቅ
አስማማው ኃ/ጊዮርጊስ

20 ኢኮኖሚያችን እና የአግልግሎቱ ዘርፍ፤
ኃይሉ አሰለፍ ገብሬ

22 የመቀሌ ዩኒቨርስቲ ምሁራን ምን ነካቸው?
ዳርሰማ ሶሪ

23 “ቤቱ ጠባቻው ነው!!... ውጣላቸው፤ ሰፊ አድርገን እንሠራላቸዋለን”
ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ

24 ለሺዎች ባልንጀራ የሚሊዮኖች መሪ

25 ወዳጄ ኮፊ አናን
ከፍቅሩ ኪዳኔ

28 “ኪነ ጥበብ ያልታዩ የሕይወት ገጽታዎችን የምናይበት መነጽር ነው”
ደራሲ ሰአዳ መሐመድ

9



“ብአዴን በትግርኛ እያሰበ በአማርኛ የሚያስተዳድር የህወሐት ክንፍ ነበር’
ጋዜጠኛ ተመስገን ደሳለኝ

ግዮን

ቀጣይ ዕትም
ቅዳሜ ነሐሴ
26
ይጠብቁን!




ቁጥር 18 ዕትም

# ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ በዚህ ሳምንት

ያለፉት አራት ወራት የኢትዮጵያ ፖለቲካ እጅግ በጣም በርካታ ለውጦች የታዩበት ነው፡፡ በተለይ ጠቅላይ ሚኒስቴር ዐቢይ የኢህአዴግ ሊቀ መንበር እና የሀገሪቷ ጠቅላይ ሚኒስቴር ሆነው ወደሥልጣን ከመጡ በኋላ የሀገር ይፈርሳል ሟርት እና አለመረጋጋቱ ቀንሷል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትሩ የወሰዷቸውና እየወሰዷቸው ያሉት እርምጃዎች በምሁራን፣ በፖለቲከኞች እና በማህበረሰቡ ዘንድ ከፍተኛ ተቀባይነት ያገኙና እያገኙ ያለ ጉዳይ ነው፡፡ ይህ የለውጥ ጉዞ ግለቱን ጠብቆ አሁንም ድረስ እንደቀጠለ የተለያዩ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ ሆኖም ግን ለውጡን የሚያደናቅፉ አለመረጋጋቶች እና ቀውሶች በተለያዩ የሀገሪቷ ክፍሎች እየተከሰቱ ይገኛሉ፡፡

በተለይ የብሔር መልክ የያዙ ግጭቶች ገና በሙሉ እግሩ ያልቆመውን የለውጥ ኃይል ተረጋግቶ ሥራውን እንዳይሠራ ያደረጉት ይመስላሉ፡፡ ከጎረቤት ሀገራት ጋር እርቅ በመፍጠር፣ ከዲያስፖራው ማህበረሰብ ጋር በመወያየትና የፖለቲካ ቡድኖችን ወደ ሀገር ውስጥ ገብተው ሰላማዊ ትግል እንዲያደርጉ በማግባባቱ ረገድ የተዋጣለት ሥራ ሲሠሩ የከረሙት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ከሰሞኑ የገጠማቸው ፈተና ከባድ የቤት ሥራ የሰጣቸው ይመስላል፡፡

በዚህም በተደጋጋሚ በቴሌቪዥን መድረኮች እየቀረቡ በሚሠሯቸው ሥራዎች ላይ መግለጫዎችን ሲሰጡ፣ የውይይት መድረኩን ሲመሩ እንዲሁም ድርድሮችን ሲያደርጉ ቢቆዩም ባለፉት አንድ ሳምንታት ግን ከመገናኛ ብዙኃን ዕይታ ርቀው ቆይተዋል፡፡

የጠቅላይ ሚኒስትሩ ከመገናኛ ብዙኃን ዕይታ መራቅ እና በወቅታዊ ጉዳዮች ላይ መግለጫ አለመስጠት ብዙኃኑን አሳስቦ ቢቆይም፤ ይህ ሳምንት ደግሞ ከላይ ለተነሡት ጥያቄዎች መልስ የሚሰጥ ሆኖ አልፏል፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ የመንግሥታቸውን እና የድርጅታቸውን አቋም በሚገልፁ በርካታ ጉዳዮች ወደ መገናኛ ብዙኃን ቀርበው፣ በተደጋጋሚ መግለጫዎችን በመስጠት፣ የውይይት መድረኮችን በመምራትና ለዜጎች መልእክት በማስተላለፍ እቅዳቸውን ይፋ አድርገዋል፡፡ የእኛም በዛሬው እትማችን ጠቅላይ ሚኒስትሩ በዚህ ሳምንት ትኩረት አድርገው ያስተላለፏቸውን መልክቶች እና አጀንዳዎች እንደሚከተለው አጠናቅረነዋል፡፡

በወቅታዊ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ፣ "ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በሀገራችን ውስጥ በሁሉም መስኮች መሠረታዊና ተስፋ ሰጪ ለውጦች እየተመዘገቡ ያሉበት ታሪካዊ ምዕራፍ ላይ እንገኛለን" ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ሆኖም ለውጡን የሚያደናቅፉ፣ አቅጣጫ የሚያስቱ ችግሮችም አብረው እየታዩ መምጣታቸውን ገልፀዋል፡፡ "በኢትዮጵያ ዘላቂ ዋስትና ያለው ዴሞክራሲ እንዲሰፍን፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ዕድገት እንዲፋጠን፤ በሕግ የበላይነት እና በሕዝቡ ፈቃድ ላይ የተመሠረተ አንድ የፖለቲካ ማህበረሰብ በጋራ መገንባት፣ ይህንንም ለማሳካት የግለሰብና የቡድን መሠረታዊ መብቶች ካለአንዳች ልዩነት እንዲከበሩ ማድረግ እና ለዚህም የሚያስፈልገውን የፖለቲካ ምህዳር በሕገ መንግሥቱ መሠረት ማደራጀት ያስፈልጋል" በማለት የመንግሥታቸውን አቋም ግልፅ አድርገዋል፡፡ "አሁን በሀገራችን እየታየ ያለውና ለሕግ የበላይነት ትልቅ ፈተና የሆነው ጉዳይ፣ ለሕግ ተገዥነትን ወደ ጎን የማድረግ ትልቅ



ጠ/ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ

ዝንባሌ ብቻ ሳይሆን፤ በስሜትና በጥላቻ የሚወሰዱ እርምጃዎች፣ ሕግን ወደ ራስ ፍላጎት እና ስሜት በመውሰድ በመንጋ የሚሰጡ ሥርዓት አልባ ፍርዶች ጭምር ናቸው፡፡" ድርጊቶቹም በአንድ ክልል፣ ብሔር፣ ቋንቋ ወይም ሃይማኖት የተወሰኑ አለመሆናቸውን ጠቁመዋል፡፡ ስለሆነም በሀገራችን የዜጎቻችንን መብት እና ነፃነት ለማረጋገጥና የአካል፣ የሕይወትና የኑሮ ዋስትናቸውን ለማስጠበቅ ብቸኛው መሣርያ ሕግና ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓትን በሙሉ አቅም ማስከበር በመሆኑ፤ ማንም ሰው ሕግ ሲተላለፍ ተጠያቂ የሚደረግበትን የአሠራር ሥርዓት መዘርጋት እና መተግበር እንደዜጋ ለእያንዳንዳችን፤ እንደ ሀገርም ለሁላችን የምርጫ ሳይሆን የህልውና ጉዳይ ስለሆነ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ከመንግሥት ጎን በመሆን ርብርብ እንዲያደርግ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

ከምንም በላይ የግልና የቡድን ጥቅሞቻቸውን ሰላማዊ በሆነ መንገድ ማስጠበቅ እየቻሉ በተለያዩ ወንጀሎችና ሰላምን የማደፍረስ እኩይ ተግባራት ላይ ለመሠማራት የሚያስቡ አካላት፣ ከድርጊታቸው እንዲቆጠቡ አሳስበዋል፡፡ በማንኛውም የሕዝብን ፀጥታ በሚያደፈርሱና ሕዝብን ከሕዝብ በሚያጋጩ ሕገ ወጥ ተግባራት ላይ ተሠማርቶ የተገኘ፤ እንዲሁም ለእንደዚህ ዓይነት ሕገ ወጥ ተግባራት በምንም መልኩ ትብብር ያደረገ አካል ላይ ሕግን ተከትሎ፣ አስፈላጊውን እርምጃ ለመውሰድ መንግሥት ቁርጠኛ እንደሆነ በጥብቅ አሳስበዋል፡፡

## የባህር ዳር ቆይታቸው

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ በዚህ ሳምንት ባህር ዳር ተገኝተው ከክልሉ ከፍተኛና መካከለኛ አመራሮች ጋር ውይይት አድርገዋል፡፡ የአቶ ተስፋዬ ጌታቸው ቤት በመገኘትም ቤተሰቦቻቸውን አፅናንተዋል፡፡ ከክልሉ አመራሮች ጋር ባደረጉት ቆይታም የኅሊና ጸሎት በማድረግ አስጀምረዋል፡፡

ጠቅላይ ሚንስትሩ ሀገር አቀፍ የትምህርት ፖሊሲ ማሻሻያ ፍኖተ ካርታ ፎረምንም በንግግር ከፍተዋል፡፡ በዚህ ወቅት፣ የተፈለገውን ግብ ለማሳካት ሁሉን አቀፍና አካታች ማሻሻያ እንደሚያስፈልግ ተናግረዋል፡፡ ዘርፉን የተሻለና ውጤታማ ለማድረግ ማሻሻያው ወሳኝ ነገር መሆኑንና በቴክሎኖጂ የታገዘ አሠራር መከተል እንደሚገባም አንሥተዋል፡፡

አዲስ ይፋ በሆነው የትምህርት ሥልጠና ፍኖተ ካርታ ትምህርት ሚኒስቴር በሦስት ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች የሚደራጅ ሲሆን የ6ኛ ክፍል ክልላዊ ፈተና፣ የ8ኛ እና የ12ኛ ክፍል ሀገራዊ (ብሔራዊ) ፈተና እንዲሰጥ፤ የ10ኛ ክፍል ፈተና እንዲቀር፤ እንዲሁም የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ከ9ኛ ክፍል ጀምሮ እንዲሰጥ፤ የትምህርት ቋንቋ ወደ 4 ከፍ ብሎ አማርኛ እንግሊዝኛና የአፍ መፍቻ ቋንቋ እንዲሰጥ፤ የመምህራን ደመወዝና ጥቅማ ጥቅምን በተመለከተ በውይይቱ ተነሥቷል፡፡

## የኢድ አል አድሃ የመልካም በአል ምኞት መግለጫ

በእስልምና እምነት ተከታዮች ዘንድ በታላቅ ድምቀት የሚከበረውንና ዘንድሮም ለ1439ኛ ዓመተ-ሂጅራ ተከብሮ ለዋለው የኢድአል አድሃ አረፋ በአል ለመላው ኢትዮጵያውያን ሙስሊም ወገኖች እንኳን በሰላም አደረሳችሁ፤ አደረሰን! የሚል መልክት አስተላልፈዋል፡፡ "የዘንድሮውን የአረፋና ኢድ አልአድሃ በዓል ልዩ የሚያደርገው ሀገራችን በአዲስ የለውጥ እርምጃ መንገዝ በጀመረችበት ማግስት የሚከበር መሆኑ ብቻ ሳይሆን ለዓመታት ተከፋፍሎ የቆየው የሙስሊም ማኅበረሰብ አንድነቱን ለማጠናከር በጋራ መንቀሳቀስ በጀመረበት አዲስ የታሪክ ምዕራፍ ላይ ሆነን የምናከብረው መሆኑ፤ በዓሉን ድርብ ድርብርብ የደስታ በዓል ያደርገዋል" ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ "የእስልምና እምነት ተከታይ በሆነው ኅብረተሰባችን መካከል የሚፈጠር አንድነት ለሙስሊሙ ወገናችን ብቻ ሳይሆን ለሀገራችንም አንድነትና ጥንካሬ ምንጭ መሆኑን መንግሥት አበክሮ ይገነዘባል" ብለዋል፡፡

አረፋ በዓልም የመስጠት፣ የደግነትና የቸርነት በዓል በመሆኑ የተቸገሩና አንዳች ጥሪት የሌላቸው ወገኖቻችንን በመርዳት በመልካምና ደግ ሥራ በዓሉን ከተቀረው ወገኖቻቸው ጋር በጋራ እንዲያከብሩት ጥሪ አስተላልፈው ነበር፡፡ ምሁራን፣ የሀገር ሽማግሌዎችና የእምነት አባቶች የማኅበረሰባቸው የእውቀት ቀንድ መሆናቸውን ጠቅሰው፤ ሥርዓት አልበኝነት እንዳይሰለጥን ማኅበረሰቡን በሞራልና በሥነ ምግባር ተግተው እንዲያንፁ አደራ ብለዋል፡፡ "ለዚህ ታላቅ እና በመስጠት ጸጋ የተቃኘ ታላቅ በዓል ወቅት፤ ለእናንተ ለወገኖቼ የመልካም ምኞት መግለጫ ለማስተላለፍ በመቻሌ የተሰማኝን ከፍ ያለ ክብርና ልባዊ ደስታ ልገልጽላችሁ እወዳለሁ፡፡ በመጨረሻም በዓሉ አብሮነታችን የሚፈካ የሚያብብበት፣ ሰላምና ሀገራዊ አንድነታችን ሥር የሚሰድበት የበረከት በዓል እንዲሆንላችሁ ከልብ እመኛለሁ፡፡"

## ስለ አሸንዳ፣ ሻደይ፣ አሸንድዬ

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ በዚህ ሳምንት ስለተከበረው ስለዚህ በዓል በሰጡት መግለጫ፣ በሁሉም አቅጣጫ ያሉትን የሀገራችንን ሕዝቦች እንዳይበታተኑ ያስተሳሰሩ፤ እንዳይለያዩ ያጣመሩ፣ እንዳይፈርሱ ያማገሩ በርካታና ጠንካራ ማጎች በሀገራችን ሁሉም ጫፎች በክብር እና በፍቅር እዚህም እዚያም መኖራቸውን ጠቁመው፤ "ሕዝቦቻችን በጋብቻ ተዛምደው፣ በማንነት ተዋሕደው የኖሩ፣ ያሉና የሚኖሩ ናቸው" ብለዋል፡፡

"ከነፍስ የተሸመነ እውነት ማሳያ ከሆኑ የማህበረሰባችን እሴት ባህሎች ውስጥ በትግራይ እና በአማራ ክልሎች የሚኖሩ የትግራይ፣ የአማራ፣ የአገው፣ የኩናማ እና የኢሮብ ሕዝቦች መመሳሰልና መተሳሳርን የሚያሳየው የአሸንዳ/ሻደይ ክብረ በዓል አንዱና ምናልባትም ዋነኛው ነው" በማለት የበዓሉን ልዩ መልክ አሳይተዋል፡፡

ይህ ሳምንት፣ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ በበርካታ ጉዳዮች ላይ ለዜጎች መልክት ያስተላለፉበት፤ እንዲሁም በቀጣይ የሚሠሩ የመንግሥት አቅጣጫዎችን እና ሀገራዊ አጀንዳዎችን ያመላከተም ሆኖ አልፏል፡፡

# የያሬድ ጥበቡ "ወጥቼ አልወጣሁም" መጽሐፍ ዛሬ ይመረቃል!




አንጋፋው የፖለቲካ ሰው ያሬድ ጥበቡ ከዐሥራ ሁለት ዓመት በኋላ፤ ባለፈው ሳምንት ቅዳሜ ወደ ሀገር ቤት ተመልሰዋል:: የኢህዴንና የኢህአፓ አባል የነበሩት አቶ ያሬድ ጥበቡ፣ አዲስ አበባ ቦሌ አየር ማረፊያ ሲደርሱ በርካታ ወዳጅ ዘመዶቻቸው በተገኙበት ደማቅ አቀባበል ተደርጎላቸዋል::

አቶ ያሬድ ጥበቡ፣ በሚኖሩበት አሜሪካ ሆነው ከሁለት ወራት በፊት ለገበያ ያቀረቡትና ሀገር ውስጥም ከፍተኛ ተወዳጅነትን ያገኘው "ወጥቼ አልወጣሁም" የተሰኘውና የ25 ዓመት ጽሑፎቻቸውን አካቶ የያዘው መጽሐፍ፤ ቅዳሜ፣ ነሀሴ 19/2010 ዓ.ም በዋቢ ሸበሌ ሆቴል በደማቅ ሥነ ሥርዓት ይመረቃል ተብሎ ይጠበቃል::

በመጽሐፉ ምረቃ ላይ፣ በፖለቲካው ዓለም ሰፊ ልምድ ያላቸው አቶ ያሬድ ጥበቡ፣ የሀገሩ ጉዳይ እንደሚያሳስበው እንደ አንድ ዜጋ፤ "ሽግግሩ ምን መልክ ሊይዝ ይገባል?" በሚለው ነጥብ ላይ የተወሰኑ ምክረ ሐሳቦችን እንደሚያቀርቡ ገልፀዋል:: በተጠቀሰው ቀን፣ በዋቢ ሸበሌ ሆቴል፣ ከቀኑ 10፡00 እስከ 12፡00 ሰዓት በሚኖረው ቆይታ ዶ/ር ቴዎድሮስ ኃ/ማርያምን ጨምሮ የተለያዩ ሰዎች በመጽሐፉ ላይ አስተያየትና ትንታኔ ይሰጣሉ ተብሎ ይጠበቃል::

## ከስድስት ወራት በኋላ የሁሉም የስኳር ፕሮጀክቶች ግንባታ ይጠናቀቃል



ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ በባህር ዳር ከተማ ከብአዴን አመራሮች ጋር ባደረጉት ምክክር ላይ እንደገለጹት ግንባታቸው በተለያዩ ምክንያቶች ተጓትቶ የነበሩ የስኳር ፕሮጀክቶች፤ አሁን ላይ የማጠናቀቂያ ሥራ እየተሠራ መሆኑን ገልጸዋል። ባለፉት 9 ወራት የተሻለ ብሔራዊ መግባባትን ለመፍጠርና ኢኮኖሚያዊ ለውጦችን ለማምጣት ውጤታማ ተግባራት መከናወናቸውንም ተናግረዋል።

በአጭር ጊዜ ውስጥ የመጡት መልካም ለውጦች የበለጠ ተጠናክረው እንዲቀጥሉም፤ "ትክክለኛ የአመራር ስልትን ለመተግበር፣ አመራሮች ሓላፊነታቸውን ሊወጡ ይገባል" ማለታቸውን የአማራ ብዙኃን መገናኛ ድርጅት ዘግቧል።

## ጥልቅ ተሐድሶውን ተከትለው እየመጡ ያሉት ሀገራዊ ለውጦች በአብዛኛው ስኬታማ መሆናቸው ተገለጸ

ከነሐሴ 14 ጀምሮ ለሦስት ቀናት በተደረገው የኢህአዴግ ሥራ አስፈፃሚ መደበኛ ስብሰባ ጥልቅ ተሐድሶውን ተከትሎ የመጡ ያሉ ሀገራዊ ለውጦች፤ በአብዛኛው ስኬታማ መሆኑን የኢህአዴግ ጽ/ቤት ባወጣው መግለጫ ገልጿል።

በስብሰባው ኢህአዴግ በሁሉም መስኮች ለውጡን ተከትሎ የተከናወኑ ሥራዎች ስኬታማና አመርቂ መሆናቸውን የገለጸ ሲሆን፤ እየመጡ ያሉ ሀገራዊ ለውጦች ሕዝቡን ባሳተፈ መልኩ እየተፈጸሙ ናቸው ተብሏል።

በፖለቲካው መስክ የዴሞክራሲ ምህዳሩን ለማስፋት ታራሚዎችን ከመፍታት ጀምሮ የትጥቅ ትግል ያደርጉ የነበሩ የተለያዩ ድርጅቶች የትጥቅ ትግላቸውን በማቆም፤ ወደሀገራቸው ገብተው በውይይትና ድርድር እንዲሠሩ፣ የመንግሥት ሚዲያዎችን ጨምሮ በሌሎች ሚዲያዎችም ሐሳቦች በነፃነት የሚንሸራሸሩበት ሁኔታ መፈጠሩ እንደ አንድ ስኬት የታየ ሲሆን በዲፕሎማሲ፣ በኢኮኖሚውና ማኅበራዊ መስኮችም ተመሳሳይ ውጤቶች መገኘታቸው ተገልጿል።

ከለውጡ እንቅስቃሴ በተቃራኒ መንገድ የሚደረግ እንቅስቃሴ ከወዲሁ ካልተገታ ሥርዓት አልበኝነት ሊነግሥ እንደሚችል ሥጋቱን አስቀምጧል።

በቀጣይ ለውጡን የሚገዳደሩ ችግሮች በመኖራቸው ችግሮችን ተቋማዊ አሠራር በመከተል፤ እንዲሁም ሕዝቡን በተደራጀ መንገድ በማሳተፍ የተጀመረውን ለውጥ ለማዳረስ የትኩረት አቅጣጫ አስቀምጠዋል።

## አምነስቲ ኢንተርናሽናል የኢትዮጵያ መንግሥት የሶማሌ ክልል ልዩ የፖሊስ ኃይልን ትጥቅ እንዲያስፈታ ጠየቀ

ዓለም አቀፉ የሰብአዊ መብት ተሟጋች ድርጅት አምነስቲ ኢንተርናሽናል "ከፍተኛ የሰብዓዊ መብት ጥሰት እየፈጸመ ነው" ያለውን የሶማሌ ክልል ልዩ የፖሊስ ኃይል፤ የፌዴራል መንግሥት ትጥቅ እንዲያስፈታ እና ለበርካታ ንጹሐን ዜጎች ሞት እና አካል መጉደል ተጠያቂ የሆኑት የልዩ ኃይሉ አመራሮችም ለፍርድ እንዲቀርቡ ጠይቋል::

አምነስቲ ኢንተርናሽናል ለሶማሌ ክልል ልዩ የፖሊስ ኃይል ሥልጠና እና ድጋፍ የሚውል 15 ሚሊዮን ፓውንድ የገንዘብ ልገሳ አድርጓል ያለውን የእንግሊዝ መንግሥትን ወቅሷል::

የእንግሊዝ መንግሥት በበኩሉ፣ የሶማሌ ክልል ልዩ ኃይልን ከማሰልጠን አልፎ፣ "አስታጥቋል" ተብሎ በተለያዩ የመገናኛ ብዙኃን የተሰራጩ ዘገባዎች "የተሳሳቱ ናቸው" በማለት አስተባብሏል:: በሶማሌ ክልል ኢ.ኤ.አ ከ 2013 እስከ 2015 ድረስ ብሪታንያ ያደረገችው ድጋፍ ሕፃናትና ሴቶች ተኮር ለሆነ የፍትሕ ሥርዓት ማሻሻያ ሥልጠና መሆኑንም ገልጿል።

## ኢትዮ ቴሌኮም በስልክ አገልግሎት የታሪፍ ቅናሽ አደረገ!

ከፍተኛ አትራፊ ከሆኑ መንግሥታዊ ተቋማት መካከል አንዱ የሆነው ኢትዮ ቴሌኮም በስልክ አገልግሎት ላይ የታሪፍ ቅናሽ ማድረጉን ይፋ አድርጓል።

እንደ ተቋሙ ገለፃ በፊት ከነበረው የኢንተርኔት አገልግሎት የ43 በመቶ፣ የስልክ ድምጽ ላይ የ40 በመቶ፣ በተጨማሪም አጭር የሞባይል የጽሑፍ መልዕክት ላይ የ43 በመቶ ቅናሽ አድርጓል።

ethio telecom™
ኢትዮ ቴሌኮም

በዚህም መሠረት ከነሐሴ 16 ቀን፣ 2010 ዓ.ም ጀምሮ፤ ቀደም ሲል በሜጋ ባይት 35 ሳንቲም የነበረው የሞባይል ኢንተርኔት አገልግሎት 43 በመቶ ቅናሽ ተደርጎበት ወደ 23 ሳንቲም ዝቅ ብሏል። በደቂቃ 85 ሳንቲም የነበረው የሞባይል ስልክ ጥሪ ወደ 50 ሳንቲም ዝቅ እንዲልም ተደርጓል። በሞባይልና መደበኛ ብሮድ ባንድ ኢንተርኔት አገልግሎት ላይም እስከ 54 በመቶ ቅናሽ መደረጉ ታውቋል።

የብሮድ ባንድ ሲም ካርድ ሽያጭ ለጊዜው የተቋረጠ ሲሆን፤ በቀጣይ በመ/ቤቱ የቀረበውን መስፈርት ሊያሟሉ ከሚችሉ ሆቴሎች፣ ባንኮችና ሱፐር ማርኬቶች ጋር ግንኙነት በመፍጠር ወደ ሥራ እንደሚገባም ኢትዮ ቴሌኮም ገልጿል። በቅርቡ በጠ/ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ትዕዛዝ፣ የኢትዮ ቴሌኮም ዋና ሥራ አስፈፃሚን ጨምሮ በርካታ ባለሥልጣናት ከኃላፊነታቸው እንዲነሡ መደረጉ አይዘነጋም።

# የብርሃኑ ነጋና የአንዳርጋቸው ፅጌ ዘመን ተሻጋሪ ትሩፋት!





ካለፉት አራት ወራት ወዲህ በሀገሪቱ ውስጥ የታየውን ጅምር የለውጥ እንቅስቃሴ መሠረት በማድረግ፣ የተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲዎች ለሰላማዊ ትግል ወደ ሀገር ቤት መግባት ጀምረዋል፡፡ በትጥቅ ትግል ላይ የተሠማሩ ግንባሮች፣ ፈጣን በሆነ ምላሽ የተኩስ አቁም ስምምነት በማድረግ፤ ለዚህች ሀገር ቀጣይ ዕጣ ፈንታ ሰላማዊ ትግል ወሳኝ መሆኑን በማመን ወደኢትዮጵያ መመለስ ጀምረዋል፤ ለመግባት መሰናዶአቸውን ያጠናቀቁት ሳይረሱ፡፡

የወያኔ/ኢህአዴግ መንግሥት ሥልጣን ላይ በቆየባቸው ረዥም ዓመታት ለተፎካካሪ ፓርቲዎች የነበረው ዕይታና የሚወስደው የመጨፍለቅ እርምጃ፤ ምን ያክል አምባገነን መሆኑን ከማመልከቱ ባሻገር፣ ለሀገር ተቆርቋሪ የነበሩ አመራሮችንና ምሁራንን ያለ ውዴታቸው የስደት ሕይወት እንዲመሩ አስገድዷቸዋል፡፡ በሕዝብና በሀገር ፊት ነገሮችን ለመጋፈጥ የሞከሩ ጥቂት የማይባሉ የፖለቲካ ሰዎች፤ "ኦነግ"፣ "ኦጋዴን"፣ ሽብርተኛ"፣ "አርበኞች ግንቦት ሠባት አባል" የሚል ታፔላ እየተለጠፈባቸው፣ በማዕከላዊ ወንጀል ምርመራና የደህንነት መ/ቤቶች በሚፈበረኩ ሐሰተኛ ማስረጃዎች፤ እንዲሁም ለኢህአዴግ ታማኝ በሆኑ ሕግ አስፈፃሚዎች ፍርደ ገምድል ውሳኔ ለእስርና ለእንግልት ሲዳረጉ ከርመዋል፡፡

የህወሓት የበላይነት የበረሃው ዘመን ሐሳብና ድብቅ ዓላማ ሲተገበሩ በኖርንባቸው ባለፉት ሃያ ሠባት ዓመታት፤ ጠንካራ የሚባሉ የፖለቲካ ፓርቲዎች ብዙም ሳይራመዱ፣ በእንጭጩ እንዲፍረከረኩ የኢህአዴግ አስተዋጽኦ የጎላ የመሆኑን ያህል፤ በጥቅማ ጥቅሞች እየተደለሉ ምስጢሮችን ለመንግሥት አሳልፈው በመስጠት፤ ድርጅታቸው እንዲበታተንና የተለጣፊነት ቅርፅ እንዲይዝ ያደረጉ ፖለቲከኞችም ጥቂት አይደሉም፡፡ በሀገሪቱ ውስጥ ከሠባ በላይ የፖለቲካ ፓርቲዎች እንዳሉ በሚነገርበት በዚህ ወቅት እንኳን፤ ሕዝብ በቅጡ የሚያውቃቸውና በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ብልጭ ድርግም የሚሉት ቁጥራቸው ከአንድ ዕጅ ጣት ያለመብለጡን ስናስብ አብዛኞቹ ድርጅቶች በተቃዋሚነት ስም ከመንፈስ አባታቸው ኢህአዴግ ዳረጎት የሚቀበሉ ታማኝ ልጆች ሆነው አግኝተናቸዋል፡፡

የመለስ ዜናዊና ጓደኞቻቸው አምባገነናዊ አገዛዝ ክፉኛ የመረረውና የወያኔ ሀገርን የመበታተን ዓላማ ያስጨነቀው የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ አዳዲስ ተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች በተቋቋሙ ቁጥር የሚናፍቀው ተስፋ እንደ ጉም ሲበንበት ከርሟል፡፡ በኢህአዴግ ውስጥ የተፈጠረውን የፖለቲካና የአቋም ልዩነት ተጠቅመው፣ ከወራት በፊት ወደ ሥልጣን የመጡት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ግን ቀደም ሲል ከነበሩት የድርጅቱ አመራሮች ፅንፍ የያዘ የዘረኝነት መንፈስ በተለየ መልኩ፤ ሁሉም ድርጅቶች ለዘለቄታዊ ሰላምና ዕድገት እንዲሠሩ በር ከመክፈት ባሻገር፣ ወደ ሀገር ቤት እንዲገቡ ሁኔታዎችን አመቻችቷል፡፡

ይህንን ታሪካዊ አጋጣሚ በመጠቀም፣ የጀመሩትን የትጥቅ ትግል አቁመው ወደ ኢትዮጵያ ለመግባት መሰናዶአቸውን ካጠናቀቁት ድርጅቶች መሀል፣ አርበኞች ግንቦት ሠባት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ንቅናቄ በዋነኝነት ይጠቀሳል፡፡ በፕ/ር ብርሃኑ ነጋ የሚመራው ይህ አንጋፋ ድርጅት፤ ሥርዓተ አልበኝነት፣ አምባገነኑን በኢትዮጵያ ያነገሠውና በዜጎች ላይ ከባድ ኢ-ሰብዓዊ ጥሰቶችን የሚፈፅመው ሥርዓት፣ "ከሰላማዊ ትግል ባሻገር፤ በትጥቅ ትግልም ሊፈተን ይገባዋል" የሚል አቋም ይዞ በኤርትራ በረሃ የጦር ካምፖችን በማቋቋም ለስምንት ዓመት በላይ ወታደራዊ እንቅስቃሴዎችን ሲያደርግ ቆይቷል፡፡

አርበኞች ግንቦት ሠባት በከፍተኛ የሰው ኃይልና በበሳል አመራሮች በመዋቀሩ፣ በሀገር ቤት ውስጥም በብዙኃኑ ሕዝብ ዘንድ ድጋፍ ያለው መሆኑን የተረዳው ኢህአዴግ፤ በተለይም በአዲስ አበባና በአማራ ክልል የሚገኙ ጥቂት የማይባሉ ንፁሐን ዜጎችን በአርበኞች ግንቦት ሠባት አባልነት ሲያስር፣ ሲገርፍ፣ ዘር ሲያመክንና ሲገድል ቆይቷል፡፡ ፕ/ር ብርሃኑ ነጋና አንዳርጋቸው ፅጌን የመሳሰሉ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ ሰፊ ልምድ ዕውቀትና የሕዝብ ተደማጭነት ያላቸው ሰዎችንም በአሸባሪነት በመፈረጅ የሞት ፍርድ አከናንቧቸዋል፡፡ ከአንድ ሉአላዊ ሀገር ሕጋዊ መንግሥት በማይጠበቅ መልኩ ለየመን ደህንነቶች ብዙ ዶላሮችንን በመክፈል የአርበኞች ግንቦት ሠባት ዋና ጸሐፊ የሆኑትን አቶ አንዳርጋቸው ፅጌን ከየመን ሰነአ ከተማ አፍኖ ያመጣበት ሂደት በራሱ፤ የህወሐት/ኢህአዴግ ሰዎች፣ ይህ ድርጅት ምን ያህል እንደሚያስፈራቸው አመላካች ነው፡፡

ሰሞኑን ወደ ሀገር ቤት የሚገቡትን የአርበኞች ግንቦት ሠባት አመራርና አባላት ለመቀበል፣ በአዲስ አበባም ሆነ በመላ ሀገሪቱ ሽር ጉዱ ተጠናክሮ ቀጥሏል፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ወደ አሜሪካ በሄዱበት ወቅት፣ ከፕ/ር ብርሃኑ ነጋ ጋር ያደረጉትን ውይይት ከጥቂት ወራት በፊት አቶ አንዳርጋቸው ፅጌ ከእስር በተፈቱ ማግስት በቤተ መንግሥት ጋብዘው ማነጋገራቸውን ተከትሎ፤ ንቅናቄው ወደ ሀገር ቤት ገብቶ በሰላማዊ መንገድ እንዲታገል መፈለጉና ነፃ ተቋማትን ለመገንባት በሚደረገው ጥረት የበኩላቸውን አስተዋፅኦ ለማበርከት፣ በሙሉ ፈቃደኝነት ፊታቸውን ወደ ኢትዮጵያ እንዲያዞሩ ማስገደዱ፤ ቀጣይ የሀገሪቱ ዕጣ ፈንታ ብርሃን ፈንጣቂ ነው ብለን እንድናስብ ዕድል ፈጥሯል፡፡

አርበኞች ግንቦት ሠባት አዲስ አበባ ሲደርስ የሚኖረው አቀባበል ከወዲሁ ብዙዎችን አጓጉቷል፡፡ በድርጅቱ በይፋ ከተወከለው አቀባበል ኮሚቴ ባሻገር፤ በየቦታው፣ በየሰፈሩ የተቋቋሙ ስብስቦችና እንቅስቃሴዎች የነፃነት ታጋዮች ሀገር ቤት ሲደርሱ፤ ለዘመናት በጽናት የታገሉለትና የደከሙለት ዓላማ ሜዳ ላይ እንዳልቀረ አመላካች የሆነ ከፍተኛ የሕዝብ ፍቅርና አክብሮት በማትረፍ እንደሚያረጋግጡ የሚታዩት ሰሞነኛ የመዲናችን እንቅስቃሴዎች ያመለክታሉ፡፡

ለሰላማዊ ትግል ወደ አዲስ አበባ የሚገባውና በእነ ፕ/ር ብርሃኑ ነጋ የሚመራው የከፍተኛ አመራሮችና የአባላት ልዑካን፤ በተለያዩ ክልሎች በሚያደርጋቸው ውይይቶችና ቅስቀሳዎችም ተመሳሳይ የሆነ የሕዝብ ድጋፍ እንደሚጠብቀው አያጠራጥርም፡፡ ድርጅቱ በ2012 ዓመት ከሚያከናውነው ሀገራዊ ምርጫ በፊት መሠራት ባለባቸው የነፃ ተቋማት ግንባታና እውነተኛ ዴሞክራሲን በሀገሪቱ ውስጥ የማስፈን ሥርዓት ውስጥ፣ ቀደም ሲል በሀገሪቱ ውስጥ በተለያየ የታሪክ አጋጣሚ ታይተው ከነበሩት ስህተቶች በመማር፤ በቀጣይነት ያለውን ድጋፍና ተቀባይነት ይዞ ለመዝለቅ ሕዝብን መሠረት ያደረጉ አጀንዳዎችን ቀርፆ ለትግበራቸው ባለችው ጥቂት ጊዜ ውስጥ ትኩረት ሰጥቶ መሥራት ይኖርበታል፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝብ የነፃነት ትግል ተምሳሌት እንደሆኑ የሚነገርላቸው ብርሃኑ ነጋና አንዳርጋቸው ፅጌ ዕድሜያቸውን፤ ዕውቀታቸውን፣ ገንዘባቸውን ያፈሰሱለት፤ ከፍ ብለው ተባብረው የኖሩትን ያህል፣ በአምባገነኖች በትር ዝቅ ብለው እንዲሸነቆጡና ዘብጥያ እንዲወርዱ፤ ከወገን እንዲገፉና እንዲርቁ የተደረጉበት፤ የእድሜ መግፋት ሳይገድባቸውም በረሃ የወረዱላትን የወደቁላትን፣ የተነሡላትን፣ ላይ ታች የባዘኑላትን ሀገራቸውን፤ ከመቼውም ጊዜ በላይ ሊያገለግሏትና የሕዝቧን ሰላምና አንድነት ሊመልሱላት የሚያስችለው አጋጣሚ ይህ ነውና፤ መላው የአርበኞች ግንቦት ሠባት አመራር አባላት ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ተደጋጋሚ የሆኑ ጥልቅ ውይይቶችን ማድረግ እንዳለባቸው ሳንጠቁም አናልፍም፡፡

# ብሔራዊ መረጃና ደህንነት

## ከፓርቲ መጨቆኛነት ወደ ህዝብ አገልጋይነት

መላኩ ብርሃኑ

አዲሱ የብሔራዊ ደህንነት አገልግሎት ሓላፊ ጄኔራል አደም መሀመድ ባለፈው ረቡዕ በሰጡት መግለጫ፣ ተቋሙ በአዲስ መልክ ከተዋቀረበት ካለፉት ሦስት ወራት ጀምሮ፤ አመርቂ ተግባራት ማከናወኑን ተናግረዋል። በተለይም እየተገበረ ካለው አዲስ አደረጃጀትና በረቂቅ ደረጃ ከተዘጋጀው አዲስ የማቋቋሚያ አዋጅ ሥራ ባሻገር የሕገ ወጥ መሣሪያዎች ዝውውርን ተከታትሎ በቊጥጥር ሥር በማዋል፣ ዶላር ከሀገር ለማስወጣት የሚደረግ እንቅስቃሴን በማክሸፍ እንዲሁም በአዲስ አበባና በዙሪያዋ በቦምብ የታገዘ የሽብር ተግባር ዝግጅትን በማምከን ውጤታማ ሥራ እንደተሠራ ተናግረዋል።

በተለይም፣ ከሰኔ 16 የመስቀል አደባባይ የቦምብ ጥቃት አስቀድሞ በደህንነቱ የተደረሰባቸውና ብዛት ካላቸው ቦምቦች ጋር በቁጥጥር ሥር የዋሉ የሽብር ቡድኖች መኖራቸውን፣ እንዲሁም ለሕዝብ ይፋ ያልተደረጉ ለማስፈራራት እና በግለሰቦች ላይ ጥቃት ለመፈጸም የተደራጁ ገዳይ ቡድኖች (ስኳድ) በአገልግሎቱ ክትትል እንደተያዙም ተናግረዋል።

ከዚህ አንጻር በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት ዳግም የተዋቀረውና አዳዲስ ለውጦች እየታዩበት የሚገኘው የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ከሕዝብ አገልጋይነት እና ከሀገር ሰላምና ደህንነት ጥበቃ አንጻር የትናንት እና የዛሬ ገጽታው ምን ይመስላል? በርግጥስ ነገ በዛሬ ፍልስፍናው መቀጠል የሚችል ተቋም ነወይ? የሚሉትን ፍሬ ሐሳቦች ይህ ጽሑፍ በአጭሩ ለመዳሰስ ይሞክራል።

### ከደህንነት የሚያሠጋው "ደህንነት"

በኢትዮጵያ በሕዝብ ዘንድ እጅግ ከሚፈሩ የመንግሥት ተቋማት ውስጥ የደህንነት ተቋምን ያህል ስሙ የብዙዎችን ልብ የሚያርድ ተቋም የለም። ከአጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመን ጀምሮ አሁን እስካለንበት ጊዜ ድረስ፤ የኢትዮጵያ የስለላና የደህንነት ተቋም መለያዎች ምስጢራዊነት፣ አፋኝነት፣ ከሕግ በላይ መሆንና ፈላጭ ቆራጭነት እንጂ፤ ሕዝብ አገልጋይነት አልነበረም። በአጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት የነበረው የኢትዮጵያ የስለላ እና የደህንነት መዋቅር እንደቀደሙት አጼዎች የስለላ ተቋማት ሁሉ ተለምዶአዊ የሆነ ሕዝብን የመሰለል እና የሥርዓቱ ጠላቶች የሚላቸውን እያሰረ የማንገላታት ተግባር ሲያከናውን ኖሯል። በየጠላና ጠጅ ቤቶች ሳይቀር ሲቪል ለባሽ ሰላዮችን እየላከ፣ በአጼው እና አገዛዛቸው ላይ ሐሜትና አሉታዊ ንግግር "ተናግረዋል" ያላቸውን ሁሉ እየቀፈደደ መግረፍ እና ማሰር ዋና ሥራው ነበር።

በተለምዶአዊ አሠራር የተዋቀረው የአጼው የስለላ እና የደህንነት መዋቅር በሰለጠኑት ሀገራት ካሉ መሰል ተቋማት ጋር ሲነጻጸርለ ደረጃው ዝቅተኛ መሆኑና ዘመናዊነት ያልዳሰሰው መሆኑ ከግንዛቤ ገብቶ ሊሻሻል የሚገባው መሆኑም በጊዜው ታምኗል። በዚህም ሳቢያ ወቅቱ ከደረሰበት ዘመናዊነት እና ከጊዜው አስተሳሰብ ጋር የሚሄድ አዲስ አወቃቀር ይዞ እንዲደራጅ ተወሰነ።

የአጼ ኃይለ ሥላሴ አስተዳደር የስለላ ተቋሙን ዘመናዊ ለማድረግና አሠራሩንም ለማሻሻል በወሰደው እርምጃ፣ በ1959 ዓ.ም "የሕዝብ ጸጥታ ጥበቃ ረዳት ዋና ክፍል" የሚል ተቋም አቋቁሟል። በዚህ ተቋም ውስጥ ከተዋቀሩት ክፍሎች ዋናው፣ "ልዩ ክፍል" የሚባለው ሲሆን "በከተማውና በአካባቢው የሚፈጸሙትን ልዩ ልዩ የተንኮል ተግባራት በምስጢር በመከታተል የማጥናት ተግባር ያከናውናል" የሚል ሓላፊነት ተሰጥቶት ነበር። በዚህ የልዩ መከታተል ተግባር /ስለላ/ ተሳታፊዎቹ የክፍሉ ዳይሬክተሮችና የበላይ ባለሥልጣናት ብቻ የሚያውቋቸው የምስጢር አባላት እንደነበሩም "የስለላ ነጥቦች" የተባለው መጽሐፍ ያስረዳል።

በቅርቡ፣ "አንዳርጋቸው ጽጌ ለአንድ ዓመት ያህል ታስሮበት ነበር" የሚባለውና አሁንም አገልግሎቱ ምን እንደሆነ በግልጽ የማይታወቀው፣ ገነት ሆቴል አጠገብ የሚገኘው ባለሦስት ፎቅ ሕንጻ፣ በአጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመን "ልዩ ካቢኔ" በመባል ይታወቅ የነበረ እጅግ አስፈሪ የሆነ የደህንነት ተቋሙ ማሰሪያና መግረፊያ ቦታ ነበር። ልዩ ካቢኔ በጊዜው፣ "የመንግሥት ጸጥታ ክፍል" በሚባል ስያሜ የተዋቀረ ሲሆን፤ ዋና ዓላማውም እንደስሙ ሕዝቡን ጸጥ አድርጎ መግዛት እንደነበር በጊዜው ያከናውናቸው ከነበሩ ሥራዎች መገንዘብ ይቻላል።

### "ግድግዳዎችም ጆሮ አላቸው"

ስለላ ሲታሰብ ወደሁሉም ኢትዮጵያዊ አዕምሮ የሚመጣው ቃል፣ "ጆሮ ጠቢ" የሚለው ለዘመናት ከዚህ ሥራ ጋር ተዳብሎ የተሰጥ ቅጽል ስም ነው። ብዙዎች እንደሚገምቱት ኢትዮጵያዊን ተጠራጣሪ (ለሚናገረው ሁሉ ከንፈሩን የሚጠብቅ፣ በሚንቀሳቀስበት ሁሉ ጥላውን የሚፈራ) ያደረገው፣ በየወቅቱ ሀገሪቱን ያስተዳደሩ ገዢዎች የሚዘረጉት መፈናፈኛ የሚያሳጣ እና እያንዳንዱ ሰው ጓዳ ድረስ የሚዘረጋ የስለላ መዋቅር ነው። ማንም ዜጋ በመንግሥቱ ላይ ግልጽ ተቃውሞ ሊያቀርብ ቀርቶ፣ በስህተት እንኳን ክፉ ቃል መናገር እስር፣ አፈና እና ግርፊያ ከዚያም ሲብስ ግድያ ያስከትልበት ነበር። በዚህ ሳቢያ፣ ማንኛውም ሰው ከሰዎች ጋር ሆኖ ቀርቶ ብቻውን እንኳን መንግሥቱን የሚቀናቀን ክፉ ቃል ከአፉ እንዳይወጣ ይጠነቀቅ ነበር።

የስለላ መዋቅሩ፣ "እያንዳንዱ ሰው ጓዳ ድረስ የዘለቀ ጆሮ ጠቢ አለው" ተብሎ ስለሚታመንና የአንድ ሰው ንግግር በማን እና እንዴት እንደሚሰማ ስለማይታወቅ፤ ከጥንቃቄ ብዛት "ግድግዳዎችም ጆሮ አላቸው" እስከማለት ተደርሶም ነበር። "እብድና ዘበናይ የፈለገውን ይናገራል" እየተባለ የአዕምሮ ህሙማን የፈለጉትን መናገራቸው እስኪያስቀና ድረስ የዜጎች በነጻ ሐሳብን የመግለጽ መብትም ተገድቦ ኖሯል። የዚህ ሁሉ መነሻ መንግሥታት የአገዛዝ እድሜያቸውን ለማራዘም የዘረጉት ተቀናቃኞቻቸውን በጽኑ የአፈና ቀንበር ውስጥ የሚያኖር የስለላ እና አፈና ተቋም ማደራጀታቸው ነው።

### ስለላና ሕዝብ ደህንነት

የአጼው ዘመን አክትሞ የደርግ መንግሥት ሥልጣን ሲይዝ፣ በመጀመሪያ ካደራጃቸው ቁልፍ የሥርዓቱ መዋቅሮች አንዱና ዋናው ገናና ስም የነበረው፣ ሕዝብ ደህንነት መሥሪያ ቤት ነበር። በሶቭየት ሕብረቱ ኬጂቢ አምሳያ የተደራጀው ይህ የሕዝብ ደህንነት መሥሪያ ቤት ሲቋቋም የወረሰው ጽህፈት ቤት ያንኑ የገነት ሆቴሉን የአጼው ዘመን የመንግሥት ጸጥታ (ልዩ ካቢኔ) ቢሮ ነው። "ሕዝብ ደህንነት መሥሪያ ቤት"ን ▶

ከልዩ ካቢኔ ወይም ከመንግሥት ጸጥታ ቢሮ የለየው፤ ስሙ ብቻ እንጂ፣ በምግባር ከዚህኛው ቢብስ እንጂ፣ የማያንስ አፋኝ ተቋም ነበር። ሕዝብ ደህንነት መባሉ ሥራውን ሕዝባዊ ለማስመሰል ስም ከመለጠፍ የተለየ ትርጉም አልነበረውም።

የሕዝብ ደህንነት ተቋም ከማናቸውም ያለፉ የኢትዮጵያ ገዢ መንግሥታት የስለላ ተቋማት በላቀ፣ እጅግ አስፈሪና ጨካኝ፤ እንዲሁም አፋኝ የስለላ ድርጅት እንደነበር ይነገራል። ደርግ ይህንን አፋኝ መሥሪያ ቤት በብቃት ካደራጀ በኋላ፣ ቢሮውን ከገነት ሆቴል በመንቀል ባምቢስ አካባቢ ወደሚገኘውና ከብስራተ ወንጌል ራዲዮ ጣቢያ ወደወረሰው ትልቅ ሕንጻ በማዛወር በሰፊው አዋቅሮታል። አስፈሪና ረጅም ክንዱን እስከ ቀበሌ ድረስ በመዘርጋትም፤ ንዑሳን ጆሮ ጠቢዎችን አደራጅቶ እያንዳንዱን ዜጋ፣ "አንሶላው ድረስ" ዘልቆ ይሰልል እንደነበርም ታሪኩን የሚያውቁ ብዙዎች ይናገራሉ። ብዙዎች ጸሐፍያን በብእራቸው እንደከተቡት፤ የደርግ የሕዝብ ደህንነት መሥሪያ ቤት፣ እጅግ በከፋ መልኩ ለብዙ ኢትዮጵያውያን ሞትና አሰቃቂ ምርመራ ሰለባነት እንዲሁም መታፈንና እንደወጡ ሳይመለሱ መቅረት ምክንያት ነው።

## የኢህአዴግ መረጃና ደህንነት

ከ1983 ዓ.ም በፊት በኢትዮጵያ የነበሩት የስለላና የደህንነት ተቋማት፣ በየትኛውም ሀገር እንደሚገኙ ለአንድ ሀገር የሰላምና ጸጥታ መረጋገጥ እንዲሁም ሉዓላዊነት መጠበቅ ወሳኝ የሆኑ የደህንነት ተቋማት ሁሉ ለብሔራዊ ጥቅም ያከናወኑት ተግባር የሚዘነጋ ባይሆንም፤ ያንን ተግባራቸውን የሚያፈርስ ዜጎችን የመበደል ሥራ ሲሠሩ መኖራቸው ግን በሕዝብ ዘንድ በመልካም እንዳይታዩ አድርጓቸዋል። ከዚህ አንጻር በተለይ በወታደራዊው የደርግ መንግሥት የጭቆና እና ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ እንዲሰፍን ወሳኙን ድርሻ የተጫወተው አስፈሪው የሕዝብ ደህንነት መሥሪያ ቤት ኢህአዴግ አዲስ አበባን ሲቆጣጠር አበቃለት ተብሎ ነበር። ኢህአዴግ ሥልጣን ሲይዝ ሲታገላቸው ከኖሩት የወታደራዊ መዋቅሮች አንዱ በመሆኑ ብቻ ሳይሆን፤ የራሱን ሰርጎ ገብ ታጋዮች ጭምር በሜንጦ እየለቀመ፤ ዘግናኝ ድብደባና ግድያ የፈጸመበትን ይህንን የሕዝብ ደህንነት መንግሥት ቤት ያለጥርጥር "ያፈርሰዋል" ብለው የገመቱ ብዙዎች ነበሩ።

ኢህአዴግ የወሰደው እርምጃ ግን በተቃራኒው ነበር። ግንባሩ ሥልጣን እንደያዘ ሰሞን የበረሃ ደህንነቱን ሥራ በተቀናጀና በዘመናዊ ደህንነት ለመተካት በማሰብ ይሁን፣ አልያም ለሚዘረጋው ሥርዓት እጀግ አስፈላጊ ሆኖ አግኝቶት፤ የደህንነቱን ሥራ ከደርግ ባለሙያዎች ለመማር ዋነኛ የደህንነት አንቀሳቃሽ የነበሩ ግለሰቦችን ከእስር ቤት ድረስ እያስጠራ ራሱን ሲያሰለጥን ቆይቷል። የደህንነት ሥራ እውቀት አንድን ሀገር በሰላምና በመረጋጋት ለመምራት አስፈላጊ ጉዳይ ቢሆንም፤ ኢህአዴግ፣ ሕዝብ ከሚጠላውና የብዙ ግፍ ማጎደር ከነበረው የሕዝብ ደህንነት ቁልፍ ባለሙያዎች፣ "የደህንነት ትምህርት ለመውሰድ ፍላጎት ይኖረዋል" ብሎ የገመተ ሰው አልነበረም። ኢህአዴግ በጊዜው ከሕዝብ ደህንነት መዋቅር ውስጥ የሚጠቀመውን መርጦ ወስዶ ሊሆን እንደሚችል ይገመታል። የለወጠው አንድ ነገር ግን የዚህን ተቋም ዋና መምሪያ ሕንጻ ለፌዴራል ፖሊስ ቢሮ ሰጥቶ እዚያው አቅራቢያ "ሳልኮስት" የሚባለው ሕንጻ አካባቢ የሚገኝ አንድ ሰዋራ ግቢ ውስጥ መግባት ብቻ ነበር። ይህንን የኢሚግሬሽንና ስደተኞች ጉዳይ መምሪያ ንብረት መሆኑ የሚነገርለትን ግቢ ደህንነት መንግሥት ቤቱ ሲወስደው፣ በዋናነት የተጠቀመበት፤ ኢሳት ቴሌቪዥን በቅርቡ፣ "የእስር ማዘዣ ተቆርጦበት ወደሱዳን ሸሽቷል" ብሎ ላወራባቸውና በብዙዎች ዘንድም፣ "ምስጢራዊ፣ ድብቅ እና አወዛጋቢ ናቸው" ለሚባሉት የተቋሙ አለቃ ለአቶ ጌታቸው ዋና ቢሮነት ነው።

ኢህአዴግ ከ1983 ጀምሮ በራሱ ፍላጎትና በአዲስ መልክ ሲያዋቅረው የቆየውን ይህንን ተቋም በ1987 በወጣው አዋጅ ቁ. 06/87 መሠረት "የደህንነት፣ የኢሜግሬሽንና የዜግነት ጉዳይ ባለሥልጣን" በሚል ስያሜ ሰጥቶ ሥራ አስጀምሮታል። ላለፉት 23 ዓመታትም የኢትዮጵያ የስለላ፣ የብሔራዊ ጸጥታ እና የደህንነት ሥራዎች በዚህ ተቋም ወይም በርሱ የበላይ ተቆጣጣሪነት ሲከናወኑ ኖረዋል ማለት ይቻላል። ይህ ተቋም ካከናወናቸው ሰፊና የማይካዱ የብሔራዊ ጸጥታና ሰላም ማስከበር፣ የሽብር ጥቃትን መከላከል፣ የሀገሪቱን ጥቅም የሚነኩ ማናቸውንም ተግባራትን የማምከን ዓይነት በጎ ሥራዎች ባሻገር፤ ዛሬ ይፋ የወጣበትን የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት፣ የዜጎች ግድያ፣ ግርፊያና አፈና፤ እንዲሁም ሆን ተብለው የተቀነባበሩ የሽብር ተግባራት (Staged terror acts) "ፈጽሟል" ተብሎም እየተከሰሰ ነው። ማንም ዜጋ በሚያወቀው ልክ ይህ ተቋም አስፈሪና የማይነካ እንዲሁም እጅግ ምስጢራዊ እና በኢህአዴግ ለተከናወኑ ብዙ ጥፋቶች፣ "ዋና ተዋናይ ነው" ተብሎም ጣት ተቀስሮበታል።

በየትኛውም ሀገር የሚገኙ የደህንነትና መረጃ መንግሥት ቤቶች፣ ከሌሎች የመንግሥት ተቋማት የሚለዩበት አንድ የጋራ ነጥብ የሚያከናውኑት ተግባር ምስጢራዊ መሆኑ ነው። ዋና ሥራቸው ከሕዝብ ሰላምና ከሀገር ደህንነት ተቃራኒ የሆኑ ሴራዎችን ማክሸፍ እንደመሆኑ፤ ተግባራቸው በአብዛኛው በምስጢር የሚከናወንና ፍጻሜ ቢያገኝም ይፋ የማይደረግ ነው። ይህ በሁሉም ሀገራት አወቃቀሩ እጅግ ምስጢራዊ የሆነ ተቋም፣ አንዳንዴ ያለበት ቦታና ቢሮው ጭምር እስከማይታወቅ ድረስ እያለ እንደሌለ ሆኖ የሚኖር ነው። የኢትዮጵያውን ከሌሎች የሚለየው ግን በአካል ባይታይም ቅሉ፣ መንፈሱ ግን ሚሊዮኖችን የማሸበር አቅም ያለው መሆኑ ነው።

በ2005 አካባቢ ይህ ተቋም በ"ብሔራዊና የመረጃና የደህንነት አገልግሎት ረቂቅ አዋጅ" መሠረት በሚኒስቴር መንግሥት ቤት ደረጃ ብሔራዊና የመረጃና የደህንነት አገልግሎት በሚል ስያሜ በአዲስ መልክ ተቋቁሟል። ይህን አዋጅ፣ ከቀደመው የደህንነት ተቋማት ማደራጃ አዋጆች የለየው ነገር የተቋሙ ዓላማዎች፣ ሥልጣንና ተግባራቱ፣ እንዲሁም ተጠያቂነቱና ስለ ቁጥጥር ሂደቱ በተመለከተ ግልጽ ድንጋጌዎችን መያዙ ነው። ለምሳሌ የዚህ ተቋም እንቅስቃሴ "በሕግ አውጪው፣ አስፈጻሚውና በዳኝነት አካላት ቁጥጥር ሥር እንደሚውል" በአዋጁ በግልጽ የተደነገገ ቢሆንም፤ ይህና ሌሎች አንቀጾች ግን በተግባር ላይ ስለመዋላቸው አንድ ሁለት ተብሎ የሚቀርብ ማስረጃ የለም። ምክንያቱ ደግሞ ተቋሙ አንድም ቀን ፓርላማ ቀርቦ ስላከናወነው ተግባር ሪፖርት ሲያሰማ፣ አልያም በሩን ለመገናኛ ብዙኃን ክፍት አድርጎ መግለጫ ሲሰጥ ወይም ተጠያቂነቱን የሚያረጋግጡ የሕግ አካላት ክሶችና ወቀሳዎች ሲቀርቡበት አለመታየቱ ነው።

በአብዛኛው የደህንነት መዋቅሮች ሲቋቋሙ ምንም እንኳን በዚህ መልኩ ተጠያቂነት ያለባቸው እንደሆኑ እንዲታወቅ በይስሙላ አዋጅ ተሸፍነው ቢሆንም፤ በተግባር የሚቆጣጠራቸውና ሪፖርት የሚቀርብለት አካል ግን የሀገሪቱ የመንግሥት ከፍተኛ የሥልጣን እርከን ላይ ያለው ግለሰብ ነው። በአዋጁ ላይ የተመለከቱት የሕግ አውጪ እና ተርጓሚ መንግሥት ቤቶች ሥራውን ለመፈተሽ የሚያገኙት ዕድል በዚህ ስሌት ዜሮ የሆነበት ምክንያትም ይህ እንደሆነ ይገመታል።

## ከባለሥልጣንነት ወደአገልጋይነት?

"በመንግሥት ውስጥ ሌላ መንግሥት" በመባል የሚታወቁት፣ የኢትዮጵያ የስለላም ይሁኑ የመረጃና ደህንነት ተቋማት፤ በፖለቲካ ታሪካችን ውስጥ ሁሌም የሥርዓቶቹ ቀኝ እጆች ሆነው ኖረዋል። አስፈሪ ያደረጋቸው ገጽታ የሚመነጨው በሥርዓቶቹ የበላዮች፣ "አድርጉ" የተባሉትን ሁሉ ማድረጋቸው፤ "አስፈጽሙ" የተባሉትን ሁሉ ማስፈጸማቸው ነው።

በኢትዮጵያ፣ መንግሥታት ሕዝባቸውን ሲሰልሉ መኖራቸው አዲስ ወሬ ባይሆንም፤ ኢህአዴግ እንደመንግሥት ሀገሪቱን ባስተዳደረበት እስከዛሬ ባሉት 27 ዓመታት ውስጥ ያካሄዳቸው ዜጋ ተኮር ስለላዎች ግን፤ በዘመናዊነታቸው እና በከፍተኛ ወጪ ጠያቂነታቸው ወደር የሚገኝላቸው አይመስሉም። ለምሳሌም፡- ኢህአዴግ በዚሁ የመረጃና ደህንነት አገልግሎት ተቋሙ አስፈጻሚነት 'ፊን ስፓይ' የተባለ የኢንተርኔት ስለላ መሣሪያ ገዝቶ ዜጎችን ለመሰለል ጥቅም ላይ ማዋሉን መሣሪያውን የሸጠለት ድርጅት ከስድስት ዓመታት በፊት አጋልጧል። በጊዜው የኢንፎርሜሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስትሩ ዶክተር ደብረ ጽዮን ድርጅቱ ያጋለጠውን ምስጢር አስመልክተው ማስተባበያ ሰጥተዋል። ያም ሆኖ የኢትዮጵያ መንግሥት ብሎገሮችን እና አንዳንድ የፖለቲካ አክቲቪስቶችን ከዚያም አለፍ ሲል የፖለቲካ ፓርቲ አመራሮችን ሲያስር፤ "ማስረጃ" ብሎ ለፍርድ ቤት የሚያቀርባቸው ሁሉ ግለሰቦቹ በግል ግንኙነታቸው በኢሜይል እና በድምጽ

> አለምአቀፍ ሚዲያዎች በበኩላቸው እንደ ኢትዮጵያ ያሉ ደሃ ሀገራት ለስለላ ተግባራት ሊውሉ የተመረቱ የስለላ መሳሪያዎችን እጅግ ከፍተኛ በሚባል ወጪ እየገዙ በዜጎች ግላዊ መብት ላይ ጋሬጣ በመፍጠር እያንዳንዱን ንግግራቸውንና ጽሁፎቻቸውን ወደ መንግስት ሰርሾር እየላኩ ነው

የተለዋወጧቸው መልክዕቶች መሆናቸው፤ በርግጥም፣ “የገዛቸውን መሣሪያዎች ለስለላ ጥቅም ላይ ማዋሉን አመላካች ናቸው” በሚል የሚኒስትሩን ማስተባበያ፣ “ሐቅን መደበቅ ነው” በማለት የተቹም ብዙዎች ናቸው፡፡

ዓለም አቀፍ ሚዲያዎች በበኩላቸው፣ “እንደ ኢትዮጵያ ያሉ ደሃ ሀገራት ለስለላ ተግባራት ሊውሉ የተመረቱ የስለላ መሣሪያዎችን እጅግ ከፍተኛ በሚባል ወጪ እየገዙ፤ በዜጎች ግላዊ መብት ላይ ጋሬጣ በመፍጠር እያንዳንዱን ንግግራቸውንና ጽሑፎቻቸውን ወደ መንግሥት ሰርቨር እየላኩ ነው” በማለት ክስ አቅርበዋል፡፡

## መረጃና ደህንነት በአዲስ ጎዳና “ከመንፈስነት ወደሥጋነት?”

ካለፉት ሦስት ወራት ወዲህ፣ በዚህ የብሔራዊ ደህንነትና መረጃ አገልግሎት ዙሪያ የሚወሩ ጉዳዮች የብዙ ኢትዮጵያውያንን ቀልብ ስበዋል፡፡ የዶክተር ዐቢይ አሕመድን ወደጠቅላይ ሚኒስትር ወንበር መምጣት ተንተርሶ ከተወሰዱት እርምጃዎች አንዱ፣ ይህንን አስፈሪና በሕዝብ ዘንድ ጥላ ተደርጎ የሚታይ ተቋም ርስት አደርገው ሲመሩት የኖሩትን አለቃ አቶ ጌታቸውን ከሥልጣናቸው ማንሣትና በምትካቸው ጄኔራል አደም መሀመድን ማስቀመጥ ነበር፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አቶ ጌታቸውን ከዚህ ሥልጣናቸው ሲያነሡ ከስማቸው በቀር ፎቶግራፋቸውን እንኳን ዐይቶ የማያውቀው ሕዝብ ተገርሟል፡፡ በከፍተኛ የዜጎች ሰብዓዊ መብት ጥሰት የሚከሰሰውንና በማስመሰል ሽብር ሀገርንና ሕዝብን ያህል ግዙፉን የፖለቲካ ዓላማ ለማስፈጸም ሲባል፣ “ጉዳት ላይ ጥሏል” የተባለውን ይህንን ተቋም ሲመሩ የኖሩት አቶ ጌታቸውና ምክትላቸው የነበረው ኮሎኔል ተክለ ወይኒ፣ “ዕጣ ፈንታቸው ምን ይሆናል?” የሚሉ ጥያቄዎችም ተነሥተው ነበር፡፡

እነዚህ አመራሮች ከተጠበቀው ጊዜ ዘግይቶም ቢሆን፣ ከተቋሙ ከተሰናበቱ በኋላ የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አስተዳደር ቀዳሚውን እርምጃ የወሰደው፣ “የህወሓት አባላት ናቸው” የተባሉ ብዛት ያላቸውን የተቋሙን የደህንነት ሠራተኞች ማሰናበት ነበር፡፡ ብዙዎች፣ “የአንድ ክልል ተወላጆች የሞሉት ተቋም ነው” ሲሉ የሚተቹት ይህን የደህንነት አገልግሎት ተቋም፤ በአዳዲስ አባላት በመተካት በሠራተኛ ረገድ የብሔር ስብጥር እንዲኖረውም ተደርጓል፡፡ በተለይም “የደህንነት አባል የሆነ የትኛውም ግለሰብ፣ የማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ አባል መሆን አይችልም” የሚል መመሪያ በማውጣት የፓርቲ አባላት የሆኑትን ለይቶ አሰናብቷል፡፡ ጄኔራል አደም በሰጡት መግለጫ፣ “በዚህ የሕዝብ ተቋም ውስጥ፣ የፓርቲ አባል ሆኖ መቀጠል አይቻልም” የሚል ቆምጨጭ ያለ ማስጠንቀቂያም አስተላልፈው ነበር፡፡

ከዚህ በኋላ ዋና ቢሮውን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሕንጻ ውስጥ ያደረገውንና እስካሁን ድረስ ግን ማንም የማያውቀውን የብሔራዊ ደህንነት አገልግሎትን ዘመናዊ ሕንጻ ለመጀመሪያ ጊዜ ለጉብኝት ክፍት አድርገውታል፡፡ እሑድ፣ ሐምሌ 14 ቀን፣ 2010 ዓ.ም የተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲ አመራሮች ተቋሙን ጎብኝተዋል፡፡ በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አዲስ የአገልግሎቱ ማሻሻያ አቅጣጫ መሠረት ተግባራዊ የተደረገው ይህ ተቋሙን ለሕዝብ ክፍት የማድረግና ከመፈራት ይልቅ የሚከበር የሕዝብ አገልጋይ መሆኑን የማስመስከር ሂደት፣ በፖለቲካ ፓርቲ አመራሮች ዘንድ አድናቆትን አግኝቷል፡፡ “እንዲህ ዓይነት ነገር በታሪክ መመዝገብ ያለበትና እንኳን ሊጎበኝ ቀርቶ በርቀት የማይታይን ተቋም በዚህ መልኩ አስተያየት እንድንሰጥበት መደረጉ መልካም ጅምር ነው” ነበር ያሉት የፓርቲ አመራሮቹ ከጉብኝት መልስ ለቀረበላቸው ጥያቄ ሲመልሱ፡፡

ጄኔራል አደም፣ የተቋሙ ሓላፊ ሆነው በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ከተሾሙ በኋላ፤ ይህ ተቋም ለኢትዮጵያ ሕዝብ ቅርብ ሊሆን እንደሚገባውና በአሠራሩም ላይ የጋራ መግባባት መፍጠር አስፈላጊ መሆኑን በመገንዘብ፤ በሪፎርም ደረጃ ግልጽ አሠራሮችን ለማስፈን በገለልተኛ ተቋምነት እንደሚሠራ ተናግረውም ነበር፡፡ “እዚህ የሚሠራ ማንም አካል ለሕዝብ ብቻ የወገነና ከፖለቲካ ፓርቲ አባልነት ጸድቶ ማንም ይምጣ ማን፤ ወደፊት የሚቀጥል ተቋም ይሆናል” ነበር ያሉት ጄኔራሉ በመግለጫቸው፡፡ በዋሽንግተን ዲሲ ከተፎካካሪ ፓርቲዎች ጋር ውይይት ሲያደርጉ የነበሩት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ የተቋሙን መሠረታዊ ለውጥ ሲያስረዱ፣ “እንኳን ሕዝቡ፣ አንድ ሚኒስትር እንኳን ብሔራዊ ደህንነት ተቋምን ልጎብኝ ብሎ የጠየቀም የለም፤ የጎበኘም የለም፤ ይህንን (የተፎካካሪ ፓርቲዎችን ጉብኝት) ያደረግነው ተቋሙ የሚሠራቸውን ሥራዎች ሕዝቡ እንዲያውቀውና የሕዝብ እንዲሆን ለማድረግም ጭምር ነው” ነበር ያሉት፡፡

በተግባር ያለመተርጎሙ እንጂ ቀድሞም የአገልግሎቱ ማቋቋሚያ አዋጅ በመግቢያው ውስጥ አገልግሎቱን እንደገና ማቋቋም ያስፈለገበትን ምክንያት ሲጠቅስ ያስቀመጣቸው ሦስት ታሳቢዎች፤ ዛሬ በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ የተነሡትን የተቋሙ ሪፎርሜሽን መነሻዎችን የሚያጠናክሩ ነበሩ፡፡

አንደኛው፣ “የብሔራዊ መረጃና ደህንነት ተቋሙን በማጠናከር ሕገ መንግሥቱንና ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን ለመጠበቅ” ሲሆን፤ ሁለተኛው፣ “ሀገሪቱን የሰላም፣ የልማት የዴሞክራሲና የመልካም አስተዳደር ሥርዓት ግንባታ ለመደገፍ፤” እንዲሁም ሦስተኛው “ሀገራዊና ዓለም አቀፋዊ ሁኔታዎችን ያገናዘበ፣ ዘመናዊና ጠንካራ የመረጃና ደህንነት ተቋም መገንባት አስፈላጊ በመሆኑ ነው” ይላል፡፡

ከዚህ አንጻር ይህ ተቋም እያለ እንደሌለ ራሱን ከሚደብቅበት ስፍራ አውጥቶ ሕዝብ የሚያውቀው ተቋም እንዲሆን መደረጉ፣ “ከመንፈስነት ወደሥጋነት እንደመለወጥ ያለ ሽግግር ነው” ይላሉ አስተያየት ሰጪዎች፡፡

**የደህንነት አዲስ ፍልስፍናዎች**

የብሔራዊ ደህንነት አገልግሎት፣ ዳግም በኢህአዴግ ዘመን ለሁለተኛ ጊዜ በሌላ አዋጅ ሊደራጅ መሆኑን ባለፈው ነሐሴ 16 ቀን፣ 2010 መግለጫ የሰጡት ጄኔራል አደም ይፋ አድርገዋል፡፡ ይህ አዋጅ በቀደመው የ2005ቱ ማቋቋሚያ አዋጅ ያልተካተቱትን የደህንነት ሠራተኞች የፖለቲካ ፓርቲ አባልነትን የሚከለክሉ፤ እንዲሁም የተቋሙን ከአንድ ፓርቲ መጨቆኛ ንብረትነት የተላቀቀ የሕዝብ አገልጋይነት በግልጽ የሚያመላክቱ አንቀጾች እንደሚካተቱበትም አስታውቀዋል፡፡

ጄኔራሉ ይህ ተቋም በአዲስ መልክ የአሠራር ለውጥ አድርጎ ወደሥራ በገባባቸው ባለፉት ሦስት ወራት ያከናወናቸው ተግባራት ውጤታማ እንደነበሩ ተናግረዋል፡፡

ይህ ማለት ግን ለብሔራዊ ደህንነት ሲባል ቀድሞ ይከናወኑ የነበሩ የስለላ እና የክትትል ተግባራት እንደሚቀሩ አድርጎ የአገልግሎቱን ተግባር በተለየ የሰብዓዊ መብት ተሟጋች ፍልስፍና ላይ መመሥረት ተገቢ የማይሆንበት ምክንያት አለ፡፡ “በብሔራዊ ደህንነትና በሰብአዊ መብት መካከል የተሰመረው ቀጭን የልዩነት መስመር በንድፈ ሀሳብና በተግባር እንዴት ሊጣጣም ይችላል?” የሚለው ጥያቄ እንዳለ ሆኖ ለምሳሌም በሕገ መንግሥቱ ከተቀመጠው “የዜጎች ግላዊ ምስጢር የተጠበቀ ስለመሆኑ” የሚገልጸውን አንቀጽ “ለብሔራዊ ደህንነት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ” በሚለው ክፍተት ተጠቅሞ፤ ብሔራዊ ደህንነትን ከአደጋ ለማዳን ዜጎችን መሰለል ሊከሰት ይችላል፡፡ እንዲህ ዓይነት ክስተት የቡድን ደህንነትን ከግለሰብ መብት ማስቀደም ስለሚሆን፤ እንደአግባቡ ተቀባይነት ሊያገኝ የሚችልበት ሁኔታ አይጠፋም፡፡ ይህ ተግባር፣ በሰለጠኑና “የዴሞክራሲ ጥግ ላይ ናቸው” በሚባሉ እንደአሜሪካ ባሉ ሀገራት ጭምር ተግባራዊ እንደሚደረግ ማወቅ፤ ዜጎችን መሰለልን ተቀባይነት የሌለው የመብት ጥሰት አድርጎ ከመቁጠር ያድናል፡፡

ለምሳሌ አሜሪካ በአንድ ወቅት ከሽብር ጥቃት ጋር በተያያዘ፣ “የሕዝቡን ደህንነት ለመጠበቅ ነው” በሚል ምክንያት “ሆምላንድ ሴኩሪቲ” የሚባል አዲስ የደህንነት መዋቅር ፈጥራለች፡፡ በዚህም፣ የዜጎቿንና የወዳጆቿን የስልክና የደብዳቤ መልእክቶች ሳይቀር በመጥለፍና በመሰለል ሥራ ላይ ተጠምዳ ነበር፡፡ የአሜሪካ መንግሥት ይህንን ተግባሩን ይፋ ባያደርግም፤ ኤድዋርድ ስኖውደን የተባለ የሲአይኤ የቀድሞ ሠራተኛ ግን፤ ድርጊቱን አጋልጦ በኦባማ አስተዳደር ላይ ራስ ምታት ፈጥሮ ነበር፡፡ የአሜሪካ ዜጎች እያንዳንዱ ቤት ውስጥ የሚካሄደው ነገር በመንግሥት ዓይን ውስጥ መሆኑን ሲያውቁ፤ ድርጊቱን በከባድ ሁኔታ ተቃውመውታል፡፡ ያም ሆኖ ይህን መሰል ስለላ፤ ምናልባትም የዜጎችን ሕይወት አደጋ ላይ ለመጣልና በሚሠሩትና በሚያደርጉት ግላዊ ጉዳይ ላይ ክስ ለመመሥረት ሳይሆን፤ የሀገሪቱን ደህንነት ለመጠበቅ መሆኑን ማሳየት የሚቻልባቸው ማመሳከሪያዎችም አሉ፡፡ ነገር ግን የኢትዮጵያ ያለፈ ታሪክና ልምድ የሚያሳየን በዜጎች ላይ የሚካሄድ ስለላ ተሰላዮችን ወደ እስር ቤት ለማጎር መጣደፍን በውጤትነት ስለሚይዝ፤ የአሁኑ የብሔራዊ ደህንነት አገልግሎትም በዚህ ፍልስፍና ላይ ተጣብቆ የሚሠራ ከሆነ፤ ድርጊቱ ከሚገባው በላይ ከመብት ጥሰት ጋር ተያይዞ መነሣቱ አይቀሬ ነው፡፡

> **ማንም ዜጋ በመንግስቱ ላይ ግልጽ ተቃውሞ ሊያቀርብ ቀርቶ በስህተት እንኳን ክፉ ቃል መናገር እስር፣ አፈና እና ግርፊያ ከዚያም ሲብስ ግድያ ያስከትልበት ነበር። በዚህ ሳቢያ ማንኛውም ሰው ከሰዎች ጋር ሆኖ ቀርቶ ብቻውን እንኳን መንግስቱን የሚቀናቀን ክፉ ቃል ከአፉ እንዳይወጣ ይጠነቀቅ ነበር**

# ከኢህአዴግ ጉባኤ የሚጠበቁ ተስፋዎችና ቀጣይ እርምጃዎች ! ! !

ጠ/ሚኒስትር ዐቢይ ወደ ሥልጣን ከመጡ በኂላ ኢህአዴግ ለመጀመሪያ ጊዜ በቅርቡ ጠቅላላ ጉባኤውን (በያዝነው ወር) ያካሂዳል ተብሎ ይጠበቃል፡፡ “የመፍትሔው አካል ለመሆን በገዛ ፈቃዴ ሥልጣኔን ለቅቂያለሁ” ያሉት የቀድሞው ጠ/ሚኒስትር አቶ ኃ/ማርያም ደሳለኝ ሓላፊነቱን ለወጣቱ ጠቅላይ ሚኒስትር ካሸጋገሩ በኂላ፤ በሀገሪቱ ውስጥ የነበረው የኢህአዴግ የአምባገነንነት መንፈስ የተሰበረና የደበዘዘ ቢሆንም፣ ድርጅቱ አሁንም ከውስጣዊ ችግሩ ሙሉ በሙሉ መፅዳት አልቻለም፡፡

ጭቆና ከመቼውም ጊዜ በላይ ያንገፈገፋቸው ኢትዮጵያውያን የዘረኝነት ፖለቲካ ቅድሚያ አጀንዳው ሆኖ ለዘመናት የሰነበተውን “ኃይል አምላኪ” ሥርዓት፤ በከፍተኛ መሥዋዕትነት የሥልጣን ወንበሩን ሲያንገራግጩት፤ ከውስጥ ብቅ ያለው የለማ መገርሳ ቲም፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለዘመናት የጓጓለትን የአንድነት መንፈስ ዜጎች በብሔራቸው ሳይሆን፣ በዜግነታቸው ብቻ ወደሚከበሩበት፤ የተረጋጋ ሰላምና ሁሉን አሳታፊ የሆነ ኢኮኖሚያዊ መዋቅር ለመዘርጋት ደፋ ቀና ማለቱን የተያያዘው ከጅምሩ ቢሆንም፤ ለውጡን በማይደግፉ አካላት ከተለያየ አቅጣጫ የሚደርስበት ግፊትና ብጥበጣ መቋጫው መቼ እንደሆነ አይታወቅም፡፡

“ገገርዎቻችን” የነበሩት አካላት፣ እነሱ ሥልጣን ላይ እስከሌሉ ድረስ ይህቺ ሀገር እንደማትኖርና ሕዝቦቿም እንደሚበታተኑ በምሳሌነት ሲያቀርቧቸው፣ በሽብርተኛነትና ፍፁም ኢትዮጵያዊ ጠላት በሆነ መልኩ ሲገልፁ የኖሯቸው የፖለቲካ ድርጅቶች፣ የፖለቲካ ፓርቲ አመራሮችና የነፃነት ታጋዮች፤ በለውጡ ማግሥት ሀገራቸውን ለመታደግ የጦር መሣሪያቸውንና የልዩነት አጀንዳዎቻቸውን አሽቀንጥረው በመጣል፤ አስፈላጊውን መሥዋዕትነት ለሕዝባቸው ለመክፈል ሀገራቸውን ከጥፋተኞች ለመታደግ እናት ምድራቸው መግባት ከጀመሩ ሰነባብተዋል፡፡

በአንፃሩ፣ የተሳሳተ ፕሮፓጋንዳ ሲነዙ የኖሩት፣ ሕዝብን በጠመንጃ አፈ ሙዝ አፉን ለጉመው አንገቱን ረግጠው ሲገዙት የነበሩ አስተዳዳሪዎች፤ ጠ/ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ በሓላፊነት ሲሾሙ በተለያየ መንገድ ተቃውሟቸውን ከመግለፅና “ለሕግ የበላይነት አልገዛም” ከማለት በተጨማሪ፤ በተለያዩ ክልሎች ግጭቶች እንዲነሡ በማድረግ፣ ሀገሪቱ እንዳትረጋጋና ከፍተኛ ትርምስ ውስጥ ለመክተት ጠንካራ ሙከራ አድርገዋል፡፡ ይሄ ሂደት ደግሞ አምባገነኑ ሥርዓት በሥልጣን ላይ በነበረበት ጊዜ ሲያስተጋባ የኖረውን ሌሎችን በሀገር በታኝነት የመወንጀል እሳቤ በግልባጩ ያስመለክተናል፡፡

ጠ/ሚኒስትር ዐቢይ፣ ኢትዮጵያን ወደ ቀድሞ ገናና ክብሯ ለመመለስ በሚጣጣሩበት ወቅት፤ በተለያዩ ክልሎች ከአሰልቺ የጭቆና ዘመናት በኂላ ያገኘነውን የዴሞክራሲ እስትንፋስ ሊነጥቁን የሚሞክሩ ኃይሎች ባለ በሌለ ጉልበታቸው ደፋ ቀና በሚሉበት ሰዓት፣ ኢህአዴግ በድርጅታዊ ስብሰባው ተጠምዷል፡፡ የአሁኑ የድርጅቱ ስብሰባ፣ ምናልባትም ጠ/ሚኒስትር ዐቢይ ወደ ሥልጣን ከመጡ በኂላ፤ በድርጅቶች ውስጥ ያለውን መከፋፈልና በተለይም የህወሓት ማፈንገጥ፣ “ቀጣይ ዕጣ ፈንታውንና የወደፊት ራዕዩን ጭምር አመላካች ነው” የሚል ግምት በመያዙ፤ በብዙዎች ዘንድ በጉጉት እየተጠበቀ ይገኛል፡፡

በድርጅታዊ አሰላለፍ ረገድ፣ ግንባር ፈጥረው የወጡት ኦህዴድና ብአዴን ለጠ/ሚኒስትር ዐቢይ መንግሥት፣ “የተለመደ ድጋፋቸውንና የለውጥ አጀንዳቸውን አጠናክረው ይቀርባሉ” የሚል ዕምነት አለ፡፡ እነ ሽፈራው ሽጉጤን ገፍቶ በአዲስ አመራር የተዋቀረው ደኢህዴንም በሙሉ ድጋፍ የለውጡን አብዮት ያጠናክራል ተብሎ ይጠበቃል፡፡ እነዚህ ድርጅቶች በኢህአዴግ ዓመታዊ ጠቅላላ ጉባኤ ላይ ባለፉት አራት ወራት በክልሎቻቸው ስለተፈጠሩ ችግሮችና መንስኤዎች፤ በቀጣይነት እንዲህ ዓይነት ብሔር ተኮር ግጭቶችና ሁከቶች እንዳይቀሰቀሱ፣ የተስፋ ብርሃኑ እንዲለመልም ከምንጊዜውም በላይ ትኩረት ሰጥተው መሥራት ይኖርባቸዋል፡፡ እግረ መንገድ በጠ/ሚኒስትሩ የመደመር መርህ ውስጥ ያልተካተቱ፤ በቅኝትና እሳቤ የአምባገነኑ ሥርዓት ደጋፊና አስፈፃሚ የሆኑ ግለሰቦችን በማጥራቱ ረገድም ሊሠራበት እንደሚገባ ሳንጠቁም አናልፍም፡፡

የለውጡ ዋነኛ ተፃራሪ እንደሆነ የሚነገርለት ህወሓት፣ በዚህ ድርጅታዊ ጉባኤ ላይ ይዞት የሚመጣው ሀሳብ ገንቢና ሀገራዊ አንድነትን የተመረኮዘ ሊሆን እንደሚገባ መረሳት የለበትም፡፡ ፅንፍ የያዘ የዘረኝነት መንፈስ አሁንም ከዳር ዳር እንዳስተጋባ ከማሰብ ባሻገር፣ ያጡትን አምባገነናዊ አገዛዝ ለማስመለስ የሚጥሩና ለውጡን የሚሸሹት ኃይሎች፤ ስለሚወክሉት የትግራይ ሕዝብም ቢሆን፣ በፅኑ ማሰብ ይገባቸዋል፡፡ የመበታተንና “እኛ ከሌለን ሀገሪቷ አትኖርም” የሚል የትም የማያደርስ፣ ጊዜው ያለፈበት ፕሮፓጋንዳ ከማስተጋባት ታቅበው፤ ሀገሪቱ በጀመረችው የዴሞክራሲና የአንድነት ጉዞ ላይ ታሪካዊ አሻራቸውን የሚያስቀምጡበት ዕድል እንዳለ በአጽንኦት ሊያስቡበት ይገባል፡፡

በመጨረሻም ሰሞነኛው የኢህአዴግ ጉባኤ የሚያበስረን መልካም ዜና እንዲኖርና የድርጅቶቹ ዕሳቤና መንፈስ ወደ አንድ አቅጣጫ እንዲያዘም፤ እንደ ዜጋ ከልብ እየተመኘን፣ ከኢህአዴግ ጉባኤ የሚጠበቁ ተስፋዎችና የተጀመረውን የለውጥ ጉዞ አጠናክሮ ለመቀጠል ሊወሰዱ የሚገባቸው ድርጅቱን ከፀረ ለውጥ ኃይሎች የማጥራት እርምጃ፣ በፍጥነት መከናወን እንደሚገባው እናሳስባለን፡፡


**ግዮን መጽሔት**

**ኢትዮ ሐበሻ ኅትመትና**

**ማስታወቂያ ኃ/የተ/የግ/ማኅበር**

**በየሳምንቱ ለኅትመት የምትበቃ መጽሔት**

**ማኔጂንግ ዳይሬክተር**

ፍቃዱ ማ/ወርቅ

**ማኔጂንግ ኤዲተር**

ዘኤልያስ ወልደ ሚካኤል

**ዋና አዘጋጅ**

ሮቤል ምትኩ

አድራሻ፡- የካ ክ/ከተማ ወረዳ 2 የቤት ቁጥር 475

**ተባባሪ ዘጋቢያችን**

ቶማስ አያሌው(**ከአሜሪካ**)

**አዘጋጅ**

ብሩክ መኮንን

**አምደኞች**

ፍቅሩ ኪዳኔ (**ከሲውዘርላንድ**)

ዶ/ር ዘሪሁን ሙላቱ

መስፍን ጌታቸው

አስማማው ኃ/ጊዮርጊስ(**ከአሜሪካ**)

ተስፉ (ኢትዮጵያ) አልታሰብ

ታምራት መርጊያ

ኃይሉ አሰለፍ ገብሬ

**ጸሐፊ**

ሠላም ግርማ

**ክርኤቲቭ ዲዛይን**

ሀብታሙ መኮንን

**የዝግጅት ክፍሉ አድራሻ**

አራዳ ክ/ከ ወረዳ 09 የቤት ቁጥር 552/1

አምባቸው ህንፃ 5ተኛ ፎቅ ቢሮ ቁ. 501

ፖስታ ቁ. 676 ኮድ 1029

ስልክ ፡ +251 911 227661

+251 912 165606

+251 118 12 2333

ኢ-ሜይል፡

enqu2013@ gmail.com

Facebook Gihon-meg Fekadu

**አታሚ**

ቴዎድሮስ ገብሩ ማተሚያ ቤት ፤

አራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 10 የቤ.ቁ. 066/ሀ



በዚህ መጽሔት ላይ የሚወጡ ጽሑፎች በሙሉ ማተሚያ ቤቱን አይመለከትም



ጋዜጠኛ ተመስገን ደሳለኝ

*ከጋዜጠኛ ተመስገን ደሳለኝ ጋር በቁጥር 18 ዕትማችን በአውሮፓ ጉዞው ስለነበረው ቆይታና ስለመከላከያ ሠራዊት ሰፊ ትንታኔ ማቅረባችን ይታወሳል፤ ቀጣዩንና የመጨረሻውን ክፍል በዚህ ዕትም እንደሚከተለው አቅርበነዋል፡፡*

# "ብአዴን በትግርኛ እያሰበ በአማርኛ የሚያስተዳድር የህወሓት ክንፍ ነበር"

## ጋዜጠኛ ተመስገን ደሳለኝ

**ግዮን፡- ስለ ጠ/ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ካነሣን፣ እሳቸው ወደ ሥልጣን ከመጡ በኋላ ባሉት አራት ወራት የታየውን ለውጥና እንቅስቃሴ እንዴት አየኸው?**

**ተመስገን፡-** መምታታት የሌለባቸውና ሁሉም ሰው ማወቅ ያለበት ሁለት ነገር አለ፤ እነ ጠ/ሚኒስትር ዐቢይ ለውጥ አላመጡም፤ ለውጥ ሊያመጡ የሚችሉበትን ዕድል ግን ይዘዋል፡፡ 'ለውጥ እናመጣለን' ነው ያሉን እንጂ፣ እስካሁን ድረስ ለውጡ አልመጣም፡፡ 'ለውጥ ይመጣል' ብሎ ተስፋ ማድረግና 'ለውጥ መጥቷል' ብሎ በር ዘግቶ መቀመጥ አንድ አይደለም፤ ዋጋ ያስከፍለናል፡፡ ኢትዮጵያ እጅግ እጅግ በጣም ወሳኝ የሚባል ዕድል አምልጧታል፤ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የፋኖን አስተሳሰብ የምንቀብርበት ዕድሎች አምልጠውናል፡፡ የመጀመሪያው ዕድል በ1966 አፄ ኃይለ ሥላሴ ከሥልጣን ሲወርዱ ያኔ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መገንባት የምንችልበት ዕድል ነበረን፡፡ በወቅቱ በነበሩ ድርጅቶች ተክለፍላፊነትና በእነ ኮ/ል መንግሥቱ ሥልጣን ወዳድነት ምክንያት የተገኘው ዕድል መከነ፡፡

**ሁለተኛ፡-** 'ነፃ እናወጣለን' ብሎ የመጣው የወያኔ ኃይል፤ 1983 ዓ.ም ላይ ሁሉንም ፓርቲዎች ያሳተፈ ነፃና ግልፅ የሆነ ዴሞክራሲያዊ ምርጫ እንዲካሄድ ቢፈቅድ ኖሮ፣ ትልቅ ዕድል ነበረ ብዬ አስባለሁ፡፡ እሱንም እነ መለስ ለድብቅ ሴራቸው ነው የተጠቀሙበት፡፡ በነገራችን ላይ እነሱ ጫካ የገቡት እኔን ወይም አንተን ነፃ ሊያወጡ ሳይሆን፤ ሀገሪቷን ወደብ አልባ ለማድረግ፣ ኤርትራን ለማስገንጠል፣ በዜግነታችን ሳይሆን በብሔራችን እንድናስብና በብሔራችን ብቻ የተነሣ ከአንዱ ክልል ወደ አንዱ ለመሄድ ፈንጂ ላይ የመረማማድ ያህል እንዲሆን ለማድረግ፤ ኢትዮጵያውያን በመከፋፈልና በጥርጣሬ እንዲኖሩ፣ የኢትዮጵያ ሐብት ፍትሐዊ ባልሆነ አካሄድ በጥቂት ሰዎች እጅ እንዲገባ እና ለመሳሰሉት ጉዳዮች ታግለው ነው ውጤታማ የሆኑት፡፡ በሃያ ሠባት ዓመት ውስጥም ያተረፍነው ይሄንኑ ነው፡፡ ለዚህም ነው እጃቸው የገባውን ዕድልና የለውጥ ካርታ ያመከኑት፡፡

**ሦስተኛው፡-** አሁንም ከጥፋቱ ያልተማረው ኢህአዴግ ቢወቀስም፣ በተወሰነ ደረጃ ሓላፊነቱን የሚወስዱት የ1997 ዓ.ም ምርጫ አሸናፊዎች ቅንጅትና ሕብረት ናቸው፡፡ በድጋሚ ኢትዮጵያ ውስጥ የተገኘውን የለውጥ ዕድል ለማበላሸት ኢህአዴግ ትልቁን ድርሻ በሰዓቱ ቢይዝም፣ ቅንጅትና ሕብረት ለስህተቱ ዐሥር ዐሥር ፐርሰንት የሚሆን ድርሻ እንደነበራቸው መካድ አይቻልም፡፡ ቅንጅት እርስ በእርሱ በመከፋፈሉ የቀለም አብዮት አካሂዶ መንግሥትን ማስወረድ የሚችልበትን ዕድል አምክኗል፡፡

አራተኛው ዕድል አሁን በእነ ጠ/ሚኒስትር ዐቢይ እጅ ላይ ወድቋል፡፡ ሕዝብ እነ ጠ/ሚኒስትር ዐቢይን አደባባይ ወጥቶ እየደገፋቸው ያለው፣ ለውጥ ስላመጡ አይደለም፤ 'ለውጥ ያመጣሉ' ብለን ተስፋ ስላደረግንባቸው ነው፡፡ ለውጥ ሊመጣ የሚችልበት የታሪክ ምዕራፍ ላይ ነው ያለነው፡፡ እዚያ የታሪክ ምዕራፍ ላይ ቆሞ ኮምፓሱን ማስተካከል ያለበት ቤተ መንግሥቱን የያዘው ኃይል ነው ብዬ አምናለሁ፡፡

**ግዮን፡- አሁን በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች የተከሰቱት ብጥብጦች እንዴት ነው መቆም ያለባቸው?**

**ተመስገን፡-** በእኔ እምነት ብጥብጡ ትክክል ነው ብየ ነው የማስበው፡፡

**ግዮን፡- ለምን?**

**ተመስገን፡-** ይሄንን ብጥብጥ በዋናነት የሚዳኘው፣ የፈቀደው ወይም ስፖንሰር ያደረገው ሕገ መንግሥቱ ነው፡፡ ይሄ ሕገ መንግሥት እስካለ ድረስ አንተ ኦሮሞ፣ አንተ አማራ፣ አንተ ትግሬ፣ አንተ አፋር ብሎ መባደን ትክክል ነው፡፡ ምክንያቱም ሕገ መንግሥቱ ኢትዮጵያውያንን እንደ ዜጋ ሳይሆን እንደ ብሔር ነው እውቅና የሰጣቸው፡፡ 'አማራ ክልል የአማራ ነው፤ ኦሮሚያ ክልል የኦሮሞ ነው' ብሏል፡፡ ስለዚህ 'ውጣ' ▶

ስትባል አካሄዱ ሕጋዊ ነው ማለት ነው:: ከዚህ በመነሣት ብጥብጡ ሕጋዊ ሲሆን፣ ስህተተኛው ሕገ መንግሥቱ ነው::

የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ በማወጅ፣ ሠራዊትህን ልከህ፣ ከአንድ አካባቢ ሰዎችን አፍስህ በመያዝ ብጥብጡን ማብረድ ትችላለህ፤ ግን ይሄ አካሄድ ዘላቂነት የለውም:: እነዚያ ሰዎች ሲፈቱ ደግሞ ወደ አመፅኝነት ይሄዳሉ:: ይሄ እንዳይሆን ከተፈለገ ሕገ መንግሥቱ ሊሻሻል ይገባዋል::

**ግዮን፡- ጠ/ሚኒስትሩ ወደ ሥልጣን ከመጡ ገና አራት ወር እንደሆናቸው ሲታሰብ፣ ሕገ መንግሥቱን ለማሻሻል ጊዜ መስጠት የለበትም? 'ይህን የሚያደርጉት ያኮረፉና የተገፉ ኃይሎች ናቸው' የሚባለውስ?**

**ተመስገን፡-** እሱ ስህተት ነው:: እኔ አሁንም፣ 'ይህ ሕገ መንግሥት ሊሻሻል ይገባዋል' አልሁ እንጂ 'እስካሁን ለምን አልተቀየረም?' ብዬ እየወቀስኩ አይደለም:: እስካልተሻሻለ ድረስ ሊቀጥል ይችላል:: መታወስ ያለበትን ግን፣ ያኮረፈው ቡድን አይደለም 'ከክልሌ ውጣልኝ' የሚል ሽብር እየፈጠረ ያለው፤ ምናልባት ከዚህ ቀደም ሥልጣን ላይ የነበረው የህወሓት ደጋፊ ከየክልሉ 'ውጣልኝ' አይባልም ነበር፤ አሁን አዲስ የሆነው ነገር የህወሓት ደጋፊም፣ ትግርኛ ተናጋሪውም 'ውጣ' መባሉ ነው::

ባለፉት 27 ዓመታት አማርኛ ተናጋሪው ከጉራ ፈርዳ፣ ከቤንች ማጂ ዞንም ሆነ ከየትኛውም አካባቢ 'ውጡ' እየተባለ በአንገቱ ሳይሆን በማጅራቱ ሲታረድ ነበር፤ ይሄ በሁለትና ሦስት ወር የመጣ አይደለም:: አሁን አዲስ የሆነብን አይነኬ የነበረው ቡድን ስለተነካ ብቻ ነው::

ከቤንች ማጂ ዞን በሺህዎች የሚቆጠሩ የአማራ ተወላጆች ሀብት ንብረታቸው ተዘርፎ፣ እየተደበደቡ ተባርረው ባህር ዳር ላይ ሲፈሱ፣ መለስ ዜናዊ ፓርላማ ላይ 'ደን ቆራጮች ናቸው' ብሎ ነው የተሳለቀባቸው፤ ይሄ እንዴት ይረሳል? ከአማራ ክልል ውጪ ከሆኑ ከየትኛውም አካባቢዎች ላለፉት 27 ዓመታት አማራ ሲፈናቀል ነበር፤ አሁን ማፈናቀሉ አድጎ ከሶማልያ ኦሮሞ ተፈናቅሏል፤ ከደቡብ ሁሉም ብሔር ተፈናቅሏል፤ ከኦሮሚያ ደቡብ ተፈናቅሏል፣ አማራ ተፈናቅሏል፣ ትግሬ ተፈናቅሏል:: በፊት በአንድ ብሔር ላይ ብቻ የሚደረግ ድርጊት ስለ ነበር ብዙ አልተጮኸለትም፤ 'ሀገር እየፈረሰ ነው' ተብሎ አልታሰበም ነበር:: አሁን ሚዲያ የያዙ፣ ገንዘብ ያላቸው ሰዎች የእነሱ ብሔር መነካት ሲጀምር፤ መጮህ ጀመሩ እንጂ፣ ችግሩ ወያኔ ሥልጣን በያዘ ማግሥት ነው ሥር የሰደደው:: ጠ/ሚኒስትር ዐቢይ ሥልጣን ላይ ስለወጡ የተፈጠረ አዲስ ነገር አይደለም::

**ግዮን፡- ጠ/ሚኒስትር ዐቢይ ወደ ሥልጣን ከመጡ በኋላ፣ በአማራ ሁሉም ከተሞችና በአዲስ አበባ ትልቅ የድጋፍ ሰልፍ ሲካሄድ፤ በኦሮሚያ በጣት ከሚቆጠሩ ከተሞች ውጪ ተመሳሳይ ነገር አልተደረገም፤ ትግራይ ላይ የታየውን ሰላማዊ ሰልፍና ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በመላ ሀገሪቱ ንፁሕ የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ በስፋት መውለብለቡን እንዴት አየኸው?**

**ተመስገን፡-** አንድ መታወቅ ያለበት ከትግራይ ውጪ በሁሉም የኢትዮጵያ ክልል ሰልፍ ተካሂዷል፤ ምናልባት አነስተኛ ሰልፍ የተካሄደው በኦሮሚያ ብቻ ነው:: በአፋር፣ በደቡብ በርካታ ትንንሽ ከተሞችን ጨምሮ፤ በሁሉም ቦታ በጅግጅጋ በደገሀቡር የድጋፍ ሰልፍ ተካሂዷል:: ያልተካሄደው በኦሮሚያ ብቻ ነበር::

ኢትዮጵያ ከዚህ ቀደም ሁለት ባህርይ ነበራት ህወሓት ይገድላል፤ ሌላው ሕዝብ ይሞታል:: ህወሓት 'የትግራይ ሕዝብ ነፃ አውጪ ድርጅት ነኝ' ብሎ ነው የትጥቅ ትግል የጀመረው፤ ከሞላ ጎደል ማኅበራዊ ጉድኝቱ የትግራይ ሕዝብ ነው፤ አሁንም በማኅበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ቦታዎች እንደምናየው፣ ከዚህ ቀደም ህወሓት ከሥልጣኑ፤ ከጨቋኝነቱና ከበዳይነቱ ነው የተባረረው እንጂ፤ ሌላ ምንም የደረሰበት ነገር የለም::

በግልፅ እንዳየነው፣ ከህወሓት አንድም እስር ቤት የገባ ሰው የለም:: 'ለምን ከዚህ በፊት እንደሚደረገው ሰዎችን እስር ቤት ከትቼ አልገርፍም? አላሰቃይም? ለምን የሀገሪቷን ሀብት እንደለመድሁት ለብቻዬ አልዘርፍም? ሀገሪቱ በዓለም አቀፍ ደረጃ ባሏት ኤምባሲዎች በሙሉ ለምን የራሴን ቦታ ይዤ አልቀጥልም? ለምን የንግድ ውድድሩን ወደ ራሴ ደጋፊዎች ባጋደለ መልኩ አላስሄድም?' የሚል ተቃውሞ ነው በህወሓት በኩል ትግራይ ላይ ሰልፍ የተደረገው::

ያ ሰልፍ ምናልባት መላውን የትግራይ ሕዝብ ላይወክል ይችላል፤ ህወሓት፣ ጉልበቱ ከፌዴራል መንግሥቱ ተመታ እንጂ፤ በትግራይ ላይ አሁንም ጉልበተኛ ነው:: ስለዚህም በተለመደው መንገድ እነደብረ ጽዮን የትግራይን ሕዝብ አስገድደው አደባባይ አስወጥተውት ሊሆን የሚችልበትም ዕድል አለ::

**ግዮን፡- ኢህአዴግ ባለፉት 27 ዓመታት የብሔርና የዘረኝነት ሥርዓት ሲያስፋፋ ቆይቷል፤ የተሻለ ለውጥ እየታየ ነው በሚባልበት በአሁኑ ወቅት እየተቋቋሙም ሆነ በይፋ እየተንቀሳቀሱ የሚገኙት ብሔር ተኮር የፖለቲካ ፓርቲዎች ናቸው፤ ይሄ አካሄድ ይጠቅማል?**

**ተመስገን፡-** በእኔ እምነት አይጠቅምም:: የብሔር ፖለቲካ ከመጣ በኋላ ከአንድነት ይልቅ ልዩነትን በከፍተኛ ሁኔተ አስፋፍቶብናል፤ በኢህአዴግ ዘመን ያለፍንበትና አሁንም እያለፍንበት ያለው ለእኛ አልበጀንም:: በነገራችን ላይ በጠቀስኸው ጊዜ ውስጥ ከ'አብን' በቀር በብሔር የተደራጀ አዲስ ድርጅት መኖሩን አልሰማሁም:: ይህ ግን ሊደንቀን አይገባም፤ ምክንያቱም አሁንም ሀገሪቷን እየመሩ ያሉ ድርጅቶች ብሔር ተኮር ናቸው:: የብሔር ድርጅቶች አቃፊና ደጋፊ የሆነው ሥነ መንግሥት አሁንም በሥራ ላይ ነው:: ይሄ እስካልተቀየረ ድረስ የብሔር ድርጅቶች መብዛታቸው አይቀርም::

በፌዴራሊዝም ላይ ጥናት ያደረጉ ምሁራን፣ 'ይሄ የብሔር ፖለቲካ ሄዶ ሄዶ ኢትዮጵያን ከመበታተን ባለፈ አንድነትን አያጠናክርም' እያሉ ደጋግመው ሲመክሩን ነበር፤ አሁን በኢህአዴግ ውስጥ የተፈጠረውን የሥልጣን መንገራገጭ ተከትሎ የምናየውም የትንቢያቸውን እውነትነት ነው:: የወያኔ የብሔር ፌዴራሊዝም የከሸፈው ዛሬ አይደለም፤ በተተገበረ በማግሥቱ ነው:: ነገር ግን ባለፉት ሃያ ሠባት ዓመታት ሊቀጥል የቻለው በኃይል እመቃና በጉልብት የፖለቲካ አገዛዝ ተደግፎ ነው ብዬ አምናለሁ::

**ግዮን፡- በኢትዮጵያ ውስጥ የተለያዩ ታዋቂ ግለሰቦችና የፖለቲካ ፓርቲ አመራሮች፣ 'የሽግግር መንግሥት መመሥረት አለበት' ይላሉ፤ ይሄ አካሄድ ተገቢ ነው?**

**ተመስገን፡-** የሽግግር መንግሥት ጥያቄ ስናነሣ፣ ነገሮችን ከተለያዩ አቅጣጫዎች መመርመር አለብን:: አንደኛ፣ ኢህአዴግን እንደ ድርጅት ካየነው፣ 'ጠንካራ ነው' ልንለው አንችልም:: ወቅታዊ ሁኔታውን ገምግሞ፣ የሕዝቡን ፍላጎት ተረድቶ፣ 'ኢትዮጵያ ላይ ሥልጣን ይዘን በቆየንባቸው ዓመታት ተመስግነናል-ተወቅሰናል፤ አልምተናል-አጥፍተናል፤ ሠርተናል-አፍርሰናል፤ አድነናል-ገድለናል፤ አሁን ግን ይበቃናል' ብሎ በመግባባት አንድ ውሳኔ ላይ የሚደርስበት ቁመና የለውም:: ድርጅቱ ተከፋፍሏል:: መሬት የረገጠው ሐቅ እንደሚነግረንም፤ ለኦህዴድ ከህወሓት ይልቅ ኦነግ ቅርቡ መሆኑን ነው፤ ብአዴንም ትግራይን ተሻግሮ፣ ኤርትራ ድረስ በመሄድ፤ የአዴኃንን ዝምድና ሲያጠብቅ እየተስተዋለ ነው:: ስለዚህም የሽግግር መንግሥት ቢፈልጉ እንኳን አራቱ እናት ድርጅቶች ተግባብተውና ተማምነው እንደ ኢህአዴግ ማወጅ የሚችሉበት ቁመና ላይ አይደሉም::

ሁለተኛ፣ ብዙ ጊዜ የሽግግር መንግሥት የሚታወጀው ማዕከላዊ መንግሥቱን የያዘው ኃይል ሲደክምና ሊወድቅ ሲደርስ፤ ሀገርና ሕዝብን ካልታሰበ ጥፋትና የእርስ በእርስ እልቂት ለመታደግ ነው:: በ1983 ዓ.ም አካባቢ ደርግ ፈርሶ፣ ሻዕቢያና ወያኔ ሥልጣን መያዛቸው አይቀሬ እንደሆነ ሲታወቅ፤ ለንደን ላይ ድርድር ተካሂዶ ነበር:: እንዲያውም ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማርያምን የመሰሉ አርቆ አሳቢ፣ ሁሉን አሳታፊ የሽግግሌ መንግሥት እንዲቋቋም መክረው ነበር፤ ግና ኢሳያስ አፈወርቂ ለግንጠላ፣ መለስ እና ጓደኞቹ ለፈረቃ ጭቆናና ዘረፋ የታገሉ በመሆኑ፤ ሐሳቡን ውድቅ አድርገውታል::

በአናቱም የዛሬውን የኢህአዴግ ዋነኛ መሪዎች ቅቡልነት ካየነው፣ በ1997 ዓ.ም እነ ኢንጂነር ኃይሉ ሻውል፣ ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማርያም፣ ፕ/ር ብርሃኑ ነጋ፣

የድህነትና የጭቆናው ምክንያት እንዳለ ሆኖ፤ ኢትዮጵያ ውስጥ ጠንካራ የፖለቲካ ፓርቲ እንዳይወጣ ኢህአዴግ በአፋኝነት፣ የተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎች በስግብግብነት እና በግል ዝና ላይ ማተኮራቸው፤ ሕዝቡ ደግሞ ዳተኛ መሆኑ ዋነኛ ችግሮች ናቸው ብዬ አስባለሁ

ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳና ሌሎች ጓዶቻቸው ከነበራቸው ቅቡልነት ጋር አይተናነስም:: ስለዚህም እነጠ/ሚ ዐቢይ የሽግግር መንግሥት እንዲመሠርቱ የሚገደዱበት አጣብቂኝ ውስጥ አይደሉም ማለት ነው:: ጥያቄው፣ 'ለሀገራችን ትንሣኤ ሲሉ በፍላጎታቸው ቢያደርጉት ጥሩ ነው' የሚል ከሆነ እስማማለሁ:: ይህንን እንዳልጠብቅ ደግሞ ጠ/ሚኒስትሩ ራሳቸው በአደባባይ፣ 'የሽግግር መንግሥት የሚባል ነገርን እንዳታስቡት' ብለውናል:: ለዚህም ነው ጥያቄያችንን በሚሆን ነገር ላይ እናድርገው የምለው::

**ግዮን፡- የሽግግር መንግሥት ካልተቋቋመ፤ ምርጫ ቦርድ፣ የፀጥታ ኃይሎችና ሌሎች ነፃ ተቋማትና የሲቪክ ማህበራትን ከፓርቲያዊ አሠራር ነፃ በሆነ ገለልተኛ ሁኔታ እንዴት ማቋቋም ይቻላል?**

**ተመስገን፡-** ጠ/ሚኒስትር ዐቢይ አህመድ በይፋ 'እኔ አሸጋግራችኋለሁ' ብለውናል:: እኔ አሸጋግራችኋለሁ ሲሉን ግን እንዴት እንደሚያሸጋግሩን፣ የትኞቹን ተቋማት ነፃ አድርገው እንደሚያደራጁ አልነገሩንም:: ምንአልባት ወደተፈለገው ሽግግር እንዴት እንደሚወስዱን ፍኖተ ካርታ እያዘጋጁ ነው ብዬ አስባለሁ:: መቼም በለመድነው ምርጫ ቦርድ፣ በለመድነው ፍርድ ቤት፣ በለመድናቸው ተቋማት 'አሸጋግራችኋለሁ' አይሉንም::

የሆነው ሆኖ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ወደ ሽግግሩና ወደ ለውጥ ሂደቱ ሊወስዱን የምራቸውን ከቆረጡ፤ ሦስት ወሳኝ ነገሮች መሟላት ይኖርባቸዋል:: የመጀመሪያውና ዋነኛው ምርጫ ቦርድ፣ የፍትሕ ተቋማት፣ ዕንባ ጠባቂ፣ የሰብዓዊ መብት ኮሚሽን እና የመንግሥት ሚዲያዎችን የመሳሰሉ ተቋማት ፍፁም ከፖለቲካ ወገንተኝነት ነፃ በሆነ መንገድ እንዲዋቀሩና እንዲሠሩ ማድረግ ሲሆን፤ ሁለተኛው በሁሉም ዘርፍ የተሰማሩ የሲቪክ እና የሃይማኖት ተቋማት ላይ ያለውን የመንግሥት ጣልቃ ገብነት ማስቆም ነው:: ሦስተኛው የታጠቀው ኃይል ነው፤ ደህንነቱ፣ መከላከያው፣ የፌዴራልና የክልል ፖሊስ፣ ልዩ ኃይልና ሚሊሺያዎች ከፖለቲካ ነፃ በሆነና ተጠያቂነት ባለው መንገድ እንዲሠሩ መደረግ አለባቸው። እነዚህ ሁኔታዎች ከተሟሉ ጠ/ሚኒስትር ዐቢይ እንዳሉት የማሸጋገር ሂደቱ ይሳካላቸዋል ብዬ አስባለሁ::

ሌላው እዚህ ላይ መነሳት ያለበት ጉዳይ፣ 'የሽግግር መንግሥት አያስፈልግም' ከተባለ፤ መንግሥት 'ራሴ አመጣዋለሁ' ያለውን የለውጥ ሂደት የሚቆጣጠር ገለልተኛ የሆነ የሽግግር ካውንስል የግድ መቋቋም ይኖርበታል:: ስለዚህም ከሀገር ሽማግሌዎች፣ ከምሑራን፣ ከአክቲቪስቶች፣ ከልሂቃን፣ ከሲቪክና ከሃይማኖት ተቋማት፤ ሕዝብ ሊያምናቸው የሚችል ሰዎች ተመርጠው የሽግግር ካውንስል መቋቋም ይኖርበታል:: ይህ የሚሆነው ግን እንደ ከዚህ ቀደሙ ለይስሙላ ይደረግ እንደነበረው አይነት የሥርዓቱን ደጋፊዎች አሰባስቦ በማደራጀት አይደለም፤ የእውነት መድረኩ ለሁሉም ክፍት ሆኖ፣ በየቀበሌው ውይይት ተካሄዶ፣ ሕዝብ የሚያምንባቸው ሰዎች ተመርጠው የሽግግር ካውንስል መመሥረት አለበት:: የካውንስሉ ሥልጣን የማሸጋገር ፖሊሲውን መተግበር ሳይሆን፣ እነ ጠ/ሚ ዐቢይ 'አለኝ' በሚሉት ፍኖተ ካርታ ልክ እየሠሩ ነው ወይስ አይደለም? ብሎ በመቆጣጠርና በመከታተል ለሕዝብ ይፋ ማድረግ ላይ የተገደበ ቢሆን ጥሩ ነው::

**ግዮን፡- ትግራይ ላይ ከህወሓትና አረና በተጨማሪ በቅርቡ ደግሞ አረጋዊ በርሄና**



*ጋዜጠኛ ተመስገን ደሳለኝ*

**ግደይ ዘርዓ ጽዮንን የመሳሰሉ ፖለቲከኞች የመጡለት ከመሆኑ አኳያ፤ የትግራይ ፖለቲካ በምን መልኩ የሚሄድ ይመስልሃል?**

**ተመስገን፡-** ከወቅታዊው የድርጅቱ አቋም አኳያ ከተነሣን አረናን የህወሓት ተቃዋሚ ፓርቲ አድርጎ መውሰድ በጣም ይቸግራል:: አረናን ሙሉ ለሙሉ ህወሓት ነው ባትለው እንኳን፣ ሊቀ መንበሩን ጨምሮ አመራሮች አሁን እየታየ ያለውን ለውጥ በማኅበራዊ ሚዲያ በከፈቱት የፕሮፓጋንዳ ዘመቻ ለማደናቀፍ ሲጥሩና ደፋ ቀና ሲሉ እየታዘብን ነው:: ድርጅቱም እንደ ድርጅት ለውጡን በተመለከተ ግልፅ አቋም ባለመያዙ፤ አረና አኩራፊ እንጂ እውነተኛ ተቃዋሚ ፓርቲ ነው ለማለት ይቸግራል::

አረጋዊ በርሄና ግደይ ዘርዓ ጽዮንም ቢሆኑ የእነ ስብሐት ነጋና አባይ ፀሀዬን ያህል አርጅተዋል፤ ዕድሜያቸው በጣም ገፍቷል፤ ህወሓት መመራት ያለበት እንደ ኦህዴድ፣ ብአዴንና፣ ደኢህዴን በወጣቶችና በአዲሱ ትውልድ ነው:: ነገር ግን ህወሓት በአሮጌው አስተሳሰቡ ባለፈበት የብሉይ ትውልድ ፈላጭ ቆራጭነት ህልም ውስጥ እየተዝናና ያለ ይመስለኛል:: እነ አባይ ፀሃዬን አረጋውያን ካልናቸው እነ አረጋዊ በርሄን ደግሞ የኦሪት ትውልድ ነው የምንላቸው፤ በዘመን ዕይታ ውስጥ ስናስቀምጣቸው፤ ያው በጫካው መንገድ ላይ ከመቅረታቸው አኳያ ማለቴ ነው። ስለዚህ ህወሓት የውስጥ ተሐድሶ አካሂዶ ከጥላቻ ነፃ በሆኑ፣ ከዘረኛነት አስተሳሰብ በወጡ፣ ያለፈውን የህወሓትን ስግብግብነትና ጠቅላይነት የሚፀየፉ ወጣት አመራሮች ተተክተውበት የትግራይን ሕዝብ ጥቅም ከዕድሜ አቻዎቻቸው ከእነ ጠ/ሚኒስትር ዐቢይ ጋር ተጋፍተውና ተከራክረው ማስከበር አለባቸው ብዬ እመክራለሁ::

**ግዮን፡- ከዚህ ቀደም፣ "ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ተፎካካሪ ፓርቲዎች፤ ኢህአዴግን የመገዳደር አቅም አላዳበሩም" የሚሉ ጽሑፎችን ለአንባብያን ስታደርስ ቆይተሃል፤ አሁንስ በዚህ ላይ ያለህ አስተያየት ምንድን ነው?**

**ተመስገን፡-** እኔ እስከ ዛሬ ድረስ፣ 'ሀገር ውስጥ ያሉት ተቃዋሚዎች አይረቡም' ላልኩበት ሦስት ምክንያቶችን መጥቀስ እችላለሁ:: የመጀመሪያውና የአንበሳውን ድርሻ የሚይዘው የኢህአዴግ አፋኝነት ነው፤ መለስ ዜናዊ ቃል በቃል በአደባባይ እንደተናገረው 'ተቃዋሚዎች እግር እስኪያወጡ እንጠብቃቸዋለን፤ እግር ሲያወጡ እንቆርጣለን' ነው:: እግርህ ከተቆረጠ እንደጤነኛው አትራመድም፤ በክራንች እየሄድክ ደግሞ ፈጥኖ ከሚሮጠው እኩል ተሽቀዳድመህ ሜዳሊያ ልታገኝ አትችልም::

ሁለተኛው አብዛኛው የፖለቲካ ፓርቲ አመራሮች ሥልጣንና የግል ዝና የሚፈልጉ መሆናቸው ነው::

በሦስተኛነት የምጠቅሰው የሕዝቡን ችግር ነው:: ሕዝቡ በ1997 ዓ.ም ከነበረው ቅንጅት ውጪ በስፋት ወጥቶ ተቃዋሚዎችን ሲደግፍ አልያም ሲገስፅ አልታየም:: 'እናንተ አትረቡም' ብሎ መቆጣትም እኮ ፓርቲዎች እንዲጠናከሩ ይረዳል፤ ሕዝቡ ምናልባት ዳተኛነት ሳይጫነው አይቀርም::

በጥቅሉ የድህነትና የጭቆናው ምክንያት እንዳለ ሆኖ፤ ኢትዮጵያ ውስጥ ጠንካራ የፖለቲካ ፓርቲ እንዳይወጣ ኢህአዴግ በአፋኝነት፣ የተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎች በስግብግብነት እና በግል ዝና ላይ ማተኮራቸው፤ ሕዝቡ ደግሞ ዳተኛ መሆኑ ዋነኛ ችግሮች ናቸው ብዬ አስባለሁ::

ወቅታዊ ሁኔታውን ካየን ደግሞ፣ አብዮት ከሚያመጣው አበርክቶ መሀል አንዱ ማኅበራዊ ፍዘትን በማኅበራዊ መነቃቃት የመቀየሩን እውነታነት እንረዳለን:: አሁን ኢትዮጵያ ውስጥ ማኅበራዊ መነቃቃት ተፈጥሯል:: አንድ ጥሩ ማሳያ የሚሆነኝ የአማራ ብሔራዊ ንቅናቄ ፓርቲ ነው። የፓርቲው ምስረታ ግማሽ ዓመት ሳይሆነው በርካታ ቢሮዎችን በመክፈት መዋቅራዊ ተደራሽነቱን እያሰፋ ነው:: ከዚህ በፊት በኃ/ማርያም ደሳለኝ ጊዜም ሆነ ከዚያ በፊት በነበሩ ጊዜያት፤ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ክልል ላይ ቢሮ መክፈት ፈተና ይሆንባቸው ነበር፤ የአካባቢው ሚሊሻ አከራዮችን ያስፈራራል፤ አባላቱን ቀጥቅጦ ያባርራል:: ዛሬ ያ ጊዜ አልፏል። እናም እየታየ ያለውን የማኅበረ ፖለቲካ መነቃቃት ሌሎች ኅብረ ብሔር ድርጅቶችም በተመሣሣይ ሁኔታ እንዲጠቀሙበት የሚያስችል ዕድል እጃቸው ላይ አለ:: ይሄ ግን ዝም ብሎ እንደ መና ከሰማይ የወረደ ሳይሆን ፖለቲካዊ መብቃት ላይ ባልደረሱ ብላቴኖች መራራ መሥዋዕትነት የተገኘ ድል መሆኑ መዘንጋት የለበትም። ይህንን ዕድል መጠቀም ያልቻለ ታቃዋሚ ፓርቲ ራሱን ቢቀብር ይሻላል።

**ግዮን፡- በትጥቅ ትግል ላይ የነበሩ ኃይሎች በድርድር መሣሪያቸውን እየጣሉ ሰላማዊ ትግልን በመቀበል ወደ ሀገር ቤት መግባት ጀምረዋል፤ ይህንንስ እንዴት አየኸው?**

**ተመስገን፡-** የፖለቲካው አስቂኙ ቀልድ ይሄ ነው:: እየተደረገ ያለው ድርድር አይደለም፤ ለምሳሌ ግንቦት ሠባትን ብትወስደው ድርጅቱ ለዐሥር ዓመት ያህል በኤርትራ በረሃ ነበር፤ እዚህ በተለይ አዲስ አበባ ላይ ቁጥሩ የማይናቅ እጅግ በጣም በርካታ ደጋፊ አለው:: ወያኔም በተደጋጋሚ ሣር ቅጠሉን 'ግንቦት ሠባት' እያለ በማሰር ለንቅናቄው በተዘዋዋሪ የሽያጭ ሠራተኛ ሆኖ አገልግሏል:: በግሌም ግንቦት ሠባት ጠንካራ ድርጅት ነው ብዬ እምናለሁ፤ ስለዚህም ይሄ ድርጅት ወደ ኢትዮጵያ ሲመጣ፣ ጠ/ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ባረፉበት ሆቴል መኝታ ክፍል ውስጥ ተነጋግሮ ብቻ አይደለም መምጣት ያለበት:: በትክክል አደራዳሪ ተመድቦ መወያየት ነበረበት:: ይብዛም ይነስም በረሃ

ቀሪውን በገጽ 17 ይመልከቱ

# የሐሳብ ልዩነት ለዘላለም ይኑር!



ተስፋ (ኢትዮጵያ) አልታሰብ

በኢትዮጵያ እስካሁን ሥልጣን የተቆናጠጡ ሁሉ በሐሳብ ከእነርሱ የተለዩትንና አማራጭ ሐሳብ የሚያቀርቡ ዜጎችን እንደጠላት ማየትና ጦር ይዞ እንደመጣ ተዋጊ መግደልና ማሰር ልማድ ሆኖ ኗሯል:: በሐሳብ የተለየ አጀንዳ ይዘው ፊት ለፊት የሚቀርቡ ዜጎች፤ "ለሰው ልጆች ደህንነት፣ ፍትሕ፣ ሰላምና ሰብዓዊ መብት መሟገት" ብለው ስለሆነ፣ "መልካም ነገር ነው" ብሎ የተለየ አማራጭ ሐሳብ በፀጋ መቀበል አልተለመደም:: እንዲያውም ከመልካም ነገሮች ሁሉ የላቀው መልካም ነገር፣ የተለየ አማራጭ ሐሳብ ይዞ ወደ መድረክ መቅረብ ነው:: የተለየ ሐሳብ ያቀረበን መግደልና ማሰር ጤነኝነት አይደለም:: ተቀናቃኝ የፖለቲካ ፓርቲ እንዲፈጠር በሕገ መንግሥት የፈቀደ ሀገር የሚቃወምና አማራጭ ሐሳብ ይዞ ለሚመጣ በፀጋ የሚቀበል እንጂ፤ ማሰርና ማንገላታት ፍፁም ተቀባይነት የሌለው ምግባር ነው:: በሕገ መንግሥቱ የመናገርና የመፃፍ ነፃነት የፈቀደ ሀገር የተለየ ሐሳብ ሲጻፍበት የሚደነብር መንግሥት፤ ለአማራጭ ሐሳብ ራሱን ክፍት ካለማድረጉም በላይ ላወጣው ሕግ የማይገዛና ለሕጉ ምንም እምነትና ተገዢነት የሌለው ማለት ነው::

ዋለልኝ መኮንን፤ በላይ ዘለቀ፤ ሁለቱ ወንድማማቾች መንግሥቱ ንዋይና ገርማሜ ንዋይ የተገደሉት የተለየ ሐሳብ ስላቀረቡ ነው:: አቤ ጉበኛ፣ በአሉ ግርማ፣ ታሪኩ ላይኔ የተገደሉት የተለየ ሐሳብ በማቅረባቸው ብቻ ነው:: እስክንድር ነጋ፣ ተመስገን ደሳለኝ፣ አንዱ ዓለም አራጌ፣ ውብሸት ታዬ …ወዘተ የታሰሩት ከመንግሥት የተለየ አማራጭ ሐሳብ በማቅረባቸው ነው:: ብዙዎቹ የሀገራችን ጋዜጠኞችና ፖለቲከኞች ሀገር ጥለው ለስደት የተዳረጉት ለሕዝብ የተለየ አማራጭ ሐሳብ በማቅረባቸው ብቻ እንጂ መሣርያ አንግበው መንግሥትን ውጊያ ስለገጠሙ አልነበረም::

አረጋዊ በርሄና ግደይ ዘርዓ ፅዮን በትግሉ ወቅት ለምን ከህወሓት ተባረሩ? የተለየ አማራጭ ሐሳብ በማቅረባቸው ነበር:: በ1992 ዓ.ም ከህወሓት የተባረሩት ጉምቱ ታጋዮች ገብሩ አስራት፣ ስዬ አብርሃ፣ ተወልደ ወ/ማርያም፣ ጄኔራል ፃድቃን ገ/ትንሣኤ፣ ጄኔራል አበበ ተ/ሃይማኖት ወ/ሮ አረጋሽ አዳነ … ወዘተ፤ ከደህዴን አባተ ኪሾ፣ ከኦህዴድ ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ …ወዘተ በመንግሥት ከነበራቸው ሥልጣን እንዲነሱ የተደረጉት፤ የተለየ አማራጭ ሐሳብ ስላቀረቡ ብቻ ነው:: አስተዋይ መንግሥት ቢኖር ኖሮ፣ የተለየ አማራጭ ሐሳብ ለሚያቀርቡ፤ አማራጭ ሐሳብ በማቅረባቸው ብቻ ሊሸለሙ እንጂ፣ ከሥራ ቦታቸው ማባረርና ማሰር እንደ አማራጭ ተደርጎ ሊወሰድ አይገባም ነበር:: አውቀንም ሆነ ሳናውቅ እንደ መንግሥት፣ እንደ ግለሰብ ብዙ ጥፋቶች ተሠርተዋል:: ውጤቱ ደግሞ ዜጎች ስለ ሀገራቸው ጉዳይ በጥብቅ እንዳይጨነቁ፣ ስለ እድገት እንዳይመራመሩ የተሻለ አማራጭ አቅርበው፤ ለሀገር የእድገት መንገድ እንዳያሳዩ እንቅፋት ተሁኗል::

የእኛ ታሪክ (Culture of Resistance) ነው፤ የአሸናፊ ተሸናፊ ፖለቲካ ነው የፖለቲካ ባህላችን፤ የተለየ ሐሳብ የሚያቀርብን የማሳደድ፤ የማሰርና የመግደል ክፉ አባዜ የተጠናወተን ሕዝቦች ነን:: ይህ ደግሞ ደካማ መለያችንና ዓርማችን ሆኗል:: ማንኛውም ሐሳብ ወደ ገበያ ቀርቦ ገዢ ያገኘውን ልእለ ሐሳብ ተቀብለን ሁላችንም በአሸናፊነት ልንወጣ የምችልበት መንገድ መኖር አለበት:: በተለይ የአሁኑ አዲሱ ትውልድ የራሱ አዲስ ሐሳብ ይኖረዋል:: ዘመኑ የሚወልደው አዲስ ሐሳብ ሊኖረው ግድ ነው:: እኛ በፊውዳሉ ዘመን አስተሳሰብ ላይ፣ ልክ እንደ አክሱም ሀውልት ተገትረን ቆመን፤ አዲስ ሐሳብ ሲመጣ የምንቃወም ልንሆን አይገባም:: ከአዲሱ ትውልድ የሚቀርበውን የተለየ አማራጭ ሐሳብ በጥሞና ማድመጥና ተባብሮ ለመሥራት መዘጋጀት ይገባል:: አዲሱም፣ አሮጌውም ትውልድ ሁላችንም ለሀገራችን የረጅም ጊዜ ሕልም አለን:: አንድነቷ የተጠበቀ የበለፀገች ኢትዮጵያን ማየት ነው:: ወደዚያ ለመድረስ ደግሞ ሁሉም ኢትዮጵያውያን ያላቸውን የተለየ አማራጭ ሐሳብ ለህብረተሰቡ የሚያበረክቱበት ነፃ መድረክ ይፈልጋሉ:: "ለሀገሬ ከኔ የሚጠበቀውን እሠራለሁ" ለማለት በቅድሚያ ዴሞክራሲያዊ የሆነ ሀገርና ሁሉንም የተለየ አማራጭ ሐሳብ በእኩል የሚያስተናግድ የፖለቲካ ምህዳር መመቻቸት አለበት::

የተለየ አማራጭ ሐሳብ ለማቅረብ ከፍርሀት ነፃ የሆነ ትውልድ እንዲኖር፤ እኛ በቅድሚያ ከፍርሀት ነፃ መሆን አለብን:: እኛ ከፍርሀት ነፃ ሳንሆን፤ ስለሀገሩ በድፍረት ስለ ሕዝቡ በደል በቁጭት የሚናገርና ሐሳብ የሚያዋጣ ትውልድ ልንፈጥር አንችልም:: ስለዚህም ሀሳባችን ያለ ማንም ጣልቃ ገብነት መግለፅ የምንችልበት ሁኔታ መፍጠር ይኖርብናል:: የፖለቲካ ምህዳሩ ሁሉንም ዜጎች ያለ አድልዎ በእኩልነት የሚያስተናግድ እንዲሆን ማድረግ፤ የዛሬዎቹ ትውልድ የቤት ሥራ ሊሆን ይገባል:: ለሀገራችን እና ለህዝባችን ወዳለምነው ግብ ለማድረስ የሚረዱንን አቅጣጫዎች ማመቻቸት፣ ለነገ የማይባል መሆን አለበት:: የቀድሞ ሰዎች ስለዓለም የማወቅ ዕድላቸው የጠበበ ነበር:: አሁን ደግሞ ስለዓለም ለማወቅ በጣም ቅርብ ነው:: ሞባይላችንን ተጭነን በዓለም ላይ የተፈጠረውን ነገር በሽርፍራፊ ሰከንዶች የምናውቀው ነገር ነው:: የመናገር ነፃነትን የሚያቀጭጭ መንግሥት፣ በአሁኑ ትውልድ መካከል ሊኖር አይገባም:: እርግጥ ነው የመቻቻል ባህል ብዙም የለንም:: የተለየ አመለካከትን የመታገስ ባህል የለንም:: ዴሞክራሲ በዋነኛነት የሚገለጸው በመወያየትና በመቻቻል መርህ ነው::

ነፃ የመረጃ፣ የሐሳብ ስርጭት ዴሞክራሲያዊ ሥርአትን መገንባትና ተግባራዊ ማድረግ፣ የተሟላ የሣይንስና የቴክኖሎጂ ልውውጥ ማከናወን አዳጋች ነው:: ሐሳብን የመግለፅና መረጃን የማሠራጨት ነፃነት ከመሠረታዊ ሰብዓዊ መብቶች አንደ አንድ ሆኖ የሀገራት ሕግ ውስጥ የዓለም አቀፍና የአሕጉራት ስምምነቶች ውስጥ የተካተተው ለዚህ ነው::

የተዛቡ መረጃዎችንና አመለካከቶችን በማሠራጨት፣ ሕዝብ በአንድ ወገን ላይ መሠረተ ቢስ ጥላቻ እንዲያድርበት፣ አንድ የሕብረተሰብ ክፍል (ብሔር) በሌላው ላይ በክፉ እንዲነሣሣ፣ እርስ በርስ በጥርጣሬ እንዲተያዩ በማድረግ፤ የመቻቻልን እሴት የሚያፋልሱ መረጃዎችና አመለካከቶች ሲሠራጩ ቆይተዋል:: አሁንም በስፋት እየተሰራጩ ነው:: የፕሬስ ውጤት ባለቤቶቹ ያሻቸውን አመለካከትና አቋም መሠረት ያደረገ የኤዲቶሪያል ፖሊሲ የመቅረፅ መብት ቢኖራቸውም፤ ነፃ ፕሬስ የሕዝብን ዘላቂ ሠላም፣ ልማትና የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ የሚያረጋግጡ ሐቀኛና ሚዛናዊ መረጃና አመለካከቶችን ይዘው መውጣት ይጠበቅባቸዋል፤ "ነፃ ፕሬስ" የሚያሰኛቸውም ይሄንኑ አማራጭ ሐሳብ ለሕዝብ በነፃነት የማቅረብ ተግባራቸው ነው::

አማራጭ ሐሳቦች በገበያው ውስጥ እንዳይንቀሳቀሱ መፈለግ ማለት፣ ሌሎች አማራጭ ሐሳቦች እንዳያፈልቁና በቆየው ሐሳብ ውስጥ የነበሩ ስህተቶች እንዳይታረሙ መግታት ማለት ነው:: "የነበረው የኔ ሐሳብና አሠራር ብቻ መቀጠል አለበት" ማለት ደግሞ፣ ሁሉም ሰው እንደ ሃይማኖት በአንድ ሐሳብ መመራቱን ለማረጋገጥ ቁጥጥር፣ ግምገማና መሸማቀቅ ያስከትላል፤ ያስቀጥላል:: በእንደዚህ ዓይነት አስተሳሰብና አሠራር ላይ የተመሰረተ ሥርዓት ነፃነትን በማሳጣት የመተራረም ዕድልን ስለሚዘጋ፤ ለሀገርም፣ ለዜጎችም የማይጠቅም አካሄድ ነው::

የቁጥጥርና የአፈና መዋቅር ተዘርግቶና ካድሬዎች ተሠማርተው፣ ሕዝብ በግምገማ እየተዋከበ የአንድ ሰው (መንግሥት) ፍላጎትና ሐሳብ ብቻ እንዲሰርፅበት እንዲሆንና ሌላ የተለየ አማራጭ ሐሳብ እንዳያፈልቅ ሲገደድ ቆይቷል:: ሐሳብን የመግለፅ ነፃነት እስከሌለና በሀገር ጉዳይ ላይ ነፃ ትችት ማቅረብ እንደ ወንጀል ተቆጥሮ የሚያስገድል፤ ወሕኒ ቤት የሚያስወርድና ከሀገር የሚያሰድድ እስከሆነ ድረስ፣ በሀገር ለውጥ አያመጣም:: የአንድ አምባገነን ፓርቲ አገዛዝ፣ የአንድ ግለሰብ ▶

ፈላጭ ቆራጭነትና በአንድ ግለሰብ አምልኮ መጠመድን እንዳስከተለው ሁሉ፣ በድህነትና በአፈና የሚማቅቁት ሚሊዮኖች ጭቆናው በርትቶ፣ "ሆ!" ብለው ሲነሡበት አገዛዙ እንዳልነበረ ይደመሰሳል:: በኢትዮጵያ ውስጥ ሐሳብ እንዳይወረውሩ የተከለከሉ ዜጎች፣ ዛሬ ድንጋይ ለመወርወርና ንብረትና ሰውን አንድ ላይ ለማቃጠል እንደተነሣሡ እያየን ነው:: ድንጋይ መወርወርና ንብረት ማቃጠል ተገቢ ባይሆንም፣ ወደዚህ ደረጃ የተደረሰው ግን የሚቀድመውን በመከልከል የተፈጠረ ነው::

በአንድ ሀገር ሕዝብና መንግሥት የልዩነትና የሐሳብ ብዝኃነት ከተረጋገጠ፤ ልዩነቶችንና ችግሮችን በጉልበትና በመሣሪያ ኃይል መፍታት ያስቀራል:: ለሥልጣን፣ ለዝናና ለሀብት ብለን መከፋፈልን እናቆማለን:: ውይይቶችና ድርድሮች በቅድመ ሁኔታ በማስቀመጥ የጋራ ችግሮቻችንን በቀላሉ እንፈታለን:: የሐሳብ ብዝኃነት ከተረጋገጠ፣ ዜጎችን በማሰርና በመግደል በማሰደድ የማንበርከክ ፍላጎት ባህል ያስቀርልናል:: አምባገነናዊ ፍፁማዊነትን አስወግደን፣ በልዩነት የመኖር መብት ለዘላለም ቢኖር፤ ዜጎችና ሀገር ይበልጥ ተጠቃሚ እንደሚሆኑ እንረዳለን:: የሐሳብ ልዩነት ለዘላለም የሚኖር ከሆነ፣ ለሕዝብ ወሳኝነትና ለሥልጣን ባለቤትነት ጠንክረን በቀጣይነት እንድንታገል ያደርገናል:: በነፃነት ያለፍርሐት ሐሳብን ወደ ገበያ በማውጣት እንዲሸጥ ማድረግ ከቻልን፣ የማኅበደድና የተንበርካኪነት ባህልን በጽናት እንድንንታገል በር ይከፍትልናል:: ለሀገርና ለሕዝብ ሲባል ሐሳባችንን ለመግለፅ ደፋሮች እንሁን:: መጥፎ የሆነውን ነገር ከማቅረብ እንቆጠብ:: መጥፎውን እናስወግድ እንጂ፣ ለሰው ልጆች ጠቃሚ፣ ወደትውልድ የሚሸጋገር አማራጭ ሐሳብ የማቅረብ ጉዳይ ዛሬውኑ እንለማመድ::

የተለየ ሐሳብ ለሀገር ማቅረብ የሕዝብ ፍቅር፣ የሕዝብ አደራ፣ የሕዝብ ጥቅም፣ የሕዝብ አለኝታነት፣ የሕዝብ ወገንተኝነት፣ የሕዝብ አጋርነት መሆን እንደሆነ እንጂ፤ እንደ ጠላት የሚያስገድል፣ ከሀገር የሚያሰድድና የሚያሳስር ሊሆን አይገባም:: ሀገር የምታድገው የተለያየ አማራጭ ባላቸው

> **የአሁኑ አዲሱ ትውልድ የራሱ አዲስ ሐሳብ ይኖረዋል፡፡ ዘመኑ የሚወልደው አዲስ ሐሳብ ሊኖረው ግድ ነው፡፡ እኛ በፈውዳሉ ዘመን አስተሳሰብ ላይ፣ ልክ እንደ አክሱም ሀውልት ተገትረን ቆመን፤ አዲስ ሐሳብ ሲመጣ የምንቃወም ልንሆን አይገባም**

ተቃራኒ ሐሳቦች ጭምር ነው:: ያለወንድና ሴት ልጅ አይፈጠርም:: ያለኔጌቲቭ እና ፖዚቲቭ መብራት አይበራም:: ያለቀንና ሌሊት ጊዜ አይቆጠርም:: የተለየ እውቀት ሳይኖር ሳይንስ አያድግም:: ሀገር ያለመቻቻልና መከባበር ዘላቂነት ሊታሰብ አይችልም፤ ሁሉንም ያማከለ፣ በተቻለ አቅም የሁሉንም ጥቅም ያስጠበቀ ሥርዓት እስካልተመሰረተ ድረስ፣ ሀገርን በሀገርነቷ ለማዝለቅ ይከብዳል:: ይህ ሊሆን የሚችለው ሁሉም የመሰለውን ሐሳብ በነፃነት ማቅረብ ሲችል ነው::

ብዝኃነትን መቀበል ማለት ዞሮ ዞሮ የተለያዩ ፍላጎቶችን በዴሞክራሲያዊ አኳኋን ማስተናገድ ማለት ነው:: እነዚህን ፍላጎቶች ለሟሟላት ደግሞ የተለያዩ ተቃዋሚ ፓርቲዎች መፈጠራቸው አይቀርም:: የነዚህ ፓርቲዎች ዋና ዓላማ በዴሞክራሲያዊ መንገድ በሕዝብ የተመረጠ መንግሥት ያሉትን ጠንካራ ጎኖች ከመንግሥት ጎን ሆነው አብረው የሚያጠናክሩበት፤ ደካማ ጎኖች ካሉት ደግሞ የሚያሳዩበትና የሚተቹበት፤ በአጠቃላይ በሀገራዊ ጉዳይ ላይ በፖለቲካ ሕግ ጨዋታ የሚፋጩበት መድረክ ሲፈጠር ነው:: መድረኩ ደግሞ ሁሉም ያለውን አማራጭ የሚያቀርብበት ሊሆን ይገባል:: እንግሊዛዊ ፖለቲከኛ የነበረው ኤድመንድ ብሩክ የተለየ ሐሳብ ለሚያቀርቡ ተቃዋሚ ፖለቲከኞች፤ "ተቃዋሚዎች ነርቮችንን ያነቃቃሉ፤ ችሎታችንንም ይስላሉ፤ የሚቃወሙን የሚያግዙን ናቸው" ሲል ገልፆ ነበር::

በኢትዮጵያ ውስጥ የነገሡ የተለያዩ የመንግሥት ሥርአቶች ማንኛውም ሰው በነፃ የማሰብ፣ ያመነበትን የመናገርና የመፃፍ፤ እንዲሁም የመረጠውን የማድመጥ መብት ሳይቀር ተከልክሎ የነበረበት ጊዜ ነበር:: የደርግ ሥርዓት በመንግሥት የመገናኛ ብዙሃን ከሚሠራጩ አመለካከቶችና መረጃዎች ውጭ፣ በአየር ላይ የሚሰራጩ የውጭ የሬዲዮ ጣቢያዎችን ማድመጥ እንደ ጠላት ስለሚያስቆጥር፤ መረጃውን ከሌላው ሰው ተደብቆ ለብቻው ለማድመጥ እና ተደብቆ ለማማት የተገደደበት ጊዜ ነበር:: ደርግ እንዲህ በማድረጉ፣ በሥልጣን ላይ አላቆየውም:: ይበልጥ ከሥልጣኑ እንዲወርድ ተጨማሪ ምክንያት ሆኗል::

ማንም ሰው ያመነበትን አመለካከት የማንፀባረቅ መብት ቢያገኝ፤ የሕዝብን መሠረታዊ ሰብአዊ መብቶችና ነፃነቶች የመጋፋት ፍላጎት አይኖረውም:: በሕገ መንግሥቱና በፕሬስ ሕጉ ላይ የተቀመጡት መመሪያዎች፣ የሁሉንም ዜጎች መብት በአግባቡ ሊያስተናግዱ በሚችሉ አኳኋን የተቀመጡ ናቸው:: አንድ ዜጋ የመናገርና ሐሳቡን በነፃነት የመግለፅ መብቱን የሚያስከብረው፤ የሌላውን መብትና ሰብአዊና ግላዊ ክብር እየረገጠ መሆን የለበትም:: መብትን የሚጠይቅ ሁሉ ግዴታውን ጭምር ማወቅ ይጠበቅበቅበታልና::

የዴሞክራሲ ባህልና የተለየ ሐሳብን በነፃነት ማቅረብ ሲባል፣ በድምሩ ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብንና እሴቶችን በህብረተሰብ ውስጥ በዘላቂነት ማስረፅ ማለት ነው:: ይህም ሲባል የዴሞክራሲያዊ ፖለቲካ ጨዋታ ሕግጋትን በጥብቅ መገንዘብንና መተግበርን ይጨምራል::

አምባገነን መንግሥታት የሚፈልጉት ከእነርሱ የተለየ አማራጭ ሐሳብ ይዞ የሚቃወማቸውን ሳይሆን፤ እነርሱን የሚከተል (ተከታይ) ብቻ ነው:: የእነርሱን ማንኛውንም ሐሳብ የሚቃወም፣ ለእነርሱ ዜጋቸው አይደለም:: በአምባገነኖች ቤት መቃወምና አዲስ ሐሳብ ማቅረብ፣ እንደኃጢአተኛ ያስቆጥራል:: አምባገነን መንግሥታት ራሳቸው ያቀረቡት ሐሳብ እንደ ፀሐይ አድርገው፤ ከእነርሱ አመለካከት ውጪ ያሉትን ሌሎችን አማራጭ ያቀረቡ ሐይሎች ደግሞ፣ ጥላዎች ሆነው እንዲታዩ ይፈልጋሉ:: የሌሎች ሐሳብ ፀሐይ መስሎ እንዲታይ ጨርሶ አይፈልጉም:: ስለዚህ ሌሎች አማራጭ አዲስ ሐሳብ አቅርበው ፀሐይ ለመሆን የሚሞክሩትን በመግደል፣ በማሰርና በማሰቃየት ወደ ጥላነት እንዲቀየሩ ከማድረግ አይመለሱም:: አዲስ ሐሳብ ያቀረቡ ዜጎች በነሱ ፊት እንደ ፀሐይ ሆነው ቢታዩ ለሥልጣናቸው አደጋ እንደሆነ በማሰብ፤ እንዲህ አይነት ዜጎች በቅርብ ርቀት እንዳይታዩ የሚፈልጉ መንግሥታት ናቸው:: የተለየ አማራጭ ሐሳብ ያላቸው ዜጎች፣ በቅርብ ርቀት እንዲታዩና እንዲበረክቱ አይፈለግም:: አምባገነን መንግሥታት የሚፈልጉት ተከታዮች፣ አሜን ባዮች፣ ፍፁም ታዛዦችና የሥርአቱ አጨብጫቢዎች እንዲበዙ እንጂ፤ በራስ መተማመን ያላቸውና ለሀገራቸው፣ ለወገናቸውና ለመብታቸው የሚከራከሩ ተከራካሪዎች፤ አዲስ ሐሳብ አፍላቂዎች፤ ጠያቂዎች እና እውነት አፈላላጊዎችን በዚች ምድር እንዲኖሩ ጨርሰው አይፈልጉም::

አሁን ባለንበት 21ኛው ክፍለ ዘመን ላይ፣ አምባገነን መንግሥታትና ጨቋኝ መሪዎች፤ "ለምን ሕዝባቸውን ይጨቁናሉ? ለምን የተለየ አማራጭ ሐሳብ ይፈራሉ?" ብሎ በሥነ እውቀት ደረጃ መፈተሽ ግድ ይለናል:: ጨቋኞች በሥነ እውቀት ከሌላው የወረደ እውቀት ስላላቸው፤ የሰውን ልጅ ለነፃነት፣ ለዴሞክራሲና ለሰብአዊ መብት መከበር ሥልጣናቸው ላይ "አደጋ ያመጣል" ብለው ስለሚሠጉ ነው:: ጨቋኞች በሥልጣናቸው የፈለገውን ያህል ጊዜ ቢቆዩም፤ የሰው ልጅ በሰላም፣ በዴሞክራሲና በነፃነት ውስጥ እንዲኖር አይፈልጉም:: እንዲህ እንዲሆኑ የሚያደርጋቸው አንደኛው ምክንያት የግላቸውን ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጥቅም በዘላቂነት ለማስጠበቅ ስለሚፈልጉ ነው::

አምባገነን መሪዎች የማይተገብሩት አፍአዊ አስተሳሰብ አላቸው:: በተግባር የሚተረጎም፣ ለሕዝብ የሚጠቅም ቅን ግብራዊ ርእዮተ ዓለም ጨርሶ የላቸውም:: ስለ ሕዝቦች ዴሞክራሲ፣ ሰብአዊ መብት፣ መልካም አስተዳደርና የጋራ ተጠቃሚነት በአፋቸው የሚናገሩት ጉንጭ አልፋ ወሬ እንጂ፤ በተግባር የሚተገብሩት እውነተኛ አጀንዳ የላቸውም:: አምባገነኖች በጥቂት ሆድ አደር በሆኑ ተከታዮቻቸው በመጠቀም፤ የተለየ አማራጭ ሐሳብ ለሀገር ያቀረቡን ዜጎችን ሲያስሩ፣ ሲጨቁኑና ሲገድሉ ይታያሉ እንጂ፤ በአፋቸው የሚናገሩትን፣ በየስብሰባው የሚደጋግሙትን ዴሞክራሲ፤ ለሕዝብ ሲሰጡ እስካሁን አልታዩም::

የግለሰብ ፈላጭ ቆራጭ አምባገነንነት መገለጫው፣ "የኔ ሐሳብ ብቻ ነው ትክክል" በማለት የሌሎች ሐሳብ በጭራሽ እንዳይደመጥ መከልከል ነው:: ይህ አይነት አካሄድ ደግሞ ሀገሪቱን ከድህነት፣ ሕዝቡንም ከመሐይምነት እንዳይላቀቅ በማድረግ፤ የአስተሳሰብ ብዝኃነት በዜጎች መካከል እንዳይኖር የእንቅፋት መንገድ ሆኗል:: በመጨረሻም እርስ በርሳችን መቻቻል ያቃተን፣ እርስ በርሳችን የማንተማመን፣ በመግባቢያ ቋንቋችን የማንስማማ፣ በወረደ አስተሳሰብ የዘር እና የብሔርተኝነት አዙሪት እንድንዳክር ያደረገንና የኋላ ቀርነት መገለጫ ሀገር ወይም ምሳሌ ሆነን እንድንታይ ያደረገን ዋናው ምክንያት፤ አማራጭ ሐሳብ ገበያው ውስጥ እንዳይኖር በማድረጋችንና ፈልገንም በማጣታችን ነው:: ስለዚህ ለሀገር ሰላም፣ እድገት፣ ለዴሞክራሲ ማበብ፣ የዜጎች መቻቻል በሀገራችን እንዲኖር፤ "የልዩነት መኖር መብት ለዘላለም ይኑር" ብለን ልንፊክርና ልንተገብር ይገባል::

***የተለየ ሐሳብና ኢትዮጵያ ለዘላለም ይኑሩ!***

# “ህወሐት ከመንግሥት አካውንት 35 ሚሊዮን ዶላር በመውሰድ ኤፈርትን ደጉሟል”



## አምባሳደር ካሳ ከበደ (ልዩ ቃለ ምልልስ)

*አምባሳደር ካሳ ከበደ ከአባታቸው ደጅ አዝማች ከበደ ተሰማ፣ ከእናታቸው ከወይዘሮ ይታጠቁ ኪዳኔ፤ የካቲት 18 ቀን 1935 ዓ.ም በአዲስ አበባ ነው የተወለዱት፡፡ ጣልያን ከሀገር በወጣ በሁለተኛው ዓመት የተወለዱት አምባሰደር ካሳ ከበደ፣ ዐሥራ ስምንት ዓመት ሲሞላቸው፤ ወደ እስራኤል በመሄድ በውትድርናም አካዳሚክ ትምህርት ተከታትለው ከአምስት ዓመት ቆይታ በኋላ ወደ ሀገር ቤት ተመልሰዋል፡፡*

*በንጉሡ ዘመንም ሆነ፣ በደርግ ሥርዓት ውስጥ በከፍተኛ የመንግሥት ተቋማት ላይ በሐላፊነት ያገለገሉት የመጽሔታችን እንግዳ፤ በተለይም፣ በኮ/ል መንግሥቱ ኃ/ማርያም የሥልጣን ዘመን የኢሰፓ ፓርቲ የውጭ ጉዳይ ሐላፊ በመሆን በርካታ ሥራዎችን ያከናወኑ ሲሆን፤ በጄኔቭ የኢትዮጵያ አምባሳደር በመሆንም ትልቅ የዲፕሎማሲ ሥራ አከናውነዋል፡፡*

*በ1983 ወርኃ ግንቦት፣ የደርግ ሥልጣን ማክተሚያ ላይ በአሜሪካ አይሁዶችና መንግሥት ግፊት፤ በእስራኤል ጠያቂነት ወደ ቴልአቪቭ የተጓጓዙት ሃያ ሺህ የሚደርሱ ኢትዮጵያውያን አይሁዶችን ጉዳይ በተመለከተ፤ ከሀገሪቱ ጋር የተደረገውን ጠንከር ያለ ድርድር በበላይነት የመሩትና አይሁዶቹን ለሚያጓጉዘው ለኢትዮጵያ አየር መንገድ የ35 ሚሊዮን ዶላር ክፍያ እንዲፈፀም ዝርዝር ሂደቱን ያስፈፀሙት አምባሳደር ካሳ ከበደ፣ በወቅቱ ስለነበሩት አጠቃላይ ፖለቲካዊና ሀገራዊ ሂደቶች በስፋት ነግረውናል፡፡*

*አምባሳደር ካሳ ደርግ እንዴት እንደተመሠረተና አጠቃላይ መዋቅሩ በማንና በምን መንገድ ይሽከረከር እንደነበር የነገሩንን ወደ ፊት ለአንባብያን የምናደርስ ሲሆን፤ ለዛሬው “መቅደም አለባቸው” ያልናቸውን ጉዳዮች መርጠን አቅርበናል፡፡ አምባሳደር ካሳ ከበደ ከሃያ ሰባት ዓመት በኋላ ወደ ሀገር ሲመለሱ ባረፉበት ኢንተር ኮንትኔንታል ሆቴል የተገኙት የግዮን ጋዜጠኞች ፍቃዱ ማ/ወርቅና ሮቤል ምትኩ እንዲህ ባለ መልኩ አነጋግረዋቸዋል፡፡*

**ግዮን፡- በደርግ ሥርዓት ማብቂያ፣ ኢህአዴግ አዲስ አበባ ሊገባ በጣት የሚቆጠሩ ቀናት ሲቀሩት ነበር ከሀገር የወጡት፤ አወጣጥዎ በጣም ሰፊ ታሪክ ያለው ከመሆኑ አኳያ፤ አስቀድመው ይሄን ነገር ቢገልፁልኝ?**

**አምባሳደር ካሳ፡-** በሀገሪቱ ውስጥ በሰሜን በኩል ያለው እንቅስቃሴ ወደ መሀል ሀገር እየገፋ፣ በኤርትራም ያለው ሁኔታ እየተለወጠ ሲመጣ፤ ደርግ ያዘው የነበረው ሠራዊት እየተፈታ፣ እየተበተነ መዋጋቱን አቁሞ ወደ አዲስ አበባና ወደ መጣበት አካባቢ መመለስ ሲጀምር፤ በቅድሚያ በመንግሥት በኩል የተፈለገው ከወያኔና ከሻዕቢያ ጋር መደራደር ነበር::

ጎርቫቾቭ ሥልጣን ላይ ከወጣ በኂላ፣ ከ1983 ዓ.ም በፊት በነበሩት አራት ዓመታት የጦር መሣሪያ መርዳት አቁሞ፣ ችግሩ በድርድር ነው መፈታት ያለበት የሚል አቋም በመያዟና ጎርቫቾቭ ከአሜሪካ ጋር በመቀራረባቸው፣ የአደራዳሪነቱን ሚና ለአሜሪካኖቹ ሰጡ:: በዚህ የተነሣ አሜሪካኖቹን በግድ ተቀበልን፤ ለድርድር በምንዘጋጅበት ጊዜ፣ በወቅቱ የነበሩት የአሜሪካ ፕሬዝዳንት ትልቁ ቡሽ መልዕክተኛ ላኩ:: ድርድሩን ከኢትዮጵያውያን አይሁድ ፈላሾች ጋር አያያዙት:: በጎንደር በመጠኑ ደግሞ በትግራይ አካባቢ ኢትዮጵያውያን አይሁዶች አሉ፤ ቀደም ሲል እስራኤሎች ‘ዘመቻ ሞሰስ’ ብለው በጠሩት ኦፕሬሽን አማካይነት በ1977 ዓ.ም የድርቅ ወቅት አካባቢ በድንበር በኩል በሱዳን እያሻገሩ፣ ‘የድርቅ ጉዳተኞችን እንረዳለን’ በሚል የውጭ በጎ አድራጎት ድርጅቶች ሽፋን ገብተው የነበሩ የአሜሪካና የእስራኤል አይሁዶች ‘ወንበዴ’ ብለን ከምንጠራቸው ወያኔና ሻዕቢያ ኃይሎች ጋር እየተረዳዱ ኢትዮጵያውያን አይሁዶችን ወደ እስራኤል ወስደዋቸው ነበር::

ከስድስት ዓመት በኂላ በ1983 ዓ.ም የአሜሪካ አይሁዶች በሚያደርጉት ከፍተኛ ግፊት ምክንያት፤ በእስራኤል መንግሥት ላይ ባሳደሩት ተጽዕኖ፣ ኢትዮጵያውያን አይሁዶችን ወደ እስራኤል ለማምጣት በኢትዮጵያ መንግሥት በኩል ተስማማን:: ግን ስንስማማ ያስቀመጥናቸው መደራደሪያ ነጥቦችና ጥቅማ ጥቅሞች ነበሩ::

**ግዮን፡- እነዚያ የመደራደሪያ ነጥቦችና በኢትዮጵያ መንግሥት በኩል የተቀመጡት ቅድመ ሁኔታዎች ምን ምን ነበሩ?**

**አምባሳደር ካሳ፡-** በሰዓቱ፣ ‘እነዚህ ቤተ እስራኤሎች አይሄዱም’ ብሎ መንገታገት ይቻል ነበር፤ ግን ወንበዴዎቹ በተለይ ህወሓት ብዙ አካባቢዎችን ተቆጣጥሯል፤ ስለዚህ፣ ‘ከጎንደር አዲስ አበባ አይመጡም’ ማለት አስቸጋሪ ነው:: ደርግ ከመውደቁ ሁለት ዓመት በፊት፣ ኢትዮጵያና እስራኤል ወዳጅነት መሥርተዋል፤ ያንን ተከትሎ፣ አዲስ አበባ የእስራኤል ኤምባሲ መቋቋሙ ሲሰማ፤ ብዙ ኢትዮጵያውያን አይሁዶች ያኔ ‘ፈላሾች’ ነበር የምንላቸው፣ እስራኤል ኤምባሲ አካባቢ ግርግር መፍጠር ጀምረው ስለነበር፣ እነዚህ ኢትዮጵያውያን አይሁዶች ወደ እስራኤል ካልሄዱ፣ ‘የኢትዮጵያን መንግሥት ከወንበዴዎች ጋር አናደራድርም’ የሚል አቋም በፕሬዝዳንት ቡሽ መንግሥት ተያዘ::

ያኔ በነበረው የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት፣ ‘ማንኛውም ዜጋ የመንቀሳቀስ መብት አለው’ ስለሚል ይሄን መብታቸውን ለነዚህ አይሁዶች ሊያከብርላቸው ይገባል:: በሌላ በኩል፣ ‘ኦፕሬሽን ሞሰስ’ በተሰኘው ዘመቻ፣ ባል ሄዶ ሚስት የቀረችበት፤ ልጆች ሄደው ወላጆች የቀሩበት የተገነጠለና ያልተሟላ አካሄድ ስለነበር፣ ‘ሕገ መንግሥታችሁ ለዜጎች ጥበቃ ይደረጋል’ ይላል፤ ‘ያ ለምን አልተደረገም?’ የሚል ለክርክር አስቸጋሪ የሆነ ምክንያት ቀርቧል::

ይሄንን ጥያቄ ሊቀ መንበር መንግሥቱ ሲቀበሉት፣ በእኛ በኩል ሊደረግልን ስለሚገቡ ጉዳዮች ጥያቄዎች አቅርበው ነበር:: ይሄንን ሥራ የመምራትና ዝርዝሩን የማስፈፀም ሓላፊነት፣ ለእኔ ነው የሰጡት:: በዚያ መሠረት፣ በእኛ በኩል እኔ፤ በእስራኤሎችም በኩል ▶



◀እንዲሁ ዝርዝር ጉዳዩን የሚያስፈፅሙ ሰዎች ተመርጠው፣ ንግግሮች ተደርገው ስምምነት ላይ ተደርሷል:: አይሁዶች ስላልተጓጓዙ፣ ለንደን ላይ ሊካሄድ የነበረው ድርድር፣ በቀጠሮ ከተያዘ በኋላ፤ የአሜሪካኖቹን በጉዳዩ ላይ ማምረርና አለማምረር ለመፈተሸ ሞክረናል፤ ማምረራቸው ሲታወቅና የድርድር ቀጠሮው እንዲተላለፍ ሲደረግ፣ ወደ አፈፃፀም ነው የተሄደው::

ያኔ አረቦቹ፣ ቤተ እስራኤሎች ወደ እስራኤል እንዳይሄዱ ከፍተኛ ፍላጎት ስለነበራቸው፤ አረቦቹንም ሳናስቀይም፣ ሥርዓት ባለው መንገድ፣ ብዙ ጩኸት ሳይኖር፣ ለሕዝብም ይፋ ሳይሆን እንዲፈፀም ተፈልጎ ነበር - በሊቀ መንበር መንግሥቱ በኩል:: ሌላው 'የቤተሰብ ውሕደት' ተብሎ የተጀመረ የጉዞ ፕሮግራም ነበር፤ እነዚህን የተለያዩ ልጆችና ወላጆች፣ ባልና ሚስት የማገናኘት በኢምግሬሽን ባለሥልጣን አማካይነት፣ ስምንት ሺህ አምስት መቶ የሚሆኑ ቤተ እስራኤሎች ከኦፕሬሽን ሰሎሞን በፊት ወደ እስራኤል ሄደዋል:: የአካሄድ ጫጫታና ግርግር የሞላው ስላልነበረ እስካሁን ድረስ እንኳን ብዙ ሰው አያውቅም::

ያኔ እነሱ የሚጓጓዙት፤ ከዚህ ሮም፣ ከሮም ወደ እስራኤል ቴልአቪብ እንጂ ቀጥታ በረራ አልነበረም፤ ሊቀ መንበር መንግሥቱ በዚያ ኦፕሬሽን ሰሎሞን ኢትዮጵያውያን አይሁዶች ሲጓጓዙ፤ 'የኢትዮጵያ አየር መንገድ ቀጥታ ተጠቃሚ እንዲሆን እፈልጋለሁ' ብለው ስለነበር የኢትዮጵያ አየር መንገድ ባለሥልጣኖችን ቢሮ ድረስ ጠርቼ ከእስራኤሎች ጋር አገናኘኋቸው:: 'ቤተ እስራኤሎቹ ለመሄድ ፈልገዋል' በሚል አዲስ አበባ መሰብሰባቸውን ብቻ ነው የምናውቀው፣ ግን እዚያ ከሄዱ በኋላ ሳይመቻቸው ቢቀርና 'እንመለስ' ቢሉ አስቸጋሪ ስለሚሆን፤ የኢትዮጵያ አየር መንገድ በጠየቀው ዋጋ መሠረት የደርሶ መልስ የቲኬት ዋጋ ገንዘብ እንዲከፈል አድርገን ነበር:: ለዚሁ ጉዳይ የሚያገለግሉ አውሮፕላኖች የኢትዮጵያ አየር መንገድ መድቦ እንደነበር አስታውሳለሁ:: ሁለተኛው ቀጠሮ ሲደርስ፣ በእኛ በኩል እንዲያደርጉልን የምንፈልጋቸው ፖለቲካዊ ጉዳዮች ነበሩ::

**ግዮን፡- የአሜሪካ መንግሥት እንዲያስፈፅመው የተፈለገው ፖለቲካዊ ጉዳይ ምንድን ነው?**

**አምባሳደር ካሳ፡-** እስከዚያ ጊዜ ድረስም ሆነ አሁን አሜሪካኖቹ የኢትዮጵያን አንድነት ይደግፋሉ፤ ሻዕቢያ በጦርነቱ ድል ቀንቶት አስመራን ቢቆጣጠርና ነፃነትን ቢያውጅ፤ የአሜሪካ መንግሥት ለኤርትራ ነፃነት እውቅና እንዳይሰጥ በዋነኝነት ጥያቄ አቅርበናል:: ራሳቸው ዕውቅና አለመስጠት ብቻ ሳይሆን፣ አጋሮቻቸውም ዕውቅና እንዳይሰጡ ግፊት እንዲያደርጉልን በሰዓቱ ስንጠይቅ፤ ጦርነቱ በነበረው መልክ ያበቃል የሚል ዕምነት አልነበረንም:: መንግሥት መቀመጫውን ወደ ደቡብ በማዞር ትንሽ ተጠናክሮ መልሶ ወደ ማጥቃት ይገባል የሚል እሳቤ ብዙዎቻችን ነበረን:: ግን ያው መጨረሻ ላይ ይሄ ሂደት ባለበት ሰዓት ሊቀ መንበሩ ከሀገር መውጣታቸው ተነገረ:: ድርድሩ ሊካሄድ የቀረው ጊዜ ከሳምንት ያንሳል::

ስለዚህ በዚያ ጊዜ ውስጥ የአሜሪካኖችና የእስራኤሎች ፍላጎት መጠናቀቅ ነበረበት፤ የወቅቱ የእስራኤል ጠ/ሚኒስትር ሻሚር፣ ልዩ መልዕክተኛ ለፕሬዝዳንት ቡሽ በመላክ፣ በአሜሪካ በኩል እኛን ለመደገፍ ይሁንታ ተገኝቶ የነበረ ቢሆንም፤ ሊቀ መንበር መንግሥቱ ኃ/ማርያም ከሀገር ከወጡ በኋላ፣ በውስጣችን የነበረው ሽኩቻ፣ የሥልጣን አያያዝ ነው ችግር የፈጠረው:: የኢሠፓ ወይም የኢህዲሪ መንግሥት አካል የመሆን ጉዳይ፣ የኢሠፓና የመንግሥት ካድሬዎችን ደህንነት ጉዳይ በሚመለከቱ ከአሜሪካኖች ኢንሹራንስ ጠይቀን ፈቃደኞችም ነበሩ፤ በእኛ መካከል በነበረው አለመግባባት የተነሣ ደብዳቤ ሳንለዋወጥና ማስፈፀም ሳይቻል ቀረ:: ስለዚህ፣ በዘመቻ መልክ ኢትዮጵያውያን አይሁዶች፣ በግንቦት 1983 ዓ.ም አጋማሽ መጀመሪያ ላይ ከሀገር እንዲወጡ ተደረገ::

**ግዮን፡- የእርስዎ ሓላፊነት ምን ነበር?**

**አምባሳደር ካሳ፡-** በጊዜው የኢሠፓ ፓርቲ የውጭ ግንኙነት ሓላፊ ነበርሁ፤ በዚህ ምክንያት ከእስራኤሎች ጋር ይደረግ የነበረውን ድርድር በሓላፊነት የመራሁት እኔ ነኝ፤ ቤተ እስራኤሎቹን ማስወጣት በሚመለከት ግን የኢሚግሬሽን ጉዳይ ነው:: ያከናወነው የሕዝብ ደህንነት ም/ሚኒስትር የነበረው ኮ/ል መርሻ ቀፀላ ከእኔ ጋር ይሠራ ስለነበር፤ የሚወሰነውን የሚያስፈፅመው እሱ ነው:: ኮ/ል መርሻ ከመጨረሻችን አንድ ስድስት ወር ያህል ቀደም ብሎ፣ ከእስራኤሎች ጋር በዚሁ ሥራ ይገናኝ ስለነበረ፤ ቤተሰቡን እስራኤሎች እንዲወስዱለት በጠየቀው መሠረት ባለቤትና ልጆቹ ወደ እዛ ሄደው ነበረ፤ ግን በግዜው እሱ ይሄን ጥያቄ ሲያቀርብ፤ 'አምባሳደር ካሳ ከፈቀደልህ ነው የምንወስደው' ስላሉት፣ ጠይቆኝ ፈቅጄለት ነው ቤተሰቦቹን ወደ እስራኤል የላከው:: መጨረሻ ላይ ደግሞ፣ 'ቤተ እስራኤሎቹን ልትወስዷቸው ነው፤ የእኔም ቤተሰቦች ያሉት እስራኤል ስለሆነ፣ እኔንም ወስዳችሁ ከቤተሰቤ ቀላቅሉኝ' የሚል ጥያቄ ሲያቀርብ፤ አሁንም፣ 'ካሳ ከፈቀደልህ እንወስድሃለን' ስላሉት መጥቶ ሲነግረኝ፤ 'ቀን ቤተ እስራኤሎች ተወስደዋል፤ ማምሻው ላይ እስኪ እንሂድና እስራኤሎቹን እናነጋግር' በሚል ከኮ/ል መርሻ ጋር ተያይዘን ሰዎቹ ወደ አረፉበት ሄድን::

እዚያ ስንደርስ፣ ለካ የእስራኤል ጦር ኤታማዦር ሹም ሁሉ በድብቅ መጥቶ፣ ያንን ኦፕሬሽን ያስተባብር ነበር፤ ይሄ መረጃ እኛ አልነበረንም:: ሌሎች በሥራ ኢየሩሳሌም የማውቃቸው የእስራኤል ባለሥልጣናት ሁሉ እዚህ ገብተዋል:: 'ሶሻል ወርከርና ለሥራው የሚያግዙ ሰዎች' ብለው የእስራኤል ኮማዶዎችን ሲቪል አልብሰው አስገብተዋል::

**ግዮን፡- ይሄ የሆነው ምናልባት ኢትዮጵያውያን አይሁዶችን በመንግሥት በኩል በሰላም የመልቀቅ ፍላጎት ከሌለ፤ የኃይል አማራጭ ለመጠቀም ነው?**

**አምባሳደር ካሳ፡-** ትክክል:: በኋላ እንደተረዳሁት ከሆነ፣ እኛ እምቢ ብንላቸው፣ የኃይል ዕርምጃ ወስዶ ኦፕሬሽኑን ለማሳካት የተደረገ ዝግጅት ነበር፤ ግን በጣም የሚገርመው በዚህ መልክ እስራኤሎቹ ሀገር ውስጥ ሲገቡ፣ እኛ አናውቅም ነበር:: ስለ ቀኑ ውሎአቸው ለማወቅ እስራኤሎቹ ጋር ስናመራ፤ 'ምነው በሌሊት ምን አመጣህ?' ሲሉኝ፤ ስለ ኮሎኔል መርሻ ጉዳይ መሆኑን ስነግራቸው፤ ቺፍ ኦፍ ስታፍ ወይም የጦር ኤታማዦር ሹም የነበረው ሰው፣ 'ለራስህስ ምን አስበሃል?' ሲለኝ፤ 'ለእኔማ ምን አስባለሁ፤ ውሰዱኝ ብልስ ትወስዱኛላችሁ ወይ?' ብዬ ስጠይቃቸው፤ 'እሱን ከወሰድን አንተን ለምን አንወስድህም?' የሚል ምላሽ ሲሰጡኝ፤ ያኔ እዚህ የእስራኤል አምባሳደር የነበረ አሸር ዳሂም የሚባል ሰው፣ 'እሱን አንችልም፤ ለአሜሪካኖቹ ከፈላሾች ጋራ ከፍተኛ ባለሥልጣኖች አናስወጣም' የሚል ቃል ገብተናል፤ በሚል ችግር መኖሩን በፊት ለፊት ተናገረ::

ከዚህ ሰው ጋር፣ ቀደም ሲል ወጣት ሆነን እስራኤል ውስጥ እንተዋወቃለን፤ እኔ እስራኤል ነው የተማርሁት:: 'እዚህ ነው የመሸው እንጂ፣ ዋሽንግተን ገና ቢሮ አልተዘጋም:: አሜሪካኖቹን ለምን አናናግርም?' በሚል ኮ/ል መርሻና እኔን ቤታቸው ትተውን ወደ ኤምባሲ ሄደው ጠይቀው ተመልሰው መጡ:: 'እጁ ላይ ደም የለምና ካሳንም መውሰድ ትችላላችሁ ብለውናል' የሚል ምላሽ ሰጡኝ፤ 'ስለዚህ ነገ ኦፕሬሽኑ ሲያልቅ፣ ተያይዘን መሄድ እንችላለን' የሚል ያላሰብሁበት ምላሽ ሰጡኝ::

በጊዜው፣ 'የደብዳቤ ልውውጦች በሠራናቸው ሥራዎች ላይ ይኖራሉ' ብዬ ተስፋ አድርጌ ነበር፤ ለእኛ፣ ማለትም በሰዓቱ ለነበረው መንግሥት ፓርቲ የሚበጀው እሱ ነበር:: አስታውሳለሁ፤ እዚያው እስራኤሎች ቤት ሆኜ፣ 'የመጨረሻ ሙከራ ላድርግ' በሚል በወቅቱ የሀገሪቱ ጊዜያዊ ፕሬዝዳንት ለነበሩት ጄኔራል ተስፋዬ ገብረ ኪዳን ስልክ ደወልሁኝ:: ቀደም ሲል፣ ዋሽንግተን ሄደው ለአሜሪካኖቹ አሳይተው እነሱም ተቀብለውታል፤ የሚቀረው ያንን ረቂቅ ደብዳቤ ለሊቀ መንበር መንግሥቱ እንዲልኩ ነው:: ሊቀ መንበር መንግሥቱ ኃ/ማርያም ከሀገር የወጡት ደግሞ፣ የእስራኤል ልዑካን እዚህ የገቡ ቀን ነው:: ያለውን ሁኔታ አስረድቼ፣ ለምክትላቸው እንዲጻፍ ተደርጎ ደብዳቤው ወጣ፣ ያንን ደብዳቤ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትርም አቀረበ፤ እኔም አቀረብሁና ጄኔራል ተስፋዬን 'ፈርም' አልሁት:: ጄኔራል ተስፋዬ ግን ለመፈረም ችግር ውስጥ ገባ::

**ግዮን፡- ምክንያታቸው ምን ነበር?**


**አምባሳደር ካሳ፡-** እስራኤሎቹም፣ እኔም ደብዳቤ እንዲፈረም ጓጉተን ነበር፤ ግን ጄኔራል ተስፋዬ ሲጨንቀው፣ 'ሥልጣን እኮ እኔ እጅ አይደለም፤ እኔ እስከ ሰኞው የለንደን ድርድር ድረስ ወንበር ጠባቂ ነኝ:: ሥልጣን ያለው ተስፋዬ ዲንቃ፣ ተስፋዬ ወ/ሥላሴና መንግሥቱ ገመቹ ጋር ነው፤ እነሱ ደግሞ አይሆንም ብለዋል፤ እስኪ በራስህ ሞክራቸው' አለኝ:: መንግሥቱ ገመቹ፣ 'ሊቀ መንበሩን ሳይፈልግ ነው ያባረረው' በሚል፣ የልዩ ጥበቃ ጦር ይፈልገው ስለነበር፤ ሌላ ቦታ ሄዶ ተደብቆአል፤ እሱን ማግኘት አይቻልም ነበር:: አቶ ተስፋዬ ዲንቃና ኮ/ል ተስፋዬ ወ/የስን ግን አግኝቼ አነጋግሬ፣ 'እኛ ራሳችን በቀጥታ ከሲአይኤ (CIA) ጋር የዘረጋነው መስመር ስላለ ተነጋግረናል፤ እነዚህ እናንተ የምትሏቸው ነገሮች በጭራሽ አያስፈልጉም' የሚል አቋም ያዙ:: እንዲያውም ለንደን ላይ ቁጭ ብለን ስንደራደር፣ 'ለፈላሾች ጉቦ ሰጥታችሁ መጣችሁ ብለው ያናንቁናል' የሚል ሐሳብ ሰነዘሩ:: በተለያየ መንገድ ላግባባቸው ብሞክርም አልተሳካም::

መጨረሻ ላይ እስራኤሎቹ፣ 'እንወስድሃለን' ያሉኝ ቀን፤ ለጄኔራል ተስፋዬ ገ/ኪዳን ቤቱ ደወልኩና፣ 'እነዚህ ሰዎች ሌሊቱን ወደ እስራኤል ተጓጉዘው ሊያልቁ ይችላሉና፣ ከቻልህ የመጨረሻ ሙከራ አድርገህ ይሄ ደብዳቤ ቢፈረም' ብዬ ለማሳሰብ ሞከርሁኝ፤ እሱም፣ 'ጠዋት ቢሮ ናና አብረን ደግሞ እንሞክራቸው' ብሎ ስለቀጠረኝ፤ ቅዳሜ ጠዋት ተነሥቼ እሱ ቢሮ ሄድኩኝ:: እንደ አጋጣሚ እዚያ ስደርስ፣ 'አንተን እየጠበቁ ▶

እያለ፣ በአጋጣሚ ኮ/ል ተስፋዬ ወ/ሥላሴ ገብቷል፤ መምጣትህን ገብቼ ልንገራቸው ወይ?' የሚል ሐሳብ ጽ/ቤት ሓላፊው ሲያቀርብልኝ፤ የኮ/ል ተስፋዬን ሐሳብ ስለማውቅ፤ ያንን ማድረግ አልፈለግሁም:: ለእኔ ግልፅ ባልሆነ ምክንያት እነዚህ ሦስት ሰዎች ቀደም ሲል የተነደፈው ዕቅድ በታለመለት ፕሮግራም እንዲጓዝ አልፈለጉም ነበር:: 'ከሲይ አይ ኤ ጋር ግንኙነት አለን የሚሉ' አሉ፤ ከዚያ ውጭ ያለነውን የማግለል ነገር ነበር፤ እርስ በርሳችን አልተስማማንም ነበር:: በዚያ ሰዓት ጄኔራል ተስፋዬ ቢሮ ኮ/ል ተስፋዬ ወ/ሥላሴ እንደገባ የነገረኝ ሰው፣ የዕለት ሁኔታ ተመዝግቦ በሪፖርት መልክ የመጣውና ለፕሬዝዳንቱ የተላለፈ ነገር ደግሞ፤ ሙሉ በሙሉ እኔ ከምሠራው በተቃራኒ የሆነና ጠልፎ ለመጣል የሚደረግ እንቅስቃሴ ነበር::

**ግዮን፡- በሰዓቱ እነዚህ ኃይሎች እርስዎን ለመወንጀል ሞክረው ነበር ማለት ነው?**

**አምባሰደር ካሳ፡-** ያኔ እኔ የምይዛት ላዳ መኪና ነች፤ የእሷ ታርጋ ተጠቅሶ፣ ሐሙስ ዕለት ሀዋሳ ከተማ መታየቴ በሪፖርት ተላልፎአል፤ ይህ የሆነው ቅዳሜ ቀን ነው:: 'ይህ ምን ማለት ነው?' ስል፤ የልዩ ጥበቃ ጦር አዛዥ የነበረ፣ ጄኔራል ገረመው በቀለ፣ ጦሩ አባሮት እዚያው ጄኔራል ተስፋዬ ቢሮ ተቀምጦ ነበር፤ ወደ ኮሪደር ወሰደኝና፣ 'ይሄ ሊያጠፉህ የፈለጉ ሰዎች እንዳሉ የሚያሳይ ሪፖርት ነው' ይለኛል፤ ያኔ ድንጋጤ ተሰማኝና፣ 'ተመልሼ እመጣለሁ' ብዬ ከጄኔራል ተስፋዬ ቢሮ ሥራው እንዴት እንደሆነ ለማወቅ እስራኤሎቹ ወዳረፉበት ሒልተን ሆቴል ስሄድ፤ ሌሊቱን በሙሉ ኦፕሬሽኑን ጨርሰው፣ ለእኔ ቃል ስለገቡልኝ እየጠበቁኝ ነበር፤ 'የት ጠፋህብን? ቢሮም የለህም፤ ቤትህም የለህም፤ ስልክ ብንደውል አጣንህ፤ አንድ ሰዓት ጊዜ አለህ፤ ሁሉን ነገር አስተካክለህ ተመልሰህ ሂልተን ና፤ አብረን እንሄዳለን፤ ካልመጣህ ግን ጥለንህ መሄዳችን ነው' አሉኝ::



ባለቤቴ አንድ ሰዓት ለመጠቀም ብዬ፣ ወደ ቤት ሄድሁ፤ በእጄ የምይዘው ትንሽ ነገር በጥድፊያ አዘጋጅቼ፣ ቦርሳ ቢጤ መያዣ ውስጥ ከተትሁኝ፤ የግል ሽጉጥ ነበረኝ፣ እሱን ያዝሁኝ፤ እንደተባባልነው ተመልሼ ወደ ሒልተን በመሄድ እዚያ ተገናኘን:: ኮሎኔል መርሻም እዚያ ይጠብቅ ነበር፤ የሰፈር ሰው 'ሒልተን አድርሰኝ' ብዬ የራሴን መኪና ቤት ትቼ ነው የሄድሁት፤ ትንሽ ድንጋጤም ነበር::

**ግዮን፡- በዚያ ፍጥነት ከሀገር ለመውጣት ከእስራኤሎች ጋር ሲስማሙ የቤተሰብዎን ሁኔታ እንዴት አደረጉ? የነበረዎት ስሜትስ ምን ይመስል እንደነበር ወደ ኋላ መለስ ብለው ቢያጫውቱን...**

**አምባሰደር፡-** ባለቤቴ ለተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ነበር የምትሠራው፣ ከጄኔቫ አምባሳደርነት እኔ ወደዚህ ስመለስ፤ እሷም እንደ አጋጣሚ እዚህ የዩኤንኤችአር (UNHR) አስተዳዳሪ ሆና ወደ ኢትዮጵያ ተዛውራ ነበር:: የወያኔ ጦር እየተቃረበ ሲመጣ፣ የአዲስ አበባ ፀጥታ አሳሳቢ ሲሆን፤ በርካታ የውጭ ድርጅቶች ሥራቸውን ወደ ኬንያ አዟዙረው ነበር፤ በሰዓቱ የኢትዮጵያ አየር መንገድም ቢሮውን ወደ ኬንያ ናይሮቢ አዟዙሮ ነበር:: ስለዚህ፣ ባለቤቴም ልጆቼም ውጪ ነበሩ፤ በወቅቱ የቤተሰብ ሁኔታ ለእኔ አሳሳቢ አልነበረም::

ስሜ በሌላ መስመር ወደበላይ አካል ሪፖርት በመደረጉ፣ የነበረኝ ምርጫ ወይ ከሀገር መውጣት፤ አልያም ነገሮችን በድፍረት መጋፈጥ ነበር:: ይሄ የሚሆነው ከራሳችን ሰዎች ጋር መሆኑ በርግጥ ያሳዝናል፤ በጊዜው ከሀገር መውጣት የሚችሉ ብዙ የእኛ ጓዶች ነበሩ:: ግን ያኔ በነበረው የራሳችን ደህንነት እየታገቱ እንዳይወጡ ተደርገዋል፤ እኔም እንዳልወጣ መፈለጉን ተረድቻሁ፤ በምንም ዓይነት እንድሄድ አይፈቅዱልኝም ነበር:: ከወያኔም ከሻዕቢያም ጋር በተለይ ከወያኔ ጋር የሚሠሩ የእኛ ሰዎችም ነበሩ፤ ይሄ በጣም ያሳዝናል::

ቀደም ሲል እንደነገርኩህ መሣሪያዬን ይዣለሁ፤ ውትድርናም ቢሆን ትንሽ ሰልጥኛለሁ፤ ስለዚህ መጨረሻው ከመጣ፣ ለወያኔም አሳልፈው ቢሰጡኝ 'ሞት ነው' በሚል ከፍተኛ ጥንቃቄ አድርጌ ነበር:: በመኪናዬም ያልሄድሁት ለዚህ ነው:: እስራኤሎች ከመጡ በኋላ ለእኔና ለኮ/ል መርሻ መገናኛ ሰጡን፤ ለክፉም፣ ለደጉም ዕብራይስጥ አስተርጓሚ እስኪያገኙ፤ የእኛ ደህንነቶች 'በዕብራይስጥ እንነጋገር' በሚል እኔ በደንብ ዕብራይስጥ መናገር እችላለሁ:: ዕውነታው፣ 'እንደጠረጠርነው ደህንነቶች ሴት ሰላዮችን መድበዋል፤ እናንተ ተከተሉን፤ 'ቁሙ' የምንላችሁ ቦታ ትቆማላችሁ፤ ሌላ መኪና አዘጋጅተናል' አሉን፤ ከሒልተን በመርሻ መኪና መነቃነቅ ስንጀምር ሌላ መኪና ተከተለን፤ እስራኤሎች በያዝነው መገናኛ፣ 'እንግዶች እንዳሉ እያየህ ነው ወይ?' በማለት የሚከታተለን አካል እንዳለ ገለፁልኝ::

ያኔ እንደ ሾፌር ሆኖ መኪና እየነዳ ይሄን ሁሉ የሚሠራው የእስራኤል ጦር ም/ኤታማዦር ጄኔራል አምኖን የሚባል ሰው ነው:: እነሱ ፊት ለፊት ሄዱ፤ እኛ ወደ ላይ አራት ኪሎ በመውጣት በቤተ መንግሥትና በአራት ኪሎ መሀል ትንሽ ጨዋታ ተጫውተን፣ ሀሳባቸውን ለሁለት ከከፈልን በኋላ፤ እንዳመለጥናቸው ሲገባን፣ 'እነሱ ወደ ቦሌ የሚሄዱት በመስቀል አደባባይ አድርገው ነው' ብለን ስለገመትን እኛ በዑራኤል በኩል እንድንሄድ እስራኤሎች ሀሳብ አቅርበው በዚያ ስንሄድ፣ ቀድሞ ቦርቸሌ የሚባለው ቦታ ስንደርስ ሌላ የሚጠብቀን መኪና ስለ ነበር፤ ከሦስቱ ላንድ ክሩዘር መኪናዎች መካከለኛው ውስጥ ገባን:: እዚያ መኪና ውስጥ ሾፌር ሆኖ ይህንን ኦፕሬሽን የሚመራው የእስራኤል ጦር ም/ጠቅላይ ኤታማዦር ሹም ነው::

በዚህ መልክ ወደ ኤርፖርት ስንሄድ የእስራኤሎች ዋናው ቺፍ ኦፍ ስታፍ በሬድዮ አማካይነት፣ 'የእኛ አውሮፕላን የቆመው ቪአይፒ (VIP) ቦታ ላይ ነው የምንወጣውም በቪአይፒ ነው፤ ግን በአሁኑ ሰዓት ሁለት እንግዶች ኤርፖርት አሉ:: አንደኛው ተስፋዬ ዲንቃ ለንደን ለድርድር ለመሄድ ጋዜጣዊ መግለጫ እየሰጠ ነው፤ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ተስፋዬ ታደሰ ለኦኤዩ (OAU) ስብሰባ ናይጄሪያ ለመሄድ ጋዜጣዊ መግለጫ እየሰጠ ነው፤ እነሱን ለመሸኘት የእናንተ ባለሥልጣኖች በሙሉ እዚህ ናቸው፤ አንተ በዚህ በኩል ብትመጣ፣ ሰዎችህ ይተናኮሉሃልና ምን ይሻላል?' ሲለኝ፣ 'ምን አማራጭ አለኝ እንግዲህ፤' ብዬ ግራ በተጋባሁበት ሰዓት 'ሀንጋር' የሚባል ቦታ ነበር፤ እዚያ ኤርፖርት ውስጥ:: እዚያ ሲዋን ሰርቲ የሚባል አውሮፕላን እነሱ ለዕዝ ማስተባበሪያ አድርገው የሚገለገሉበት፤ ስፔር ፓርት፣ የጦር መሣሪያዎች፣ ቦንብና ጥይቶች ጭኖ የቆየ ስለነበር፤ 'በእሱ ብትሄዱስ?' ሲሉኝ፤ 'እንኳን በእሱ በአህያም ቢሆን ለመሄድ ዝግጁ ነኝ' የሚል ምላሽ ሰጠኋቸው::

**ግዮን፡- ከሀገር የወጡት በዚህ የእስራኤሎች የጦር መሣሪያ መጫኛ አውሮፕላን ተሳፍረው ነው ማለት ነው?**

**አምባሳደር ካሳ፡-** ምን ምርጫ አለኝ ታዲያ? ይሄ ራሱ የማይገኝ ዕድል እኮ ነው:: ሀንጋር ወደተባለው ኤርፖርት ግቢ ውስጥ ባለው ቦታ ስንገባ፤ 'ቁሙ፤ ወዴት ነው?' የሚል ሰው የለም:: አውሮፕላን ሜዳውንም የሚጠብቅም የለም:: ግን እንዲሁ በአጋጣሚ እንዳንታይ በሚል፤ የእስራኤል ወታደሮች ግራ ቀኝ አሰልፈው በእነሱ መሃል አውሮፕላን ውስጥ እንድንገባ አደረጉን:: ቀደም ሲል እንደገለጽኩት አውሮፕላኑ በወታደራዊ ቁሳቁስ ተሞልቷል፤ የወታደር አልጋ የመሰለ ሸራ አለ፤ እሱን አወረዱልንና ተቀምጠን ለመሄድ ስንጋጅ አውሮፕላኑ አልነሣ አለ፤ ኋላ መለስ ብዬ ሳስበው ይገርመኛል፤ በጣም ፈታኝ ጊዜ ነበር:: ተስፋዬ ዲንቃና ተስፋዬ ታደሰ እስኪሄዱ፣ እስራኤሎችም በሌላ በረራ እስኪሄዱ፤ የእኛ አውሮፕላን የኮምዩኒኬሽን አውሮፕላን ስለሆነ ፓይለቱንና የኮምዩኒኬሽኑ ሰዎች አንድ አንድ ጠርሙስ ውሃ ሰጡንና ክፍላቸው ውስጥ ገብተው ዘግተው ሲቀመጡ ጭንቀታችን የበለጠ በረታ::

**ግዮን፡- በዚያች የመጨረሻ ፈታኝ ሰዓት እርስዎም ሆኑ ኮ/ል መርሻ የነበራችሁ ስሜት ምን ይመስላል?**

**አምባሳደር ካሳ፡-** አውሮፕላን ውስጥ ቁጭ ያልነው መርሻና እኔ ብቻ ነን፤ ከአብራሪዎች ሌላ ተጨማሪ ተሳፋሪ አልነበረም:: ያኔ 'በቃ ለመውጣት ማሰባችን ተነቅቶ ሊይዙን ነው፤ አውርዷቸው፣ አናወርድም ጭቅጭቅ ላይ ናቸው' የሚል ግምት ውስጥ ገባን:: እኛም፣ 'ተይዘን ከምንዋረድ እርስ በርሳችን እንገዳደል' በሚል ሀሳብ ተስማማን፤ እኔና መርሻ ሁለታችንም ሽጉጦቻችንን አወጣን፤ ከአሁን አሁን 'ውረዱ' ለማለት ሲያንኳኩ፤ 'መጀመሪያ ሊይዙን የሚመጡትን አንለቃቸውም' አልን:: እኔ በብሪፍ ኬዝ የያዝኋት ሚኒ ኡዚ ነበረችኝ፤ እሷንም አዘጋጅቻለሁ:: ያንን ስናስተካክል አውሮፕላኑ ተንቀሳቀሰ፤ ማመን አልቻልንም:: ወደ ማኮብኮቢያው ሄደ፤ ከዚያ ሰማይ ላይ ወጣ::

እኔ ያኔም ቢሆን በእግዚአብሔር አምናለሁ፤ በአደባባይ ይህ ዓይነቱ ነገር ባይገለጽም፣ ከቤተ ክርስቲያን አልለይም ነበር:: ጸሎት እወዳለሁ፤ ልክ አውሮፕላኑ መሬት ሲለቅ መጀመሪያ ያደረግሁት አውሮፕላኑ ውስጥ ተንበርክኬ መጸለይ ነው፤ እግዚአብሔርን አመስግኜ ዞር ስል አጠገቤ መርሻም ተደፍቷል:: መርሻ ለእኔ ድብን ያለ ኮሚኒስት

ቀሪውን በገጽ 26 ይመልከቱ

## ብአዴን በትግርኛ . . . *ከገጽ 11 የዞረ*

ሰብስቦ ይዟቸው የገባቸው ልጆች ዕድሜ ቢያንስ በዐሥር ዓመት ተቃጥሏል:: ክሬም የሆነውን የወጣትነት ዕድሜያቸውን ስለኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን ነፃነት ሰውተዋል። የእነዚህ በረሃ የቆዩት የድርጅቱ ታጋዮች ዕድሜ፣ 'አልተቃጠለም' የምንለው፤ ግንቦት ሠባት ራሱን የሚመጥን ድርድር ከመንግሥት ጋር ቢያደርግ ነበር:: አደራዳሪ ተቀምጦ፣ የሁሉም ድርጅት ተወካዮች ሀሳባቸውን በግልፅ አስቀምጠው ከተማመኑ በኂላ ነበር የአውሮፕላን ትኬት መቁረጥ የነበረባቸው::

አሁን ግን እየሆነ ያለው ያ አይደለም:: አቶ አንዳርጋቸው ፅጌ ከእስር ቤት ሲፈታ ጠ/ሚኒስትር ዐቢይ በቤተ መንግሥት ጋብዘው አነጋግረውታል:: ይሄ በሰውኛ አረዳድ 'እንኳን ተፈታህ' ለማለት እንጂ ድርድር አይደለም:: እኔ እስከማውቀው ድረስ አሜሪካ ውስጥ በእነ ፕ/ር ብርሃኑና ጠ/ሚኒስትር ዐቢይ መሀል ተደረገ የተባለው ውይይት ነው እንጂ ድርድር አይደለም:: ከዚህ የተሻለ መረጃ በእናንተ በኩል ካላችሁ ልታርሙኝ ትችላላችሁ:: ለፖለቲካ ፓርቲ ውይይት ዋጋ የለውም፤ ድርድር ነው ወሳኙ:: በአቡነ ማትያስ እና በአቡነ መርቆሬዎስ የሚመራው ሲኖዶስን ስምምነት እንኳ ብናይ ያደራደረው መንግሥት ነው:: መንግሥትን ወደሚመለከተው ዋና ጉዳይ ስንመጣ ግን አደራዳሪውም፣ ተደራዳሪውም ራሱ መንግሥት ሆኖ እናገኘዋለን::

ድርጅቶች ሀገር ውስጥ ከገቡና ሠራዊቱ ከተበተነ በኂላ (የሻዕቢያን አሻጥር ሳንረሳ ማለቴ ነው) ኢህአዴግ፣ 'እኔ የምከተለው መንገድ የተለመደውን ነው' ቢል ምንድን ነው ዋስትናቸው? ማነው ምስክራቸው? ይሄ አሳሳቢ ነው:: ግንቦት ሠባት የፖለቲካ ቁማር እንዳይበላ ያሰጋኛል። ከ1983ቱ የኦነግ ታሪክ መማር ብልህነት ነው። ሠራዊቱ ካምፕ ከገባም ሆነ መሣሪያውን አውርዶ ከተበተነ በኂላ፤ ኢህአዴግን በሚገባው ቋንቋ መልሶ ማናገር የሚቻል አይደለም። አሁንም ጊዜው አልረፈደም። ኢህአዴግ እንደ ጌታ ከሚያያቸው የምዕራብ ሀገራት አንዱ በአደራዳሪነት ቢሳተፍ ጠቃሚ ነው ብዬ አስባለሁ::

**ግዮን፡- ስለዚህ አካሄዳቸውና አመጣጣቸው ጥፋት ነው?**

**ተመስገን፡-** 'ጥፋት ነው፣ ወይስ ጥፋት አይደለም' የሚለውን ለድርጅቶቹ እንተወውና፤ እኔ ላነሣ የፈለግሁት የተደረገው ድርድር ሳይሆን፣ ውይይት ነው የሚለውን ነው::

***ግዮን፡- ጠ/ሚኒስትሩ በተለያዩ መድረኮች ደግመው ደጋግመው መደመርን አስተጋብተዋል:: መደመርን አንተ እንዴት አየኸው?***

**ተመስገን፡-** በነገራችን ላይ ጠ/ሚኒስትር ዐቢይ አሁን ላለችው ኢትዮጵያ ትክክለኛው ሰው ናቸው ብዬ አምናለሁ:: እየፈራረሰች ባለች ኢትዮጵያ ላይ፣ የዘረኝነት ጠርዝ ከግራና ቀኝ እንደ ማዕበል በሚያላትማት ሀገር ላይ፣ ማንም የኪቦርድ አርበኛ ተነስቶ 'መገንጠል እንችል ነበር' እያለ በሚፎክርባት ሀገር ላይ፣ ሕይወትን ሊያሳጣ የሚችል አደጋን ተጋፍጠው፤ የሥልጣን ኃይሉን በሴራ ፖለቲካ ከተቀባው ከህወሓት ላይ ነጥቀው ሀገሪቱን ለማረጋጋት የተንቀሳቀሱበት ሂደት ተገቢና ሊደገፍ የሚገባው ነው ብዬ አምናለሁ::

እዚህ ላይ 'ለውጥን እንደግፍ ዴሞክራሲን እናበርታ' በሚል መሪ ቃል አዲስ አበባ ላይ የተካሄደው የሰኔ 16ቱ የድጋፍ ሰልፍ 'መደመር' ከሚለው መፈክር ይልቅ፣ ጠ/ሚ ዐቢይ ከተጠላው የህወሓት አስተዳደር በተቃራኒ ቆመው ከኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል ጎን ከመሰለፋቸው ጋር የሚያያዝ ይመስለኛል። እነአቶ ደመቀ፣ አቶ ለማና ገዱ አንዳርጋቸውም የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል ውጤቶች ናቸው:: እነሱ የትግሉ መሪ ሆነው ቢወጡም ድጋፍ የተሰጠው በግል ለእነሱ ሳይሆን ለትግሉ ነው:: መደመር ሌላ ጉዳይ ነው፤ መደመር አውራ ፓርቲ መፍጠር ነው? መጠርነፍ ነው? ወይስ ምንድን ነው? ይሄ አልተብራራም:: እኔ መደመርን የማየው መንግሥቱ ኃ/ማርያም ፍልስፍናችን 'ኢትዮጵያ ትቅደም ነው' እንዳለው መፈክር አድርጌ ነው፤ እናም የጠ/ሚኒስትሩም መደመር መፈክር ከሆነ እሰየው፤ ከመፈክር አልፎ ፓርቲዎችን እያሸፈትክ ወደ ራስህ የምትቀላቀልበት ከሆነ ግን አደገኛ አካሄድ ነው፤ አግባብም አይደለም:: ይህም ሆኖ በተለያዩ ክልሎች ለጠ/ሚኒስትሩ የተደረገው የድጋፍ ሠልፍ ተገቢ ነው:: ምክንያቱም ህወሓት በፖለቲካው ላይ ብቻ ሳይሆን፤ በኢኮኖሚው ውስጥም የዝሆን እግርና የአንበሳ ጡንቻ ይዞ ቆይቷል:: ያንን ኃይልና ጉልበት ቄጤማ ለማድረግ፤ ቁርጠኝነትንና ብልህነትን የሚጠይቅ ጥበብ ነው:: የድጋፍ ሰልፎቹ የእዚህ ውጤት ምስጋና ናቸው::

***ግዮን፡- ጠ/ሚኒስትር ዐቢይ በአሜሪካ ያደረጉት ጉብኝትና ውይይት የአንድነት መንፈስ የተንፀባረቀበት ነበር፤ የተደረገላቸውን ትልቅ አቀባበልስ እንዴት አየኸው?***

**ተመስገን፡-** የአሜሪካው አቀባበል የሰኔ አስራ ስድስቱ የድጋፍ ሰልፍ ተቀጥላ ነው:: እኔ እስከማውቀው ድረስ፣ እነ አቶ መለስ ዜናዊ አሜሪካ በሄዱ ቁጥር፤ የገማ እንቁላል እና የቦካ ቲማቲም ሲወረወርባቸው ነው፤ ዛሬ ያ ቀርቶ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከአሜሪካ ጉዟቸው 'እንወድሀለን፣ የለውጥ ሐሳብህን እንደግፋለን፤ ኢትዮጵያ ውስጥ ለምታመጣው ለውጥ ከጎንህ እንቆማለን' የሚል ድጋፍ ነው ያገኙት:: ስለዚህ በአሜሪካ በተለያዩ ግዛቶች የተገኘው ሕዝባዊ ድጋፍና የፖለቲካ ውጤት፣ ከሰኔ 16ቱ የድጋፍ ሰልፍ ተቀጥላነት የመነጨ ነው::

***ግዮን፡- የአማራ ክልል ፕሬዝዳንት ገዱ አንዳርጋቸው፣ "የወልቃይት ጉዳይ ወደ ግራ፣ ወደ ቀኝ፣ ወደ ፊትና ወደ ኂላም እያየን ሊተወን አልቻለም፤ ስለዚህ ከአሁን በኂላ ወደ ፊት ነው የምንሄደው፤ ጥያቄዎቹንም እንመልሳለን" ማለታቸውንስ እንዴት አየኸው?***

**ተመስገን፡-** አሁን ያልኸውን የአቶ ገዱ ንግግር አልሰማሁም። ግን ወደ ፊት እንሄዳለን ካሉ ጥሩ ነው፤ ወደ ግራና ወደ ቀኝ ከሆነ ግን እስከ ዛሬ የነበረው ዓይነት ዘጭ እንቦጭ ነው የሚሆነው::

ከዚህ ቀደም ከኦህዴድ አመራሮች መሀል በኦሮሞ ሕዝብ አንድም የሚሞገስና የሚከበር አመራር አልነበረም:: እነሙክታር ከድርና አስቴር ማሞ ድረስ የነበሩ የአመራር አባላት የኦሮሞን ሕዝብ አሳልፈው የሸጡ ይሁዳ ተብለው ሲወገዙ ነበር የምንሰማው:: አሁን እነ ጠ/ሚ ዐቢይ መጡና ያንን ቀየሩት፤ የኦሮሞ ሕዝብም ከጎናቸው ቆመ::

ወደ አማራ ክልል ስንሄድ የለውጡ እንቅስቃሴ እስከተጀመረበት ድረስ የነበረው ብአዴን፣ በትግርኛ እያሰበ በአማርኛ የሚያስተዳድር የህወሓት የአማርኛ ክንፍ ነበር:: አሁን እነ ገዱ አንዳርጋቸው፣ 'ክንፍ አንሆንም፤ የሕዝብ አገልጋይ እንጂ' ብለው እንደተነሡ ምልክቶች እየታዩ ነው::

ወደ ጥያቄህ ስመጣ፣ 'የወልቃት መሬት የእኔ ነው' የሚለው የአማራው ሕዝብ በጉልበት ነው የተነጠቀው:: እነ ደብረ ጽዮን 'ሕገ መንግሥቱ የፈታው ነው'፣ ምናምን እያሉ የሚሸሹት ነገር አይሠራም:: 'ወልቃይት፣ ኮረም፣ አላማጣ በተስፋፊ የመሬት ረሀብተኞች ተወሰዱብኝ' የሚለው የአማራ ሕዝብ፤ አሁን ድረስ ሥራ ላይ እየዋለ ያለው ሕገ መንግሥት ሲወጣ አንድም ውክልና አልነበረውም፤ በጉዳዩ ላይ አልተከራከረም፣ አልተነጋገረም:: ስለዚህ መሬቱን ቆርሶ ወደ ትግራይ ላሻገረበት የህወሓት ማኒፌስቶ ይሁንታ መስጠት አይጠበቅበትም::

ሁለተኛ በ1983 ዓ.ም ወያኔ ሥልጣን እስኪይዝ ድረስ ወልቃይት በጎንደር ክ/ሀገር፣ ኮረምና አላማጣ ደግሞ በወሎ ክ/ሀገር ሥር የነበሩ ናቸው:: አሁን ሞት እምቢ ብሏቸው በሕይወት ያሉት እነ ስብሐት ነጋና አባይ ፀሀዬም ቢሆኑ፤ አራተኛ ክፍል ላይ የተማሩትን የህብረተሰብ ትምህርት ካርታ ይረሱታል ብዬ አላስብም:: የትግራይ፣ የጎንደር፣ የወሎ፣ የወለጋ ወዘተ ክ/ሀገር እያለ ካርታው በግልጽ ያስቀመጣቸው ቦታዎች አሉ:: ያንን መሬት ነጥቀው ነው ወደ ትግራይ የወሰዱት፤ ተወያይተው፣ ተነጋግረው፣ በማስረጃ አሳምነው አይደለም:: ጉዳዩ በታሪካዊ ሰነድ ሳይሆን፤ በፖለቲካዊ ውሳኔ የተፈፀመ ነበር።


አማራው በዚያ ክርክር ላይ ተሳትፎ በባህል፣ በታሪክና በተለያዩ ማስረጃዎች ተሸንፎ ቢሆን እንኳን፤ እሰየው ይባል ነበር:: ግን በህወሓት ማንአህሎኝነት ብቻ ነው መሬቱ የተነጠቀው:: ብአዴንም ከዚህ በኂላ የሚመዘነው በመልካም አስተዳደር ብቻ አይደለም፤ የሚመዘነው የህወሓት አሽከር ባለመሆን ብቻ አይደለም:: ተስፋፊነትና የመሬት ረሃብ ስሜት የወለደውን ኢ-ፍትሐዊ የሆነ የክልል ሽንሸና እና የመሬት ዘረፋ ወደ ነበረበት እንዲመለስ በሚያደርገው ትግል ነው በዋናነት ሊመዘን የሚገባው:: ምናልባት ይሄን ብአዴን ብቻውን መወጣት አይችል ይሆናል፤ ግን ለእዚህ ጥያቄ ሙሉውን አማራና ሌሎች የዴሞክራሲና የፍትሕ ወዳጅ የሆኑትን አጋር አካላትን በሙሉ ከጎኑ ማሳለፍ አለበት ብዬ አምናለሁ፤ ይሄ ጥያቄ የፍትሕና የሕግ ጥያቄ ነው:: የትኛውም የፍትሕ ተቋም የሕግ ጥያቄ ሲነሣበት መቆም ያለበት ማስረጃ፣ መረጃ እና እውነትን ከያዘው ጎን ነው:: ብሔርና ጎጥን ለጊዜው ኂላ ኪስህ ትከታለህ:: ስለዚህ ብአዴን ትልቅ ፈተና ይጠብቀዋል::

ደግነቱ አሁን የጉዳዩ ባለቤት ሕዝቡ ለእንደዚህ ዓይነት ጥያቄዎች ንቁ ስለሆነ፤ ከድርጅቱ ጎን ቆሞ ይታገላል። የእስከዛሬው ብአዴን የሚወክለውም፣ የሚታገልልትም ማኅበራዊ መሠረት አልነበረውም። እነ አቶ በረከት ስምኦን፣ አዲሱ ለገሠ፣ ታምራት ላይኔ ሲያሽማቅቁት፣ አናት አናቱን ሲረግጡት ነው የኖሩት:: የብአዴን ሁለተኛ ትውልድ የሆነው አቶ ዓለምነው መኮንን እንኳን፣ 'ጫማ የማታደርግ' እያለ ነበር አማራውን ሲዘልፍ የነበረው:: አሁን የመጣው የብአዴን አመራር ከሕዝብ ጎን የመቆም አዝማሚያ ስላሳየ፤ የሀገሪቷን መላ ሕዝብ አስተባብሮ ለታሪክና ለዴሞክራሲ ከሚጨነቁ ወገኖች ጋር በማበር ይህን ጥያቄ እንዲመልስ ታሪካዊ ሓላፊነት ወድቆበታል::

**ግዮን፡- በእስር ላይ ለሦስት ዓመት በመቆየትህ ከሚዲያው ርቀሃል፤ በቀጣይነት ከሥራህ አኳያ ምን እንጠብቅ?**

**ተመስገን፡-** አሁን ላይ ሆኖ የወደፊቱን እርግጠኛ ሆኖ መናገር ቢከብድም፣ በምታውቀበት የኅትመት ዘርፍ ከተለመደው አቋሜ ጋር በቅርቡ የምመጣ ይመስለኛል::

**ግዮን፡- እናመሰግናለን::**


አስማማው ኃ/ጊዮርጊስ

# ከልሒቅ እስከ ደቂቅ ከግብታዊነት ቢርቅ

ጊዜው ይራቅም ይቅረብ፣ ቁጥሩ ይብዛም ይነስ፣ ድርጊቱ በስፋት ይዘገብ ወይም ይሸፋፈን፣ ድርጊቱ መነሻም ይኑረው በዘፈቀደ ይከወን፤ ብቻ በአራቱም የሀገሪቱ አቅጣጫዎች ዘግናኝ የሆኑ ድርጊቶችን መስማቱ ማባሪያ አልተገኘለትም:: በተለይ የሻሸመኔው ሰቅጣጭ ድርጊት ብዙዎችን ያሳዘነ ሆኗል:: በዚህ ክስተት ዙሪያ ብዙ እንደመነገሩ፣ በሆነው ላይ ሳይሆን፤ ከሻሸመኔው ክስተት በፊት ሆነም በኋላ ባሉት አጠቃላይ የመንጋ ኢ-ፍትሐዊነት ድርጊቶች ዙሪያ የበኩሌን ሐሳብ መሰንዘሩን መርጬያለሁ:: እንዲህ ያለው ክስተት በጊዜ ሁሉን አቀፍ ተቋማዊ የሆነ መፍትሔ ካልተበጀለት በቀር፣ ሊያስከትል የሚችለውን ቀውስ መገመቱ ለማንም የሚያዳግት አይደለም:: ከሰሞኑ እዚህም እዚያም እየተሰሙ ያሉ ዘገባዎች በጣም ሰቅጣጭ መሆናቸውን ተከትሎ፤ አንዳንዶች እንዲህ አይነቱ ድርጊት መከወን የተጀመረው አንፃራዊው ነፃነት በአዲሱ አመራር አማካኝነት ከመጣ በኋላ እንደሆነ አድርገው ሲጽፉ ታዝቤያለሁ:: ይህ አይነቱ አጠቃላይ ድምዳሜ በፍጹም ምክንያታዊ ያልሆነ ብቻ ሳይሆን፤ አርቆ አስተዋይነት የተጓደለበትና የተቻኮለ ድምዳሜ ነው:: እዚህ ላይ የጠ/ሚኒስትሩ የአሜሪካ ጉዞ አባል የነበረው ዲ/ን ዳንኤል ሳይቀር፣ “ነጻነት ሰውን አውሬ ካደረገው፡ ባርነት ለዘላለም ይኑር” ማለቱን፤ ብዙዎች ሲቀባበሉት በማየቴ በጣም አዝኛለሁ:: አንደኛ አንድን ከሞራል የወጣ ኢ-ሰብዓዊ ድርጊት በሌላ ኢ-ሞራላዊ ድርጊት ማረም በጭራሽ የሚመከር አይደለም:: ነፃነትም ቢሆን በበለፀጉት ሀገራት ሆነ እንደ ቦትስዋና ባሉ የአፍሪካ ሀገራት እንዳየነው የሰውን ልጅ ወደ ላቀ የሞራልም ሆነ የሥልጣኔ ደረጃ የሚያደርስ እንጂ፤ አውሬ የሚያደርግ አይደለም:: በዚያ ላይ ባርነት የሰውን ልጅ እንደሸቀጥ እንዲቆጠር የሚያደርግ እና ባለቤቱ እንዳሻው እንዲሸጠው እንዲለውጠው የሚያደርገው በመሆኑ፤ ይህ አይነቱ ዘግናኝ ድርጊት እንኳን ለዘላለም ቀርቶ፣ ለሰአታት በጭራሽ የሚመኙት አይደለም:: ከዚህ ውጪም፣ በቦታው ላይ የነበሩ ቁጥራቸው በርከት ይበል እንጂ መቶ ሚሊዮን ከሚሆነው የሀገራችን ሕዝብ አንፃር፣ እዚህ ግባ የማይባል ቁጥር ባላቸው ሰዎች የጅምላ ፍረጃ ላይ ለመድረስ መጣደፍ፤ አንድን ድርጊት ተከትሎ በሀገራችን፣ በተለይ ከልሒቅ እስከ ደቂቅ በማህበራዊ ሚዲያ የሚሰነዘሩ ሐሳቦች ምን ያህል ከስሜታዊነት ያልራቁ መሆናቸውን የሚያሳይ ነው::

## “ስም አልባው” አረመኔያዊ ድርጊት ከትናንት እስከዛሬ

በዋነኛነት “ያልሰለጠኑ ሰዎች ድርጊት” በሚል የሚገለፀው አሳፋሪው ንጹሐንን በደቦ ተጠያቂ በማድረግ፣ መንጋው ራሱን ከሳሽ እና ፈራጅ በማድረግ፣ ሌላውን ዘግናኝ በሆነ ሁኔታ ሕይወቱን እንዲያጣ ወይም ለከፋ የአካል ጉዳት እንዲዳረግ የሚያደርግበት ሕገ ወጥ ተግባር፤ የመንጋ ፍትሕ ተደርጎ በስፋት ይወሳል:: ይሁን እንጂ የድርጊቱ መጠሪያ በጭራሽ ክስተቱን የሚገልፅ አይደለም:: በመንጋ የሚወሰድ አረመኔያዊ ድርጊት፣ ፍትሕ ብሎ ነገር አያውቅም:: በመሆኑም፣ እንዲህ ያለው ድርጊት፤ በቋንቋ ተቋማት ወይም በስነ ልሳን ምሁራን አግባብ ያለው ስያሜ እስኪወጣለት ድረስ በግሌ የመንጋ ኢ-ፍትሐዊነት የሚለውን ቃል መጠቀሙን እመርጣለሁ:: የሆነው ሆኖ ይህ ስም አልባው አረመኔያዊ ድርጊት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እዚህም እዚያም መከሰቱ እሙን ይሁን እንጂ፤ ባለፉት ዓመታት እንዲህ ያለው ድርጊት በበርካታ ቦታዎች ተከናውኗል:: ለዚህ እንደማሳያ ቂሊንጦ ሳለሁ አብረውኝ የነበሩ ተከሳሾች፤ ጥፋተኛ የተባሉበትን እና በጋምቤላ ክልል በማዣንግ ዞን፣ ጎደሬ ወረዳ፣ ሜጢ ከተማ ውስጥ የተፈጠረው የተደራጀው የመንጋ ኢ-ፍትሐዊ ድርጊት ለዚህ አንዱ ማሳያ ነው:: በዚህ ያልተገባ እና ሰላማዊ ዜጎች ላይ በተወሰደ ሕገ ወጥ እርምጃ ለ79 ሰዎች ሞት፣ ለ27 ሰዎች ከፍተኛና ዝቅተኛ የአካል መጉደል፣ ከ270 ለሚልቁ መኖሪያ ቤቶች መቃጠል፣ ከ13,000 በላይ ለሚሆኑ ነዋሪዎች ከቤት ንብረታቸው እንዲፈናቀሉ መንስኤ ሆኗል::

## የሰሞነኛ የመንጋ ኢ-ፍትሃዊ እርምጃዎች

ከሦስት ዓመት በፊት ከተከሰተው በዚህ ዘግናኝ የመንጋ ኢ-ፍትሐዊ እርምጃም ሆነ ከሌሎች መሰል ድርጊቶች በመነሣት ሌሎች ሀገራት ችግሩን ለመፍታት የሞከሩበትን ብልሃት ለመረዳት በመጣር፣ በሀገራችን ያለውን ይህንኑ ችግር ለመፍታት ሁሉን አቀፍ የሆነ መፍትሄ ባለመቅረቡ፤ በሀገሪቱ በአራቱም ማዕዘን ከጅግጅጋ እስከ ቤኒሻንጉሏ አሶሳ፣ ከሻሸመኔ እስከ ድሬ፣ ከባህር ዳር እስከ አዲግራት የተሰሙት አሳዛኝ ዜናዎች ይህ ዓይነቱ ያልተገባ ድርጊት መቋጫ ሊበጅለት እንደሚገባ አይነተኛ ማሳያ ናቸው::

በተለይ ከመንጋው ኢ-ፍትሐዊ ድርጊት ባልተናነሰ መልኩ በኢትዮጵያ ሶማሌ እና በኦሮሚያ ፖሊስ መካከል የሚደረገው ግጭት የበለጠ ለማገርሸቱ ያለፉት ሳምንታት አሳዛኝ እልቂቶች ሁነኛ ማሳያ ናቸው:: በተለይ የሻሸመኔው አሳዛኝ ክስተት በተፈፀመበት ወቅት፤ “የሶማሌ ክልል ልዩ ኃይል ፈጽሞታል” በተባለው ጥቃት፣ በምሥራቅ ሐረርጌ 37 ሰዎች ሲገደሉ፤ 44 ሰዎች ጉዳት ደርሶባቸዋል:: በርግጥ ይህንን ጥቃት ከመንጋ ኢ-ፍትሐዊነት እርምጃ የበለጠ አስከፊ የሚያደርገው፤ ሰላማዊ ዜጎች ሊጠብቃቸው በተገባ ኃይል ሕይወታቸውን መነጠቃቸው ነው:: አቶ መሐመድ ሲራጅ፣ “በቤት ውስጥ ተቀምጠን ባለንበት ወቅት የሶማሌ ልዩ ፖሊሶች በር ገንጥለው ገቡብን። ባለቤቴን፣ ልጄንና የሁለት ዓመት የጎረቤት ልጅ አጠገቤ ገደሉ’’ ሲሉ የደረሰባቸውን ጉዳት ለቢቢሲ የገለፁበት ሁኔታ፤ የጥቃቱን ስፋት በግልፅ የሚያሳይ ነው:: በተለይም ሴቶች፣ ዓይነ ስውር አዛውንቶች እና ከአንድ ዓመት በታች የሆኑ ሕፃናት ሳይቀሩ በጥቃቱ “ተገድለዋል” መባሉ የችግሩን አሳሳቢነት በስፋት የሚጠቁም ነው::

ከዚህ ጥቃት በፊትም፣ በሞያሌ የኦሮሚያ ፖሊስ በሶማሌዎች ላይ “አድርሶታል” በተባለው ጥቃት፤ 50 ሰላማዊ ዜጎች ተገድለው፣ በመቶዎች ወደ ኬኒያ ተሰደው፣ ከፍተኛ የሆነ ▶

ንብረት ወድሟል:: አንድ እናት አራት ልጆቿን በአንድ ቀን ያጣችበት ይህ ዘግናኝ ክስተት፣ በተገቢው መንገድ ባለመዘገቡ፤ ከፍተኛ ቁጣን በኢትዮ-ሶማሌ አራማጆች ዘንድ መፍጠሩ አልቀረም:: የዚህ አይነቱ ጥቃት ለጅግጅጋው የደቦ የጭካኔ እርምጃ እንደሁነኛ መቀስቀሻ በአብዲ ኢሌ ኃይሎች መዋሉ ይታወቃል:: አሳዛኙ ነገር ግን ይህንን ሊጠብቋቸው በሚገቡባ ፖሊሶች ከሁለቱም ወገን እየደረሰ ያለውን ሕፃን አዛውንትን ያልለየ ግድያ ለማስቆም፣ ጠንካራ እርምጃ አለመወሰዱ ነው::

## ከግብታዊነት ወደ ለውጥ አራማጅነት

በመንጋ እሳቤ የሚከሰት ግድያም ሆነ ሌላ ክፉ ክስተት ሲሰማና ሲታይ፤ በግብታዊነት ምሬትን ብቻ መሰንዘሩ ዋጋ የለውም:: ከዚህ ይልቅ እንደ ክስተቱ ሁኔታ የአጭር እና የረዥም ጊዜ መፍትሔ ለመሻት መረባረቡ እና የሚመለከተውን አካል መጠየቁ የላቀ ጠቀሜታ አለው:: ከዚህ ውጪ አንድን ክስተት ብቻ ነጥሎ፣ በተለየ ሁኔታ ማራገቡ ወደ መፍትሔ አያደርስም:: እውነቱን ለመናገር በደቦ ዜጎችን የመግደሉ፣ የማሳደዱ ተግባር ድርጊቱን የሚገልፅ ስያሜ እንኳ የለውም:: ለምሳሌ ሌብነት በሕግ ድርጊቱ ጥፋት መሆኑ ታውቆ ማንም ቢሆን ከዚህ አይነቱ ድርጊት እንዲርቅ የሕግ ማዕቀፍ ውስጥ ተገቢው ቅጣት ተቀምጦለት ይገኛል:: ይህ የደቦ አረመኔያዊ ተግባር ግን፣ የሰውን ሕይወት የሚነጥቅ ዘግናኝ ተግባር ቢሆንም፤ በድንገት የሚፈጠረውን እንዲህ ያለውን ወንጀል ለመግታት፣ እስካሁን ድረስ ምንም የተወሰደ ተቋማዊ እርምጃ የለም:: የመንጋው ኢ-ፍትሐዊ የሆነ ተግባር ከጎረቤታችን ኬንያ እስከ ልዕለ ኃያሏ አሜሪካ፣ ከማንዴላዋ ደቡብ አፍሪካ እስከ ፑቲኗ ራሺያ ድረስ በተለያዩ ምክንያቶች፣ "የደቦ ጥቃቶች" ይፈጸማሉ:: ይሁን እንጂ፣ ሀገራቱ በዚህ ሕገ ወጥ ድርጊት የተነሣ የደረሰውን በደል ከግምት በማስገባት፣ ተቋማዊ መፍትሔ አስቀምጠውለታል:: በመሆኑም ድርጊቱ ልክ በወንጀል ሕግ እንደተቀመጡ ማናቸውም ጥፋቶች ተለይቶ የታወቀ በመሆኑ፤ እንዲሁም በዚህ ያልተገባ ድርጊት ላይ ሰፊ ግንዛቤ የሚፈጥሩ ፕሮግራሞችም ሆነ የቅስቀሳ ሥራዎች በመከናወናቸው፤ እንዲህ ያለውን ዘግናኝ ተግባር ለመቀነስ በቅተዋል:: ኬንያ እንኳን እንዲህ አይነቱን ድርጊት በየዓመቱ ለመቆጣጠር በከፍተኛ ደረጃ ከመንቀሳቀሷ ባሻገር፤ የዚህን አይነት የደቦ ጥቃት ትመዘግባለች::

የእኛው ሀገር ዋነኛ ችግርም ለክስተቱ ተቋማዊ መፍትሔ ለመስጠት አለመቻሉ ብቻ ሳይሆን፤ ድርጊቱን በስፋት በማውገዝና ግንዛቤ በሚፈጥር መልኩ ለሕዝቡ በማቅረብ ፋንታ፤ "እከሌን አይወክልም" በሚል ሽፋን ጥፋቱ አላግባብ ተሸፋፍኖ ይቀራል:: እርቃኑን ያለግብሩ የተሰቀለው የወንድማችን ማንነት፣ የእናቱ ሐዘን፣ የቤተሰቡ ምሬት፤ ምን አልባትም፣ የትዳር አጋሩ ወይም የልጆቹ ሁኔታ ቢቀርብ፤ ይህንን አረመኔያዊ ድርጊት የፈፀሙትን ከማሳፈር ባለፈ፣ ሌሎች ወገኖችም በዚህ አይነቱ የመንጋ አረመኔያዊ ተግባር ላለመሳተፍ ቆም ብለው እንዲያስቡ መንገድ በከፈተ ነበር:: በተለይም ድርጊቱን የፈፀሙትን ሰዎች ለሕግ ማቅረብ፣ ተከታትሎ መዘገብ እና የሚተላለፍባቸውን ውሳኔ ማሳወቅ ሌላኛው የዚህን አይነቱን ድርጊት መግቻ መንገድ ነው:: ይሁንና ከዚህ በተቃራኒው፣ "ሰዎቹ ተይዘዋል" ወይም "በጉዳዩ ላይ ምርመራ እየተከናወነ ነው" የሚል ጎደሎ ሐሳብ ከመሰንዘር ባለፈ፤ በተከታታይ ሂደቱን ተከታትሎ፣ ውጤቱን ለሕዝቡ ይፋ የማድረግ ባህል አለመኖሩ ድርጊቱን በየጊዜው እዚህም እዚያም ከመከሰት ለመግታት የሚደረገውን ጥረት ዋጋ ቢስ አድርጎታል::

ዘግናኝ የሆነውን የደቦ ጥቃት ተከትሎም ከልሒቅ እስከ ደቂቅ ከሚሰጠው ስሜታዊ አስተያየት ባለፈ፣ "ይህ ጉዳይ እዚህ ላይ መገታት ይኖርበታል" የሚል ተነሳሽነትን በመውሰድ፤ መንግሥት ለጉዳዩ ትኩረት እንዲሰጥና ተቋማዊ የሆነ መፍትሔ እንዲያመጣ ያለመ መንግሥታዊ ያልሆነ ተቋም ወይም መደበኛ ያልሆነ የዜጎች የውይይት መድረክ መፈጠር አለመቻሉ፤ መፍትሔውን እውን ለማድረግ የሚሄድበትን ርቀት ጠቋሚ ነው:: በተለይ ሚዲያው ሊጫወት የሚችለውን ሚና በሚገባ እንዳይጫወት መሸበቡ፤ የራሱ የሆነ ሰፊ አሉታዊ ተፅዕኖን መጫወቱ አልቀረም::

## በመንጋ የሚመሩ - "ሰዎች በጎች፣ ቴሌቪዥን እረኛቸው ነው"

ታዋቂዋ ደራሲ ጄሲ ስኮት በመንጋ የሚመሩ እና የማያገናዝቡ ሰዎችን በተመለከተ፤ "ሰዎች በጎች፣ ቴሌቪዥን እረኛ ነው" የሚለውን መከራከሪያ ያወሳችው፤ የተነገራቸውን በማድመጥ ብቻ ለደቦ ፍርድ የሚጣደፉትን ወገኖች ለመግለፅ ነበር:: እንግሊዛዊው ፈላስፋ፣ የሥነ አመክንዮ ሊቅ እና ሐያሲ በርትራንድ ረስል፣ "የጋርዮሽ ፍርሃት መንጋዊ ስሜትን ይቀሰቅሳል:: የመንጋው አባል ያልሆኑ ወገኖች ላይም ጭካኔያዊ ድርጊት እንዲፈጠርባቸው ያደርጋል" የሚል ሐሳብ ያንጸባረቀ ሲሆን፤ በሀገራችን አንዳንድ ቦታዎች የተወሰዱት የደቦ ድንጋይ ውርጅብኞች ተጠቂዎች፣ የመንጋው ወይም የጥቃቱ አድራሾችን ቋንቋ ተናጋሪ ቢሆኑም እንኳን፤ "ተከፍኋችሁ ለስለላ ነው የመጣችሁት" በሚል ያልተጨበጠ ፍረጃ የከፋ ጥቃት እንደደረሰባቸው ሲታወስ፤ ምን ያህል መንጋዊ እርምጃው ፈሩን እንደሳተ መገንዘብ ይቻላል::

ቻርልስ ማኬይ፣ "Memoirs of Extraordinary Popular Delusions" በተሰኘ ሥራው፤ "በመንጋ እሳቤ የሚመሩ ሰዎች በደቦ ያብዳሉ፣ የሚሠሩትን አያውቁም፤ ወደ ትክክለኛ ማንነታቸው የሚመለሱትም ከመንጋው ተነጥለው ብቻቸውን የተከሰተውን ነገር ሲያስቡ ብቻ ነው" ሲል የደቦ እብደት መቆሚያን ይጠቁማል:: አሳዛኙ ነገር ግን የደቦ እብደቱ ከስሕተት በኋላ ቢያበቃም፣ መተኪያ የሌለው ሕይወት መቅጠፉ ነው:: "Impacts of Mob [In]Justice on the Rule of Law in Ghana" በተሰኘው ጥናት መሠረት፤ ለመንጋ ኢ-ፍትሐዊ ተግባር የሚያነሣሡ ነገሮች ያልተጠበቀ ውድቀት፣ የሕዝቦች በመንግሥት የፍትሕ እና የሕግ ተቋማት መተማመን ማጣት፣ የመንጋው ኃይል ጉልበት ማግኘት ዋነኞቹ ስለመሆኑ ያወሳል:: ይህ ድምዳሜ በተወሰነ ደረጃም በሀገራችን ለሚስተዋለው የመንጋ ፍትሕ መነሻ ሊሆን ቢችልም፤ ሀገራችን የተለየ ገፅታ ያላት እንደመሆኑ፣ ይህንኑ ልዩ ገፅታ ከግንዛቤ ያስገባ ሰፊ ጥናት ማከናወን የመፍትሔ ሐሳቦችን ለማመንጨት የሚመለከታቸው አካላት ትልቁ የቤት ሥራ መሆኑን መረዳት ይኖርባቸዋል::

የሁኔታውን አሳሳቢነት ከግንዛቤ በማስገባት፣ በተለይ ድርጊቱ እየሰፋ እንጂ እየቀነሰ ባለመሄዱ፤ ይህንን ወደ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የመሸጋገሪያ ወቅት፣ ወዳላስፈላጊ እልቂት ከማምራት ለመታደግና ከምንም በላይ የንፁሐንን ሕይወት ለመታደግ፤ በተለይም የማንነት (የብሔር) ፖለቲካውን እንዲጦዝ በማድረግ፣ መንጋውን መሾፈሩ ቀላል ስለሚያደርገው፤ ቢያንስ ዜጎችን በየትኛውም ክልል ተዘዋውረው የመኖር መብታቸውን በላቀ ደረጃ የሚያስከብር እና እዚህም እዚያም የሚታየውን የደቦ ጭፍጨፋ ለማስታገስ፤ አማራጭ የሕግ ማዕቀፍ እውን መሆን ይኖርበታል:: በተለይ በሕግ ብቻ ይህንን ድርጊት መግታቱ አዳጋች እንደመሆኑ መጠን፤ በተለይ የእምነት ተቋማት አባቶችም ሆኑ ሌሎችም ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት፤ በዚህ አስጸያፊና ከሰውነት በወጣ አረመኔያዊ ድርጊት ዙሪያ ከወጣቱ ጋር መምከር ይጠበቅባቸዋል::

የዜጎችን ደህንነት አለማስከበር ወደለየለት ሁከት እና ብጥብጥ ዜጎች ያመሩ ዘንድ የሚጋብዝ በመሆኑ፤ በተለይም በሰላም ውሎ ቤት መግባቱ፣ ቀዳሚው የሰው ልጅ ፍላጎት እንደመሆኑ፤ የተጀመረው ተስፋ ሰጪ ማሻሻያ ግቡን እንዲመታ እና ሀገሪቷን ወደላቀ ደረጃ ለማድረስ፤ ዜጎች ከመንጋ ፍርድ ተጠብቀው ኑሮዋቸውን በአግባቡ እንዲገፉ ማድረጉ ለነገ ቀጠሮ ሊሰጠው የማይገባ አንገብጋቢ ጉዳይ መሆኑን ተረድቶ፤ ለተግባራዊነቱ ከወዲሁ ተግቶ መሥራትን ይጠይቃል::

> "አንድ እናት አራት ልጆቿን በአንድ ቀን ያጣችበት ይህ ዘግናኝ ክስተት፣ በተገቢው መንገድ ባለመዘገቡ፤ ከፍተኛ ቁጣን በኢትዮ-ሶማሌ አራማጆች ዘንድ መፍጠሩ አልቀረም:: የዚህ አይነቱ ጥቃት ለጅግጅጋው የደቦ የጭካኔ እርምጃ እንደሁነኛ መቀስቀሻ በአብዲ ኢሌ ኃይሎች መዋሉ ይታወቃል:: አሳዛኙ ነገር ግን ይህንን ሊጠብቋቸው በሚገቡባ ፖሊሶች ከሁለቱም ወገን እየደረሰ ያለውን ሕፃን አዛውንትን ያልለየ ግድያ ለማስቆም፣ ጠንካራ እርምጃ አለመወሰዱ ነው



ኃይሉ አሰለፍ ገብሬ

# ኢኮኖሚያችን እና የአግልግሎቱ ዘርፍ፤

በፊውዳሉ ኢኮኖሚ ተጀምሮ በቀጣዮቹ ዘመናዊ ሥርዓቶች ስለሚዘምነውና ስለሚስፋፋው የአገልግሎት ዘርፍ፣ ከሌሎች ዘርፎች ጋር ሊኖረው ስለሚገባ ዘመናዊና ውጤታማ ግንኙነት በትክክል መረዳት ጠቃሚ ነው:: የመጀመርያው የፊውዳል አስገባሪዎች ስለነበሩ ብቻ፣ የሚገባቸውን ሳይሆን፤ በሀገራቸው ላይ ተመሥርተው የሚፈልጉትን ግብር ወደ ዜጎች የጋራ አስተዳደራዊና ልማታዊ ወጭ መቀየርና መመጠን፣ ለዜጎች ሁሉ በፍትሐዊነት ማከፋፈል፤ ገቢውን ለታለመለት ዓላማ በተገቢው ሥርዓት ኢኮኖሚው፣ አብዛኛው ዜጋ የበለጠ ውጤታማ በሚሆንበት ቅደም ተከተል በመጠቀም ሲሆን የመንግሥትን አገልግሎት ማዘመን ልንለው እንችላለን::

ሌላው ደግሞ በፊውዳሉ ሥርዓት አቆጥቁጠው የነበሩ ተጨማሪ የኢኮኖሚውን የአገልግሎት ዘርፎች ማዘመንና ማስፋፋት ነው:: የመጀመርያውን የግብርና ዘርፍ የተለያዩ ምርቶችን ወደ ገበያ የሚያደርሱ፣ ለዚህ ዘርፍ ግብዓት፣ ለአምራቹ አርሶ አደርና አርብቶ አደር መሠረታዊ ሸቀጦችን የሚያቀርቡ፣ ለዚህ ዐቢይ ተግባር ወሳኝ የሆኑ የሚዳሰሱ ወይም የማይዳሰሱ መሠረተ ልማቶችን የሚያቀርቡ፣ ከቀበሌና ከወረዳ ጀምሮ እስከዓለም አቀፍ ገበያ የሚያደርስ የኢኮኖሚውን የተለያዩና በአገልግሎት ዘርፍ የሚያጠቃልሉ ሥራዎችን በማዘመንና በማጎልበት ሁሉንም ተጠቃሚ ማድረግ ነው::

ለዘለቄታው ሁሉም ተጠቃሚ የሚሆነው አንዱን ባንዱ ላይ በመጫን ሳይሆን፤ አምራቾች፣ ምርቶቻቸውን ራሳቸው ወደ ገበያ ቢያቀርቡ፤ ወይም ሸቀጦችን፣ ግብዓቶችን ከተመረቱበት ቦታ በቀጥታ ሲገዙ የሚያገኙት ተጨማሪ ዋጋና የሚጠበቅባቸው ወጪ፤ የግዴታ ምርቶቻቸውን ወደ ገበያ ራሳቸው ሲያደርሱና ሲገዙ በሚባክነው ጊዜ፣ በዚህም ምክንያት ሳያመርቱ ከሚቀሩት ተጨማሪ የምርት ዋጋ ማነስ አለበት:: በዚህ ሁኔታ አምራቾች የአገልግሎት ዘርፉን አገልግሎት መጠቀም ይመርጣሉ፤ የጋራ ስምምነቱ መሠረት የሚቆመው በዚህ ላይ ብቻ ሲሆን፣ ከዚህ ካፈነገጠ ለሁሉም የችግር መጀመርያ ይሆናል::

በዚህ ሂደት ላይ የሁሉንም ሥራ የሚያሳልጡና ተጨማሪ አገልግሎቶችን የሚያቀርቡ ሥራዎችም ይስፋፋሉ:: የመንግሥትን አገልግሎት ጨምሮ ከግብርና እና ከማምረቻ ኢንዱስትሪው ዘርፍ ውጪ ያለውን ሥራ ሁሉ ይጠቀልላል:: ሕልውናው፣ ዓላማውና ግቡ በሁለቱ ዘርፎች፤ በመንግሥት አስተዳደር እና የሀገሪቱ ኢኮኖሚ ከውጭ ሀገር ኢኮኖሚዎች ጋር ባለው ግንኙነት ላይ የተመሠረተ ነው::

ከመንግሥት የጤና፣ የትምህርት፣ የፍትሕ፣ የአስተዳደርና ከሌሎች የመሠረተ ልማት አገልግሎቶች በተጨማሪ፤ አስመጭዎችን፣ ላኪዎችን፣ ከወረዳ ጀምሮ እስከ ሀገሪቱ መዲና ድረስ የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር ምርቶችን ገበያ የሚያሳልጡ አቀባባይ ነጋዴዎችን፣ ሥራ ተቋራጮችን፣ የሙያ አማካሪዎችንና ተቆጣጣሪዎችን፣ የፋይናንስ ተቋማትን (ባንክና ኢንሹራንስ)፣ የትራንስፖርት አገልግሎት አቅራቢዎችን፣ የሆቴልና ቱሪዝም አገልግሎት ሰጭዎችንና የሪል ስቴት ገንቢዎችን የሚያጠቃልለው ዘርፍ፤ በኢኮኖሚው ውስጥ ሁነኛ ድርሻ ቢኖረውም፣ ከብዙኃኑ ዜጎች አንፃር በጣም ጥቂቶች የሚሳተፉበት፤ እጅግ በጣም ጥቂቶች ብቻ ደግሞ ቁንጮ የሆኑበት ዘርፍ ነው:: የተወሰነ ቁጥር ላላቸው ዜጎች የሥራ ዕድል ቢፈጥሩም፣ በሀገራችን መንግሥት፣ ፓርቲ፣ ግለሰብ፣ ወይም የእነዚህ ማህበራት ባለቤቶቻቸው ናቸው::

> አሁን ብዙዎች ታሪክ አንዳንዶች ደግሞ እንደቅርስ የጥቂቶችና የቅንጦት ሆነው፤ ንግድ ተኮሩ ፖሊሲ ሁሉንም ሥራና ምርት ከባህር ማዶ የምንሸምትበትን፤ ጥቂቶችን ተጠቃሚ ብዙሃኑን ሥራ ፈትና ቦዘኔ፣ ሀገሪቱን በአጠቃላይ የውጭ ጥገኛ አድርጓል

በመካከላቸው ግን መሠረታዊ ልዩነቶች የሉም፤ የመጀመርያ ህልውናቸው፣ ቀጣይነታቸው፣ ዕድገታቸውና ኪሳራቸው ከሥልጣንና ከፖሊሲ ጋር በእጅጉ የተቆራኘ ነው:: በከተሞች ይገኛሉ፣ የሥራና የአደጋው (Business Risk) ተጋላጮች አይደሉም፣ ወይም መጠኑ እጅግ አነስተኛ ነው:: ስለዚህ ህልውናቸው ለመንግሥት ካላሠጋ፣ ከተሞዳሞዱና ከተፈቀደላቸው እያተረፉ ለመቀጠል አይቸገሩም:: በባህርያቸው አስገባሪዎች ስለሆኑ፤ ለትርፍ ብቻ እንጂ ለተቋቋሙበት ኢኮኖሚያዊ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ፋይዳ፣ ለልህቀትና ለልዩነት አይደክሙም:: በዝናብ ላይ ጥገኛ የሆነው የዚህች ሀገር ኢኮኖሚም ይነካካቸዋል እንጂ፤ ድርቅም አያደርቃቸውም፣ ዝናብም አያበሰብሳቸውም::

መንግሥት በግብርናውና በኢንዱስትሪው ዘርፍ እንዲሰማሩ ቢወተውትም፣ ከነዚህ ጮማ ከሆኑ ዘርፎች ወደሌሎች “አኛ” ወደሆኑ ዘርፎች ለመሸጋገር አይፈልጉም:: እርስ በእርስ ይደጋገፋሉ:: ከኢኮኖሚው፣ ከብዙኃኑና ከግብርናው ዘርፍ ጋር ያላቸው ግንኙነት ግን የቀጥታም ይሁን የተዘዋዋሪ በመሠረታዊ ባህርዩ ጥገኝነት ነው:: ላለፉት ሃያ ሠባት ዓመታት የኢኮኖሚ ፖሊሲያችን ንግድ ተኮር ነበር ማለት ይቻላል::

በዚህ መልኩ ተመችቷቸው ቢቆዩም፣ በተመሳሳይ ወደ ፊት ለዘለቄታው መቀጠል አይችሉም፤ የወቅቱ የኢኮኖሚ ችግር የሚያስገነዝበን ይህንን ነው:: በዚህ ጽሑፍ ከመንግሥት ባለሥልጣናት ጀምሮ የጥቂት የዘርፉን ቁንጮዎች ወቅታዊ ምኞት፣ የደረሱበትን ደረጃና ሂደቱን የሚያስገነዝበውን ቁም ነገር፤ አጠቃላይ ምሳሌ ወስደን እንመልከት::

አንድ ቀን፣ አዲስ አበባ ከተማ፣ ለቡ ቀለበት መንገድ አካባቢ፣ ድንገት የገባሁበት የቢሮና የቤት ዕቃዎች አቅራቢ የቻይናውያን ነበር:: ይህ አቅራቢ ካሉት የቤት ዕቃዎች መካከል አንድ ስፋቱ ሁለት ሜትር የሚሆን አልጋ ላይ የተለጠፈው ዋጋ ትኩረቴን ►

> **በባህርያቸው አስገባሪዎች ስለሆኑ፤ ለትርፍ ብቻ እንጂ ለተቋቋሙበት ኢኮኖሚያዊ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ፋይዳ፣ ለልህቀትና ለልዩነት አይደክሙም፡፡ በዝናብ ላይ ጥገኛ የሆነው የዚህች ሀገር ኢኮኖሚም ይነካካቸዋል እንጂ፤ ድርቅም አያደርቃቸውም፣ ዝናብም አያበሰብሳቸውም**

ሳበው፤ አላመንሁም:: ጠጋ ብዬ አየሁ፤ ጠይቄም አረጋገጥሁ፤ የአልጋው ፊክስድ ዋጋ 575,000.00 (አምስት መቶ ሰባ አምስት ሺህ ብር) ነበር:: በመዲናችን ይህን አልጋ የሚገዛ (ኢንዱስትሪ ስለሌለን) የአንድ ላኪ፣ አስመጪ፣ ወይም ሥራ ተቋራጭ፣ የመንግሥት ባለሥልጣን …ወዘተ ቤተሰብ የሥራ ዋጋ፤ ከአርሶ አደር ወይም አርብቶ አደር ቤተሰብ የሥራ ዋጋ ጋር ማነፃፀር ተገቢ ነው:: የአምራቹን አርሶ አደርና አርብቶ አደርን ወለል፣ መደብ፣ ቆጥ፣ የጠፍር አልጋ… ዋጋ ከ 10-500 ብር ከገመትነው፤ በሁለቱ መካከል ልዩነቱ፣ 1፡ ከ 57 500 ቤተሰብ ጀምሮ 1፡ ከ 1150 ቤተሰብ የሥራ ዋጋ ጋር እኩል ይሆናል::

የጥቂቶች ፍጆታ መጠን ለብዙኃኑ የተጨማሪ ምርት ዕድገትን የሚያረጋግጥ ኢንቨስትመንት የመሆን ዕድል ስለነበረው፣ በዚህ በጥቂቶችና በብዙኃኑ የተጠቃሚነት ምጣኔ ልዩነት ውስጥ ዘላቂ ዕድገት መጠበቅ ሞኝነት ነው::

ሂደቱን ስንመለከተው፣ የፊውዳሉን ጥቂት ተጠቃሚዎች በእርሻ ሰብልና በመንግሥት ተቋማት ተጠቃሚነት በቀየረው የወታደራዊው መንግሥት ሥርዓትና መጨረሻ ላይ አቆጥቁጠው በኢሕአዴግ መጀመርያ ላይ ማደግ የቻሉ፣ ከአምራቹ ገበሬ መካከል ወጥተው ኑሯቸውን በየአካባቢው የአስተዳደር ማዕከሎች፤ ሥራቸውን ደግሞ የአምራቹን ምርት ገዝቶ ለሌላ ገበያ ማቅረብ፤ አምራቹ የሚፈልገውን ሸቀጥ ደግሞ ከሌላ ገበያ በየአካባቢው ለአምራቹ ማድረስ የቻሉ ጥቂት ነጋዴዎች ነበሩ::

እነዚህ ነጋዴዎች ከአርሶ አደሩና አርብቶ አደሩ የተለየ ችሎታ ባለቤቶች ባይሆኑም፣ እንደ ነገሩ በጀመሩት ሥራ በጣም የተሻለ ኑሮ የነበራቸው፤ በደርግ መጨረሻና በኢሕአዴግ መጀመርያ ወቅት ሁሉም በየአካባቢው እንደሚያስታውሰው፣ በየአካባቢው የጭነት መኪና ባለቤቶች መሆን የቻሉ፤ ነገር ግን የጥቂትና መሠረታዊ ሸቀጦች፤ የድርና ማግ፣ የዝሃ፣ የጣቃ ብትን ጨርቅ፣ የጨው፣ የቡና ፣ …ወዘተ፤ የግብርና ምርቶችና የሰብል ነጋዴዎች ነበሩ:: ተመሳሳይ የጅምላ ነጋዴዎች በየክፍለ ሀገሩ፣ ጥቂት ሲራራ ነጋዴዎችም በመዲናዋ ይገኙ ነበር::

እነዚህ ነጋዴዎች ለአምራቹም ይሁን፣ ለአንድ ሀገር ኢኮኖሚ የግድ አስፈላጊ ቢሆኑም፤ አዲሱን አሰላለፍ የያዙበት ሁኔታ፣ በአዲስ ሥርዓትና አስተሳሰብ በተቃኘ መልኩ ሳይሆን፤ እንደዋዛ በዚያው በጥንቱ ባህልና ወግ ነበር:: ስለዚህ ድካማቸውና ልፋታቸው ከሌሎች አምራቾች ድካምና ልፋት ጋር ሲነፃፀር፤ ተጠቃሚነታቸውና ቀጣይ ፍላጎቶቻቸው ያው ኋላ ቀሩ ቢሆን አይገርምም::

ይሄው ሂደት የተሻሉትንና አዳዲስ ባለጊዜዎችን ወደ ላይ እስከ ሀገሪቱ መዲና አድርሶ አስመጭና ላኪ በማድረግ፤ እስከ ዛሬም የቀጠለ ሲሆን፣ ይሄ ዘርፍ ያበጠው ዛሬ ከላይ ከተጠቀሱት መሠረታዊ ሸቀጦች ወደተለያዩ በውጭ ሀገር የተመረቱ ሸቀጦች ተቀይሮ በሀገር ውስጥ ይሠሩ የነበሩትን፤ የልብስ ስፌት፣ የሸማ፣ የብረታ ብረት (ቅጥቀጣ) ሥራ፣ የእንጨት ሥራ፣ ሸክላ ሥራ፣ የምግብ ዝግጅትና ባልትና (ዘይትና ቅብዓ ኑግ)፣ የቆዳ ውጤቶች ወዘተ …የመሳሰሉትን የሀገር ውስጥ ሥራዎች በትልልቅ ከተሞች ብቻ ሳይሆን፤ በገጠር ቀበሌዎች ሁሉ ውጦ ነው::

በጥንቱ የፊውዳል ሥርዓት የእጅ ሥራና በተለይ "ሠራተኞች ተንቀዋል፣ ተገለዋል" ተብሎ ቢነበነብም፤ መጨረሻው የሥራውም የሠራተኞችም መዘመንና መስፋፋት ሳይሆን፣ መጥፋት መሆኑ ያሳዝናል:: ሌሎችን ጨምሮ ከላይ የተገለፁት ሥራዎች በአንድ ወረዳ የገጠር ከተማ ገበያ ላይ የሚሠሩ፣ ወይም የምርቶቻቸው መሸጫ ቋሚ ስፍራ ነበራቸው:: ጤፍ ተራ፣ ስንዴ ተራ፣ በግና ከብት ተራ፣ ሸማ ተራ፣ ሸክላ ተራ…. ይባል ነበር፤ ቢላዋ፣ ማጭድ፣ መጥረቢያ፣ ማረሻ የሚሠሩ፣ የሚሸጡ ባለሙያዎች ነበሩ፤ የስፌትና የጥራር መገልገያ ዕቃዎች ነበሩን፤ ልብስ ስፌትም ሁነኛ የከተማ የሥራ መስክ ነበር::

ማህበረሰቡ የተጨማሪ የሥራ ዕድሎችና በሀገር ውስጥ የሚመረቱ ምርቶች ባለቤት ነበር፤ እነዚህን ሁሉ በሀገር ውስጥ ዘመናዊ ምርቶች አልተካንም:: የመጫኛ ነካሾች ቀጣይ ሰለባ ሆነው ቀሩ:: እስካሁን በነበረበት መዝለቅ የቻለው ከግብርና ውጭ የሆነ የከተማ የሥራ ዘርፍ፤ ለወንድ ወዛደርነት፣ በመኪና ላይ ጫኝና አውራጅነት፣ ለሴቶች የቤት ሠራተኝነት፣ ሴተኛ አዳሪነት ብቻ ይመስሉኛል:: አሁን ብዙዎች ታሪክ አንዳንዶች ደግሞ እንደቅርስ የጥቂቶችና የቅንጦት ሆነው፤ ንግድ ተኮሩ ፖሊሲ ሁሉንም ሥራና ምርት ከባህር ማዶ የምንሸምትበትን፤ ጥቂቶችን ተጠቃሚ ብዙሃኑን ሥራ ፈትና ቦዘኔ፣ ሀገሪቱን በአጠቃላይ የውጭ ጥገኛ አድርጓል::

በዚህ መንገድ አድገው የተጠራቀመ ሃብት እጃቸው የገባው፣ ሥልጣንና ጊዜ በአጭር ጊዜ ሰማይ ያደረሳቸው፣ የሀገራችን "ባለሃብቶች" በመዲናዋ ከትመው፤ በማቀባበል ከሚገኝ ተጠቃሚነት ውጪ ሌላው ነገር ዛሬም ዳገትና የማይሞከር ሆኖባቸዋል:: ለዚህ ሥራቸው በየአካባቢው አቀባባይ ነጋዴዎችን በእግራቸው ለመተካትም ችለዋል::

"የአገልግሎት ዘርፉ አያስፈልግም ወይም ጨርሶ ፋይዳ የለውም" ማለት ሳይሆን፤ ነገር ግን የተመረተ ምርት በተለያየ መንገድ ለገበያ መቅረብ የሚችል፣ መቅረቡም የማይቀር ቢሆንም፤ ጥቂት የግብርና ምርት ላኪዎች የሀገሪቱ ቁንጮ ናቸው:: መንግሥት ኤክስፖርትን ለመደገፍ ብሎ የሚሸልመው ላኪዎችን ነው፤ አምራቾችን አያውቃቸውም:: በብሔራዊ ባንክ ፊታውራሪነት፣ በዶላር ሱስ ላይና ንግድ ተኮር በሆነው ፖሊሲ ላይ ተመስርቶ የዘለቀው የሀገሪቱ የፋይናንስ ሴክተር ያለምንም ማስያዣ፣ ከውጪ ገዢ ጋር ውል ይዘው ስለቀረቡ ብቻ ዘጠና ከመቶ ብድር የሚሰጠው ለላኪዎች ብቻ ነው::

ከዚህ በተጨማሪ፣ አምራቹ አምርቶ ላኪዎች ሲነግዱ፤ ሀገር ባገኘችው የውጭ ምንዛሪ ከውጭ ሀገር ሸቀጥ የማስገባት ቅድሚያ መብት አላቸው:: ሁነኛ አቅም ያላቸውና ጥቂቶች ሁለቱንም የሚሠሩ ነጋዴዎች ለወጭ ንግድ የተበደሩትን ገንዘብ፣ ለገቢ ንግድ በሚጠቀሙበት ሁኔታ ብድሩንም የማስገባት፣ መብቱንም ከወጭ ንግዱ ጋር ጀርባ ካለ በኋላ፤ "የሀገር ውስጥ ምርትን ለማበረታት ለገቢ ንግድ የብድር አገልግሎት አልሰጥም" ማለቱ የሚገርምና መሰርይ ሸፍጥ መሆኑን መረዳት ተገቢ ነው:: ለንግድና ለውጭ ምንዛሬ ብቻ ታጥቆ የቆመው ኢኮኖሚ፤ በሚንሰፈሰፍለት የውጭ ምንዛሬ ማዳበርያ፣ ስንዴ ሲሸምት፤ ሌላውን ትተን በሀገር ውስጥ ገበያ ከአስር ብር በታች ዋጋ ያላቸውን፤ ጥርሳችንን የምንኮረኩርበት እስቲኪኒ፣ የቁማር መጫወቻ ካርታ…ወዘተ ከውጭ ሀገር እያስገባ፤ ጋቢና ጎጃም አዘነ በቻይና ፎጣ ሲተኩ፣ በዚህ ሁኔታ ውስጥ ሰማይ የደረሱ የአገልግሎት ዘርፉ ባለቤቶች፣ ሁሉም የመንግሥትና የግል ባንኮች በውጭ ምንዛሬና በውጭ ኮንትራክተር ሰማይ ጠቀስ ፎቅ በመገንባት እየተወዳደሩ፤ የውጭ ምንዛሬ ዕጥረት፣ ደካማ የኤክስፖርት አፈፃፀም ሲባል፤ ዛሬም አምርቶ ሲሸጥ የሚተረፍበት፣ ሲሸምት የሚተረፍበት፣ ብዙ ጭሰኛ የሚፈልግን ፊውዳል እንጂ ማንን ማስታወስ ይቻላል!?

ከፋይናንስ ተቋማቱ መካከል ወደ ውጭ ለሚላኩና ለፋብሪካ ግብአት የሚሆኑ ጥሬ ዕቃዎችን ብቻ ለሚያመርቱ የእርሻ ፕሮጀክቶች፤ ብድር ያቀርብ የነበረው ብቸኛው የኢትዮጵያ ልማት ባንክ፣ ስጦታውን ለሚሰጠው ሰጥቶ (በጋምቤላ)፣ "አበደርሁ" ያለውንም እንደ ነገሩ በትኖ "ከሰርሁ" በማለት ዛሬ ሥራውን አቁሟል:: የእርሻ ምርትን ገዝተው ለሚሸጡ፣ ወደ ውጭ ለሚልኩ፣ የትራንስፖርት አገልግሎት ለሚሰጡ፣ ህንፃ ለሚገነቡና ለሚያከራዩ ብቻ፤ የብድር አገልግሎት የሚሰጡ የመንግሥትና የግል ባንኮች ከፍተኛ ገንዘብ በማካበት ላይ ናቸው:: በተመሳሳይ ከመንግሥትና ከግል ባንኮች ጋር እጅና ጓንት ሆነው የሚሠሩት የኢንሹራንስ እህት ኩባንያዎችም ሀገርና ኢኮኖሚ ባለመረጋገት ሲናጡ በባጁበት ዓመትም አስመዝግበውት የማያውቁት ገቢና ትርፍ ባለቤት መሆናቸው ወቅታዊ ዜና ነው::

በውጭ ንግድ መቀዛቀዝና የውጭ ምንዛሬ እጥረት፣ በሀገሪቱ በተፈጠረው አለመረጋጋት፣ አጠቃላይ ኢኮኖሚው ቢቀዛቀዝም፤ የፋይናንስ ተቋማቱ ከፍተኛ ትርፍ ያተረፉት፤ (ሌሎች አገልግሎት ሰጭዎች ገቢያቸውን በብዙኃኑ አምራች ላይ ላይ ጭነው እንደቆዩት ሁሉ፤) የፋይናንስ ተቋማቱ ገቢያቸውን በሌሎች አገልግሎት ሰጭዎች ላይ ለጊዜው መጫን በመቻላቸው ብቻ ነው:: ሌላ ተሸካሚ ከታች ከሌለ አንዱ አንዱን የሚሸከመው ደግሞ ለተወሰነ ጊዜ ብቻ ነው:: የታችኛውና የመጨረሻው ስለተንገዳገደ ቀጣዩ፣ ከዚያም ላይኛው ይቀጥላል፤ ለውጥ ከሌለ ጊዜን መጠበቅ ብቻ በቂ ነው::



ዳርሰማ ሶሪ

# የመቀሌ ዩኒቨርስቲ ምሁራን ምን ነካቸው?

ነሐሴ 7 ቀን፣ 2010 አዲስ ዘመን ጋዜጣ በ77ኛ ዓመት፣ ቁጥር 337 ዕትሙ፣ በገፅ 2 የሀገር ውስጥ ዜናው ላይ ያነበብሁት ቢያስገርመኝ ግርምቴን ላካፍላችሁ ወደድሁ፡፡

የዚህ ዜና ዘጋቢ መሆናቸው የተገለፁና መርዕድ ክፍሉ በተባሉ ሰው ሥም፣ "የፌደራል መንግሥት ጣልቃ ገብነት የሕግ የበላይነትን ያላከበረ ነው" አሉ ብለው፣ "ሥርዝ የተጨመረ" የመቀሌ ዩኒቨርስቲ የሕግ መምህር መሆናቸውን በመጥቀስ፣ የሰፈረው ዜና ምሁራኑን "ምን ነካቸው?" አሰኝቶኛል፡፡

በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች የሚስተዋሉ ሁከትና ብጥብጦችን ለማስቆም እየተወሰዱ ያሉ እርምጃዎች፤ በተለይም፣ በቅርቡ በኢትዮጵያ ሱማሌ ክልል የተደረገው ጣልቃ ገብነት፣ "የሕግ የበላይነትን ያከበረ መሆኑን የመቀሌ ምሁራን ገለፁ" ይላል የዜናው መግቢያ፡፡

በጋዜጣው ላይ የተገለፁት እነዚህ የመቀሌ ዩኒቨርስቲ የሕግ ክፍል መምህር የሆኑት አቶ የማነ ካህሳይ እና አቶ ገብረ ሕይወት ሀዱሽ፣ ይህንን የመሰለ የግድ የለሽነት አስተያየት ከመስጠታቸው በፊት፤ ቢያንስ በአሁኑ ወቅት በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ሆን ተብሎ የተቀነባበረ በሚመስል መልኩ እየተዘራ ያለውን የጭካኔ እና የመገዳደል መርዝ ቢያወግዙና ቢያንስ ለሞቱት ንፁሐን ዜጎች ትንሽ ሀዘን እንደሚሰማቸው ቢገልፁ፣ አሁን የተሰማኝ ስሜት ባልተሰማኝ ነበር፡፡

እንደሚታወቀው ከጥቂት ወራት ወዲህ፣ እነዚህ ምሁራን ካሉበት የትግራይ ምድር በስተቀር፤ በመላው ሀገሪቱ የተለያዩ የሃይማኖት፣ የዘር፣ የጎሳ እና የመሳሳሉት የግጭት ቀስቶች እየተወረወሩ የፀብ ክብሪቶች እየተለኮሱ አብዛኞዎቹ የከሸፉ ቢሆኑም፤ አንዳንዶቹ የሰው ሕይወት መቅጠፋቸውና የንፁሐን ዜጎችን ሐብትና ንብረት ጨምሮ የዚህችን ደሀ ሀገር ንብረት እያወደሙ መሆናቸውን አያውቁ ይሆን?

በአንድ ሀገር ሕግ የሚያስፈልገውና ዜጎች ሕግ እንዲማሩ የሚደረገውስ ለምንድን ነው? እነዚህ ምሁራን የሚያስተምሩትም ሆነ የተማሩት ሕግ የዜጎችን ሞት እና አካል መጉደል፤ እርስ በርስ መዘራራፍና መገዳደል እንዲያቆም የማያውቁ እና የማያሳውቁ ከሆነ ጥቅሙ ምንድን ነው?

ይህን በስውር እጆች የሚዘወር ተግባር፤ ሓላፊነት በማይሰማቸው፣ ሀገር ለማመስ እና ለማበጣበጥ ልቅ በሆኑት የማህበራዊ ሚዲያዎች ላይ ባነበው ይህን ያህል ባልገረመኝ ነበር፡፡

ላለፉት ሁለት አስርት ዓመታት ከጀርባው እየተነዳ፣ በሱማሌ ክልል አድራጊና ፈጣሪ ተደርጎ የተቀመጠ አካል፤ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ዜጎች ከፍተኛ አደጋ ውስጥ ሲገቡ እና ቤተ እምነቶች፣ የመንግሥት ተቋማት፣ የዜጎች መኖሪያ ቤቶች እና የንግድ ሥፍራዎች እንደ ጧፍ ሲነዱ ጥቂት የማይባሉ ንፁሐን ዜጎች ሕይወት ሲቀጥፍ ምን መደረግ ነበረበት? ነው የምትሉት፡፡

እነዚህ ምሁራን፣ ሕገ መንግሥቱን አደጋ ውስጥ ሊጥል የሚችል ሁኔታ ከተፈጠረም፤ በጉዳዩ ላይ የፌደሬሽን ምክር ቤት ሲወስን ጣልቃ መግባት እንደሚችል እና ከዚህ ባለፈ ግን፣ ሁለቱ ምክር ቤቶች ተሰብስበው እስኪወስኑ ድረስ ችግሮች ይፈጠራሉ ከተባለ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 93 ላይ በተቀመጠው መሠረት የሚኒስትሮች ምክር ቤት አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ የማወጅ ሥልጣኑን መጠቀም እንደሚገባ ተናግረዋል፡፡

አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ በማወጅ ብዙ ሺዎችን አፍሶ በማጎር እና የእነዚህ የጭፍጨፋውና አበጣብጦ የማውደም ፊት አውራሪዎች ጋሻ ጃግሬዎቻቸውን ጨምሮ ከነሙሉ ትጥቃቸው እና ለዓመታት የተንኮል ድር ካጨናነቋቸው ሴራዎቻቸው ጋር ክልሉን ይበልጥ በማበጣበጥ፤ የመከላከያ ሠራዊትን ሕዝብ ጨፍጫፊ የማሰኘት ቀዳዳ ለመስፋት ከሆነ፣ ይህ ተግባር ላይደገም አብቅቷል፡፡

ፌዴራል መንግሥት ጣልቃ መግባት የሚችለው አንድም በክልሎች የፀጥታ ችግር ሲፈጠር እና የክልሉ መንግሥት ባለው ኃይል ሕግ ማስከበር አቅቶት ድጋፍ ሲጠይቅ፤ አልያም የፌዴራል መንግሥት ጣልቃ እንዲገባ ባይጠይቅም፣ በክልሎች ውስጥ ከባድ የሆነ የሰብዓዊ መብት ጥሰት ሲኖር፤ ለፌደሬሽንና ለሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት አሳውቆ፣ ማጣራት ከተደረገ በኋላ እንዲገባ ሲወስን መሆኑን ምሁራኑ ይናገራሉ፡፡

ለመሆኑ በእናንተ እሳቤ የሰብዓዊ መብት ጥሰት የሚባለው ስንት ሰው ሲሞት እና ስንት ክልል የሚገኙ የመንግሥትና የግል ተቋማት ወደ አመድ ቁልልነት ሲቀየሩ ይሆን?

ይሄ ከሰባት በላይ ቤተ እምነቶችን ማቃጠል ከ92 በላይ ንፁሐን ዜጎች ሲገደሉና በመቶዎች የሚቆጠሩ ሥጋቸው በጥይት ሰመተር፣ በመቶዎች የሚቆጠሩ መኖሪያና የንግድ ድርጅቶች ሲወድሙና ሲዘረፉ፤ ባንኮች፣ ኢንሹራንሶች፣ የሰብዓዊ መብት ቢሮዎች እንዳልነበሩ ሲሆኑና የተለያዩ የመንግሥት ተቋማት ቀን በቀን በጠራራ ፀሀይ ሲጋዩስ ምን ተብሎ ነው የሚገለፀው?

ለዓመታት የፌደራል መንግሥት ጽ/ቤት ብቻ መክሰስ፣ መፍረድም ሆነ ማሰር በሚችልበት የፀረ-ሽብር ሕግ፤ በፎርማው 15 ዓመት እና ዕድሜ ልክ እየፈረደባቸው ዝዋይና ቃሊቲ የክልሉን ነዋሪዎች በግልጽ ሲያጉር የቆየው ፣የሩቅ ጊዜ ድርጊቱን እንኳን አቆይተን፤ ከቅርብ ወራት ወዲህ በተደጋጋሚ ጥፋት ከመፈፀም አልፎ በመኪናው ብር አጭቆ እንደ በራሪ ወረቀት እየበተነ በግልፅ የጥፋት ተግባሩን ሲሠራ እና ሲያሠራ በእናንተ ምሑራዊ አስተሳሰብ ዝም ብሎ ማየት፤ አልያም ጥቅምት መጀመሪያ ላይ የሚከፈተውን መ/ቤት መጠበቅ ነበረበት?

በእርግጥ እንደ ግለሰብ በሀገራችሁ ጉዳይ አስተያየት መስጠታችሁን ባከብርም፤ በአንድ ትልቅ ዩኒቨርስቲ ውስጥ የሕግ መምህር ሆናችሁ፣ እንዲህ ዓይነት ለሰው ልጅ ሕይወት በጅምላ መጨፍጨፍና በጥቂት ወንበዴዎች ዘርንና ሃይማኖትን ምክንያት ያደረገ ውድመት ሲፈፀም ጭፍን አስተያየት መስጠታችሁና ተማሪዎቻችሁን ምን ዓይነት ሕግ እንደምታስተምሩ ግራ ስለገባኝ ነው ይህን ለመጻፍ የተገደድሁት፡፡

ሀገር እንዲህ በጥቂት አውሬዎች እና ሆዳሞች ስትታመስ ዝም ብሎ መመልከትና እንቅፋት መሆን፤ እንኳንስ ከአንድ ይቺ ደሀ ሀገር ተበድራ ካስተማረችው ከፍተኛ የትምህርት ተቋም የሕግ መምህር ቀርቶ፤ ከተራው ዜጋም ቢሆን ይህን መሰሉን ደንታ ቢስነት እውቀትን፣ አካባቢንና ዘርን ምክንያት አድርጎ በጀርባ የሚፈፀሙ ሴራዎችን መደገፍ አድርጌ እወስደዋለሁ፡፡

ይህን ድፍን ሀገር ያወገዘውንና እጅግ ያሣዘነውን ድርጊት፣ መንግሥት ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶ መሰል አረመኔያዊ ተግባሮች እንዳይከሰቱ ቅድመ ጥንቃቄ እና ዝግጅት ያስፈልጋል፡፡ እንዲያውም "መንግሥት በመዘግየቱ፣ እኩይ ተግባሩ ከፍተኛ ጥፋት እንዲያደርስ ሆኗል" በሚባልበት ሰዓት እናንተ "ሕገ መንግሥቱን ተጥሷል" ማለታችሁ አሳፋሪ ነው፡፡

በዚህ ላይ፣ የኢትዮጵያ የሃይማኖቶች ጉባኤ ድርጊቱን ሙሉ በሙሉ በማውገዝ፤ መንግሥት የዜጎችን ደህንነት ለመጠበቅ ፈጣን እርምጃ እንዲወስድ ያወጣውን አስቸኳይ መግለጫ ፈልጋችሁ እንድታደምጡ እየጋበዝሁ፤ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ መንግሥትን የኮነናችሁበትንና በጋዜጣው ላይ የሠፈረውን የእናንተን ሐሣብ ላስታውሳችሁና ላብቃ፡፡

"ከቅርብ ጊዜ ወዲህም ክልሎች በራሳቸው የውስጥ ችግራቸውን መፍታት የሚችሉበት ጉዳይ ላይ የፌደራል መንግሥት ጣልቃ ገብነቶች ታይተዋል፡፡ በሰው ሕይወት እና በንብረት ላይ በደረሰ ጉዳት፤ እንዲሁም ብሔርን መሠረት ባደረገ ጥቃት በተፈጠረ የሰብዓዊ መብት ጥሰት ምክንያት፤ ችግሩን በማርገብ ሰበብ፣ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች፣ በኢትዮጵያ ሶማሌ እና በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልሎች ላይ ይሄው የፌደራል ጣልቃ ገብነት ተስተውሏል፡፡ በክልሎች አመራሮችን ከሥልጣናቸው እንዲለቁ እስከማድረግም ተደርሷል፡፡"



ብሩክ መኮንን

# “ቤቱ ጠባቻው ነው!!... ውጣላቸው፤ ሰፊ አድርገን እንሠራላቸዋለን”

## ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ

ከዛሬ አርባ ሦስት ዓመት በፊት፣ ኢትዮጵያን በአልጋ ወራሽነት፣ በንጉሠ ነገሥትነት ለግማሽ ምዕተ ዓመት የገዟት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ፤ የየካቲት 1966 ሕዝባዊ አብዮትን ተከትሎ፣ ከሥልጣን ተወግደው በጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ቁጥጥር ሥር ሆነው ነበር::

ልክ የዛሬ አርባ ሦስት ዓመት፣ በዚህ ሣምንት ነሐሴ 20 ቀን፣ 1967 ዓመተ ምሕረት የደርግ ባለሥልጣናት ለተከታታይ ቀናት ንጉሡን ለመግደል የተለያዩ ሙከራዎችን ሲያደርጉ እንደነበር፤ በመጨረሻም በዚያው ቀን ነሐሴ 20፣ 1967 ኮሎኔል ዳንኤል አስፋው ሻለቃ እንዳለ፤ ሻለቃ ጎራው ንጉሡን በትራስ አፍነው መግደላቸውን፣ በወቅቱ የንጉሠ ነገሥቱ የግል አገልጋዮች በመሆን ሲያገለግሏቸው የነበሩ የዓይን ምስክሮች፣ የአፄ ኃይለ ሥላሴ የመጨረሻ ቀናት እንዴት እንደነበሩ፤ ወደ ኋላ ተመልሰን እንድናይ እንዲህ ይተርኩታል::

ኢትዮጵያዊው እውቁ የቀዶ ጥገና ሐኪም ፕሮፌሰር አስራት ወልደየስ፤ አፄ ኃይለ ሥላሴ ከሥልጣን ተወግደው እንደነበር በግንቦት ወር በጠና በመታመማቸው፣ አስፈላጊውን ምርመራ ከአደረግሁላቸው በኋላ፣ የቀዶ ጥገና ሕክምና ውጭ ሀገር ሄደው እንዲታከሙ ለደርግ ባለሥልጣናት በጽሑፍ አሳሰብኳቸው፤ የደርግ ባለሥልጣናትም፣ ‘አይቻልም፤ ራስህ አክማቸው’ ብለው አዘዙኝ::

አፄ ኃይለ ሥላሴ፣ በእድሜ ምክንያት መሸኛቸው አጠገብ ያለው አንድ ሕዋስ እያበጠ መጥቶ ሽንት መተላለፊያ ቱቦውን በመዝጋቱ፤ ይሔን ሕዋስ በቀዶ ጥገና ለማውጣት ከክቡር ዘበኛ ሆስፒታልና ከልዕልት ፀሀይ ሆስፒታል በተውጣጡ ሁለት ነርሶች፤ አንድ የአርባ ዓመት ልምድ ያለው የሰመመን ሰጭ ባለሙያና በእኔና በረዳቴ አማካይነት የተሳካ የቀዶ ጥገና ሕክምና አደረግንላቸው::

የቀዶ ጥገና ሕክምናውን ባደረጉበት ወቅት፣ ከፖሊስ ሠራዊትና ከክቡር ዘበኛ ሆስፒታሎች የሚሠሩ ሁለት የእንግሊዝና የስዊዘርላንድ ሐኪሞች እንደተገኙና ስዊዘርላንዳዊው ሐኪም፣ ‘አይዞዎት አይፍሩ’ እያለ እየደጋገመ በመናገሩ፤ አፄ ኃይለ ሥላሴ በፈረንሳይኛ ቋንቋ፣ ‘የኢትዮጵያ ንጉሥ ከመሆናችን በፊት ራሳችንን የገዛን ንጉሠ ነገሥት ነበርን’ ብለው እንደመለሱ፣ እውቁ ኢትዮጵያዊ የቀዶ ጥገና ሐኪም መምህር ፕሮፌሰር አስራት ወልደየስ ተናግረዋል::

የቀዶ ሕክምናው ከተካሄደ በኋላ፣ እንደዚያ አይነት ቀዶ ጥገና ሕክምና የተደረገለት ሕመምተኛ ለማገገም፣ ሁለትና ሦስት ሳምንት ሲፈጅበት፤ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ግን አስራ አንድ ቀን ብቻ እንደፈጀባቸው፣ ከሆስፒታል ከወጡ በኋላ ሰውነታቸው እንደ ቀድሞው መስተካከሉን፣ ምግብ በጥሩ ሁኔታ መመገብ መጀመራቸውን፤ ለዓመታት የንጉሡ የግል አገልጋይ ያስታውሳሉ::

ከወራት በኋላ፣ ከነሐሴ አጋማሽ ጀምሮ ኮሎኔል ዳንኤል አስፋውና ለጊዜው ስሙ ያልታወቀ ‘እንዳለ’ የተባለ የደርግ ጽ/ቤት የሕክምና ባለሙያ፤ ነሐሴ 17 ቀን 1967 ንጉሡ አዘውትረው በሚቀመጡበት ወንበር ሥር የኤሌትሪክ ኢንስትሩመንት አስቀምጠው በኮረንቲ ገመድ ከአያያዙ በኋላ ከግድግዳው ላይ ካለው ሶኬት ጋራ ሰክተው በኤሌትሪክ አስይዘው ለመግደል ያደረጉት ሙከራ ሳይሳካላቸው ቀርቷል::

ኮሎኔል ዳንኤል አስፋው እንዳለ የተባለው የደርግ ጽሕፈት ቤት የሕክምና ባለሙያ፣ ይህንን ወጥመድ ሲያጠምዱና ሲያቀናብሩ፤ አፄ ኃይለ ሥላሴ እና ልጃቸው ልዕልት ተናኘ ወርቅ ይመለከቷቸው እንደነበር ይህንን ወጥመድ ለማጥመድ ለምን እንዳስፈለገ ግን እንደማያውቁ የዓይን ምስክሩ የንጉሡ የግል አገልጋይ ተናግረዋል::

በነጋታው ነሐሴ 18 ቀን፣ 1967 ኮሎኔል ዳንኤል አስፋው እና የደርግ ጽህፈት ቤቱ የሕክምና ባለሙያ፣ ‘ለብርታት ለጥንካሬ ይጠቅምዎታል’ በሚል አፄ ኃይሌ ሥላሴን ኪኒን እንዲውጡ ለማድረግ ሞክረው አፄ ኃይለ ሥላሴ ጋራ ብዙ ትግል አድርገው ሳይሳካላቸው እንደቀረና እንደ ግል አገልጋይነታቸው ወደ ንጉሡ መኝታ ቤት ሲገቡ፤ እንክብሉ ወለሉ ላይ ወድቆ መመልከታቸውን የንጉሠ ነገሥቱ ከረባትና ሸሚዛቸው ተጨመዳዶና ተዛንፎ መመልከታቸውን ከሃያ አንድ ዓመት በኋላ ፍርድ ቤት በመቅረብ በሰጡት ምስክርነት ተናግረዋል::

“እኔ ንጉሡ ከሚተኙበት መኝታ ቤት በር ላይ ነበር የምተኛውና የማገለግላቸው፤ ነሐሴ 20 ቀን 1967 ኮሎኔል ዳንኤል አስፋው ጠርቶኝ፣ ዛሬ ከንጉሡ ጋር ማደር እንደማልችል በመግለጽ ከለከለኝ፤ ኮሎኔል ዳንኤል አስፋውን ትዕዛዙን እንደምቀበል፣ ነገር ግን ይህንኑ ለንጉሡ መንገር እንዳለብኝ ገለጽሁለት፤ ጥያቄዬ ተቀባይነት አግኝቶ ለንጉሡ ከምሽቱ ሦስት ሰአት ላይ ነገርኳቸው::

ለግርማዊነታቸው ስነግራቸው፣ ከአልጋቸው ተነሥተው፤ ‘ቤቱ ጠባቸው ነው፤ ውጣላቸው፤ ሰፋ አድርገን እንሠራላቸዋለን’ ብለው ብርክክ አሉና ዕንባቸውን በጎዳናቸው ላይ እየጠረጉ፣ ‘አይ አንቺ ኢትዮጵያ፤ እውነት በድለንሻል ወይ?’ ብለው እያለቀሱ ሲናገሩ አይቻቸዋለሁ” ብለዋል::

አፄ ኃይለ ሥላሴን በተደጋጋሚ ለማጥቃትና ለማሰቃየት ሲመላለስ የነበረውን ዳንኤል አስፋውን አንድ ቀን ግርማዊነታቸው አስጠርተው፤ ‘እናንተ ዓላማችሁ ምንድን ነው?’ ብለው እንደጠየቁትና ኮሎኔል ዳንኤል አስፋውም፤ ‘ዓላማችን ዝቅ ያለውን ከፍ ማድረግ፤ ከፍ ያለውን ዝቅ ማድረግ ነው’ ብሎ እንደመለሰላቸውና ግርማዊነታቸውም፣ ‘አይሆንላችሁም’ ብለው መናገራቸውን ተናግረዋል::

ነሐሴ 20 ቀን 1967 አፄ ኃይለ ሥላሴ ታስረው የሚኖሩበትን ቤት መጠበቅ ምድብ ሥራቸው የነበረ የንጉሡ አገልጋይ፤ ያን ዕለት ከምሽቱ ሦስት ሰአት አካባቢ፣ ኮሎኔል ዳንኤል አስፋው፣ ሻለቃ እንዳለ እና ሻለቃ ጎራው ንጉሡ መኝታ ቤት ገብተው ለአርባ ደቂቃ ያህል ቆይተው ተመልሰው መሄዳቸውን መመልከቱን፤ በነጋታው አፄ ኃይለ ሥላሴ ሁልጊዜ ለጸሎት በጠዋት ይነሡ እንደነበርና ነሐሴ 21 ቀን፣ 1967 ጠዋት እንደልማዳቸው ባለመነሣታቸው፣ በጥርጣሬ ወደ ንጉሡ መኝታ ቤት ገብተው ሲመለከቱ፤ አፄ ኃይለ ሥላሴ ሞተው እንዳገኟቸው፣ ክፍሉም ኤተር፣ ኤተር (የማደንዘዣ ውሁድ) ይሸት እንደነበር፤ በንጉሡ አንገት አካባቢም፣ ለቁስል ማሰሪያ የሚያገለግል ፋሻ ተቀምጦ ማየታቸውንና መሞታቸውን ሪፖርት ቢያደርጉም፤ ምንም ምላሽ እንዳልተሰጣቸው ሳግ እየተናነቃቸው ተናግረዋል::


ብዙዎች በታላቅ አክብሮት የሚያስታውሷቸው፣ ዓለም ያለቀሰላቸው፣ ሀገራቸው መቀበሪያ መሬት የነፈገቻቸው፣ ለሃምሳ ዓመታት ሀገራቸውን ያስተዳደሩ፣ የፓን አፍሪካ ርዕዮትን በማራመድ የአፍሪካ አንድነት ድርጅትን እንዲመሠረት ያደረጉት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ከተናገሯቸው ዘመን ተሻጋሪ ንግግሮች ውስጥ አንዱ፣ “ወንጀልን ማብዛትና ቂምን ማስታወስ እንተው፤ በቀል ከንቱ በመሆኑ የበቀልን ስሌት እናጥፋ፤ እንዲህ ያለው ስሜት መንፈሳችንን ከማድከምና ልባችንን ከመበረዝ የተለየ ጥቅም አይሰጠንም” ብለው ነበር::

በእርግጥም፣ ከዛሬ 43 ዓመት በፊት በግፍ የተገደሉት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ እንዳሉት፣ ዛሬም ወንጀልን አናብዛ፤ ይቅር እንባባል፤ እንደመር፤ ወቅቱ ግድ የሚለው አንገብጋቢ ሀገራዊ አጀንዳ ነው-እናድርገው::

*ዋቢ፡*

*ከልዩ ዓቃቤ ሕግ ምስክሮች ቃል ሰኔ 1988 ከፕሮፌሰር አስራት ወልደየስ ጋራ የተደረገ ቃለ ምልልስ*

# ለሺዎች ባልንጀራ የሚሊዮኖች መሪ



ኮፊ አናን

"ዓለም ያጣችው ታላቁን አፍሪካዊ ዲፕሎማት እና የሰብዓዊ መብት ተቆርቋሪውን እንዲሁም የጋራ እሳቤዎች አራማጁን የዓለም አቀፍ ሰላምና ደህንነት ጠባቂዋን ነው ሲሉ ነበር" የሕንዱ ጠቅላይ ሚኒስትር ናርዲራ ሙዲ የቀድሞ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዋና ጸሐፊ የኮፊ አናንን ዜና እረፍት ሲሰሙ የተናገሩት::

የቀድሞው የአሜሪካ ፕሬዝዳንት ባራክ ሑሴን ኦባማ፣ "በዓለም ላይ ያሉ የልዩነት ግንቦችን ካፈረሰ በኋላም ቢሆን፤ ኮፊ አናን የተሻለ ዓለም ለማየት ለመፍጠር መሥራቱን አላቆመም ነበር:: ዛሬ ግን ሞት አሸነፈው" ነበር ያሉት::

በቀድሞዋ ጎልድ ኮስት፣ በአሁኒቱ ጋና በ1938 ሚያዝያ ስምንት ቀን፣ ከመንትያ እህታቸው ከኡፊ አታ ጋራ፤ ኩማሲ በተባለች ስፍራ የተወለዱት ኮፊ አናን፣ በጋና ከታወቁ የጎሳ መሪዎች አንዱ ከሆኑ ቤተሰብ ነው የተወለዱት:: ይህ ጎሳ፣ የሚወለዱ ልጆች የተወለዱበትን ቀን ወይንም ወር ስም የመውረስ ባህል ያለው ሲሆን፤ ጋናውያን ከብሪታንያ ነፃነታቸውን በተጎናፀፉ በዋዜማው ነበር ወደ ትምህርት ቤት የገቡት::

በ1870 በኬን ኮስት በሚገኘው ማፌንቴስፓም የተባለ ትምህርት ቤት፣ በመቀጠልም በሜቶዲስት አዳሪ ትምህርት ቤት የአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ተምረው በ1957 አጠናቀቁ:: በ1958 አሁን ኩዋሜ ንኩርማህ ዩንቨርስቲ ኦፍ ሳይንስ ኤንድ ቴክኖሎጂ ኦፍ ጋና፣ የዚያኔው ኩማሲ ኮሌጅ ኦፍ ሳይንስ ኤንድ ቴክኖሎጂ ገብተው፤ በኢኮኖሚክስ ትምህርታቸውን ተከታትለው ካጠናቀቁ በኋላ፤ ፎርድ ፋውንዴሽን የሰጠውን የነፃ ትምህርት ዕድል በማግኘት ወደ አሜሪካ አቅንተው፤ በሴንት ፖል ሚኒሶታ ማክላስተር ኮሌጅ በዲፕሎማ ደ ኢትዩድ አፕሮፌንደሪስ ተመረቁ:: ከዚያም ወደ ስዊዘርላንድ በመሄድ በግራጅዌት ኢንስቲትዩት ኦፍ ኢንተርናሽናል ዴቨሎፕመንት ስተዲስ ከ1961 እስከ 1962 ተምረው በዲግሪ ተመረቁ:: ከዚያም የማስተርስ ዲግሪያቸውን በሳሎን ስኩል ኦፍ ማኔጅመንት አግኝተዋል::

ኮፊ አናን እንግሊዝኛ፣ ፈረንሳይኛ፣ አካን እና ኩሩ የተባሉ በጋና የሚነገሩ ቋንቋዎችንና ሌሎች አፍሪካ ውስጥ የሚነገሩ ቋንቋዎችን አቀላጥፈው መናገር ይችላሉ:: ገና በዲግሪ ተመርቀው ሥራ የጀመሩት በዓለም ጤና ድርጅት ወስጥ የበጀት ኦፊሰር በመሆን ነው:: ወደ ሀገራቸው ተመልሰው የጋና የቱሪዝም ኮሚሽን በመሆን ለሁለት ዓመታት ከሠሩ በኋላ፤ ወደ ጄኔቭ በማምራት የተባበሩት መንግሥታት የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽን ጽሕፈት ቤት ኃላፊ በመሆን፣ በዓለም አቀፉ ተቋም የበጀት እና የዕቅድ የቁጥጥር አሠራር ላይ አዲስ አሠራር በመዘርጋት፣ በአጭር ዓመታት ውስጥ የድርጅቱ ዋና ጸሐፊ የጽሕፈት ቤት ኃላፊ ለመሆን በቁ::

እውቁ ዲፕሎማት ኮፊ አናን፣ በ1965 በጄኔቭ ስዊዘርላንድ ከቲቲ አልካጂ ጋራ ትዳር መሥርተው ለአስራ ስምንት ዓመት በትዳር ከቆዩ በኋላ በ1983 ተፋትተዋል:: በዓመቱ በ1984 ለሁለተኛ ጊዜ ከናኒ ላጀርግሪን ጋራ ተጋብተው እስከ ዕለተ ሞታቸው ድረስ አብረው ቆይተዋል:: ኮፊ አናን የሦስት ልጆች አባት ነበሩ::

የግብፃዊው ስድስተኛው የተባበሩት መንግሥታት ዋና ጸሐፊ ቡትሮስ ቡትሮስ ጋሊ ምክትል በመሆን፤ ለዓመታት የሠሩት፣ በአዲስ አበባም ለዓመታት የኖሩት ኮፊ አናን፣ የድርጅቱ ዋና ጸሐፊ እንዲሆኑ፤ አሜሪካ በውጭ ጉዳይ ሚኒስትርዋ ዋረን ክሪስቶፈር አማካይነት ሰፊ ዘመቻ አድርጋላቸዋለች:: በጊዜው በብዙዎች፣ ሌላኛው የአሜሪካ ውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት የሚባለው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅትን አስተዳደራዊ የመዋቅር ማስተካከያ በማድረግ፤ በአጭር ጊዜ ውስጥ ለውጥ አሣይተው አድናቆት አግኝተዋል::

ከዛሬ ሃያ ዓመት በፊት፣ በመላው አፍሪካ ኤች አይ ቪ ኤድስ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎችን ሲቀጥፍ፤ ዓለም አቀፍ ተቋም በሙሉ ኃይሉ ወረርሽኙን ለመግታት የሚያደርሰውን ጉዳት ለመቀነስ የሚያስችለው ራሱን የቻለ ጽሕፈት ቤት በመክፈት ከፍተኛ የሆነ ሕይወት የማዳን ሥራ ሠርተዋል::

በኢራን የሳዳም ሁሴን መንግሥት ላይ አሜሪካ መራሹ ሕብረ ብሔር ጦር ዘመቻ አካሂዶ ካወደማት በኋላ፤ ለኢራቃውያን ሕፃናት እናቶች፣ "ነዳጅ ለምግብ" የሚል ፕሮግራም ነድፈው በሥራ ላይ እንዲውል በማድረግ በወሰዱት እርምጃ፤ በፀጥታው ምክር ቤት አባል ሀገራት ከሥልጣናቸው እንዲነሡ ከፍተኛ ግፊት ቢደረግባቸውም ከመጋቢት 1992 እስከ ታኅሣሥ 1986 ድረስ የነበረውን የመጀመሪያውን የሥልጣን ጊዜያቸውን በተሳካ ሁኔታ አጠናቀዋል::

ኮፊ አናን፣ "የአሜሪካ መንግሥት ተልዕኮ አስፈፃሚ ናቸው" የሚል ተቃውሞና ትችት ቢሰነዘርባቸውም፤ በሌላ በኩል ደግሞ በሩዋንዳ ▶

የተፈጠረውን የእርስ በርስ ጦርነት ለመቋቋም በተመድ የሚታዘዘው የሰላም አስከባሪ ጦር የሚያስፈልገውን የጦር መሣሪያ ተጨማሪ የሰው ኃይል እንዲገባ ባለመፍቀድ፣ “ተመድ ላይ የማይሽር ቁስል አኑረውበታል” ሲሉ በሩዋንዳ የተመድ ሰላም አስከባሪ ኃይል አዛዥ ካናዳዊው ሮሚዮ ዶሊየር ኮፊ አናንን ይከስሳሉ:: ኮፊ አናን በተመድ ዋና ጸሐፊነታቸው በተለያዩ ኃላፊነቶች ላይ በነበሩ ጊዜ የሠሩዋቸውን ተግባራት ባወሱበት “ኢንተርቬንሽን፡ ኤ ላይፍ ኢን ዋር ኤንድ ፒስ” መጽሐፋቸው በሶማልያ፣ በሩዋንዳ፣ በዩጎዝላቭያ የተፈጠረው ሰብዓዊ ቀውስና አኮኖሚያዊ ውድመት ከመድረሱ በፊት፤ የዓለም ማኅበረሰብ ጣልቃ እንዲገባ ያደረጓቸውን ጥረቶች፣ የዓለም ልዕለ ኃያላኖቹ መንግሥታት ያሣዩትን ዳተኛነት አጋልጠዋል::

በመጀመሪያው ዓመት የሥልጣን ቆይታቸው በወሰዱዋቸው የመዋቅር ማስተካከያዎችና የበጀት ድልድል፣ ቁጥጥር የሠፈነበት አሠራር ምክንያት፤ ለሁለተኛ ጊዜ በዋና ጸሐፊነት ተመርጠው እንዲሠሩ እጩ አድርጎ አቅርቦአቸው የተመድ ጠቅላላ ጉባኤ ለሁለተኛ ጊዜ የተመድ ዋና ጸሐፊ ሆነው እንዲሠሩ መረጣቸው:: ከሰኔ 27 ቀን 2001 ጀምሮ በባንኪሙን እስከተተኩበት ጥር 2007 ድረስ የተመድ ዋና ጸሐፊ ሆነው አገልግለዋል::

በዓለም አቀፍ ልማት ላይ የሚሠራ ፋውንዴሽን በማቋቋም፣ ከተመድ ዋና ጸሐፊነት ከተሰናበቱ በኋላ ሢሠሩ የነበሩት ኮፊ አናን፤ በሶርያ የተፈጠረው የእርስ በርስ ጦርነት ያስከተለውን ውድመት ለማስወገድ፤ በተመድና በአረብ ሊግ የተቋቋመው ጥምር ግብረ ኃይል መሪ በመሆን፣ በናይማር የደረሰውን የሮይንጋ ቀውስ የሚያጣራ የመፍትሔ ሐሳብ የሚያቀርብ ኮሚሽን በመምራት፣ እስከ 2016 ድረስ በትጋት ተንቀሳቅሰዋል::


በ2001 ዓ.ም ከሚመሩት ተቋም ጋራ የኖቬል የሰላም ሽልማት ያገኙት፤ ከደቡብ አፍሪካው የነፃነት ታጋይ ኔልሰን ማንዴላ ጋራ በመሆን ያቋቋሙት ዓለም አቀፍ የአዋቂዎች ተቋም የመሠረቱትና የዚያ ሊቀ መንበር በመሆን የሠሩት ኮፊ አናን በተወለዱ በሰማንያ ዓመታቸው ነሐሴ 18 ቀን፣ 2018 ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል::

የተባበሩት መንግሥታት የሰብዓዊ መብት ኮሚሽን ኮሚሽነር፣ “ዓለም ዛሬ በመሪዎች ልትሞላ ትችላለች፤ ነገር ግን እንደ ኮፊ አናን ያለ ለሺዎች ባልንጀራ የሚሊዮኖች መሪ መሆን የሚችል ሰው አጥታለች:: በእርግጥም ዛሬ ዓለም እውነተኛ ልጇን አጣች” ብለዋል::

የሩሲያፕሬዝዳንት ቭላድሚር ፑቲን፣ “እውነተኛ ሰብእናህን፣ ለሰው ልጆች ያለህን ፍቅርና አክብሮት እኛ ሩሲያውያን በልባችን ለዘላለም በወርቅ ቀርፀነው እንኖራለን፤ ደህና ሁን፣ ኮፊ አናን” ብለዋል::

የብሪታኒያዋ ጠቅላይ ሚኒስትር፣ “መቼም ቢሆን በችግር፣ በቀውስ ወቅት ቢሆንም፤ ተረጋግቶ ሰብአዊ ክብር እንዲረጋገጥ፣ እንዲከበር፤ ቅድሚያ ሰጥቶ የሚሠራን በዝምታ ውስጥ ያለውን ታላቅ የመሪነት ክህሎቱን እንደያዘ ያ ታላቅ የዓለማችን መሪ ዛሬ ከአጠገባችን ሄዷል፤ ኮፊ አናን መልካሙ ሥራህ፣ ተጋድሎህ፣ አብሮን አለ፤ በሰላም እረፍ፤ መፅናናት ልጇን ላጣችው ዓለማችን ይሁን” ብለዋል - የታላቁን ሰው ዜና እረፍት እንደ ሰሙ:: እኛም ያንን ታላቅ አፍሪካዊ፣ “ነፍስህን ይማር” ብለናል::


# ወዳጄ ኮፊ አናን



ከፍቅሩ ኪዳኔ



*ኒውዮርክ፣ እኤአ የ2000 መግቢያ በር ማስታወሻ ከኦሎምፒክ እንቅስቃሴ ለተባበሩት መንግስታት ሳበረክት*



*ሶልት ሌክ ሲቲ አሜሪካ፣ ኮፊ አናን፣ የአይኦሲ ፕሬዝዳንት ቶማስ ባክና ፍቅሩ ኪዳኔ*

ወዳጄ ኮፊ አናን በፕኒሞኒያ (ብርድ በሽታ) ሕመም ምክንያት በአንድ ሳምንት ውስጥ በ80 ዓመቱ ከዚህ ዓለም ተለይቷል::

ኮፊ አናንና እኔ የተዋወቅነው እኤአ በ1964 እሱ ከጄኔቫ፣ እኔ ከኮንጎ ኪንሻሳ የተባበሩት መንግሥታት ጽሕፈት ቤቶች ተዛውረን አዲስ አበባ ኢሲኤ ሥራ የጀመርን ጊዜ ነው:: ሁለታችንም የጃዝ ሙዚቃ ስለምንወድ፣ እሁድ ጧት አብረን እንሰማ ነበር:: ከዚያም እኤአ በ1970 ኮፊ አናን ወደኒውዮርክ ተዛወረ::

እዚያም በልዩ ልዩ ቅርንጫፎች በሓላፊነት በመሥራት ካገለገለ በኋላ፤ በመጨረሻ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዋና ጸሐፊ ሆኖ ተመርጦ አስር ዓመታት ሠርቷል:: ኮፊ አናን ይሄን ሁሉ ከፍተኛ ግዳጅ ያከናወነው በጥሩ ጥሩ ረዳቶች ስለተከበበም ነው:: እርሱ ካቢኔ ውስጥ ከነበሩት ውስጥ ለብዙ ዓመታት ያገለገለችው ጸሐፊ ኢትዮጵያዊት ወይዘሮ ዋጋዬ አስበ ነበረች:: ኮፊ አናን በጣም ጨዋ፣ ወዳጆቹን የማይረሣ በሚቻለው መጠን ሁሉን የሚረዳ፣ አርቆ አስተዋይ ግሩም ሰው ነበር:: ኔልሰን ማንዴላ “ቦስ፣ አለቃዬ” ብለው ይጠሩት የነበረ፣ በአሜሪካና በስዊዘርላንድ ዩኒቨርስቲዎች የተማረ፣ ሁልጊዜ ሽክ የሚል፣ ሁሉን አክባሪ ድንቅ ሰው ነበር::

በመጨረሻ የተገናኘነው ለባህር ዳር ውይይት ሽራተን ሆቴል መጥቶ ነው:: አንዴ በፆም ወራት ከወዳጆቼ ጋር ቡና ቤት ሄጄ፣ አንደኛው የፆም ማኪያቶ አዘዘ:: ልጅቷ ዞር ብላ ለባር ማኑ አንድ ኮፊ አናን ብላ አዘዘች:: የፆም ማኪያቶ ኮፊ አናን መባሉን ነግሬው አብረን እንስቅ ነበር:: በመሠረቱ በሚቀጥለው ጊዜ ወደ ጄኔቫ ስሄድ ለመገናኘት ተቀጣጥረን ነበር:: ኮፊ አናን ካረፈ ጀምሮ መላው የዓለም መሪዎች አድናቆታቸውንና ለእርሱ ያላቸውን አክብሮት በሰፊው ገልፀዋል:: ይሄም ለአፍሪካ ትልቅ ኩራት ነው:: የትውልድ ሀገሩ ጋናም አንድ ሳምንት ሐዘን አውጃለች:: ለኮፊ አናን የተሰነዘሩት የምስጋና ቃላቶች ልብ የሚነኩና የሚያስለቅሱ ናቸው:: ከዓመታት በፊት አሳትሜው የነበረው “የፒያሳ ልጅ” መጽሐፌን መታሰቢያነቱን ከአፍሪካ ለኔልሰን ማንዴላና ለኮፊ አናን ነበር ያደረግሁት:: ለሁለቱም ከፍ ያለ አክብሮት ያለኝ የማደንቃቸው መሪዎች ነበሩ:: እግዚአብሔር ነፍሱን ይማረው::

## ህወሓት ከመንግሥት . . .

ከገጽ 16 የዞረ

ነበር፤ እሱም መሬት ተደፍቶ ይጸልያል፤ ፈጣሪውን ያመሰግናል:: የተሳፈርንበት አውሮፕላን እንደ ጀቶች አይፈጥንም፤ እነሱ በሦስት ሰዓት ውስጥ እስራኤል ሲገቡ፣ እኛ ደግሞ አምስት ሰዓት ፈጀብን:: እኔ እዚያ ስደርስ የደርግ መንግሥት አልወደቀም፤ ብዙ ጊዜ ግን ወያኔ እንደ ከጂ ስሜን ያነሳል::

ቅዳሜ ነው ሀገር ለቅቄ እስራኤል የገባሁት፤ ወያኔ ጦሩን ይዞ ሙሉ ለሙሉ አዲስ አበባ የገባው ማክሰኞ ግንቦት 20 /1983 ዓ.ም ነው:: ስለዚህ እኔ ከሀገር ስወጣ ደርግ ገና ሥልጣኑን ስላልለቀቀ 'ከሀዲ' ሊለኝ የሚችለው የራሴ ፓርቲና መንግሥት ነው እንጂ፣ 'ወያኔ' የሚባለው የሥልጣን አካል አይደለም፤ ከቀናት በኋላ ነው ወንበዴዎቹ ሥልጣን የያዙት::

**ግዮን፡- በዚያ ወቅት እስራኤል ሀገር ሲደርሱ፣ የኢትዮጵያ መንግሥት ያስቀመጣቸው የፕሮቶኮል ሹማምንትና ዲፕሎማቶች የተቀበሉዎት መሆኑ፤ ይሄንን ዕውነታ የሚያጠናክር ይመስለኛል…**

**አምባሳደር ካሳ፡-** እሱ ትክክለኛው ማረጋገጫ ነው:: በፕሮቶኮል ደረጃ የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ነው የተቀበለኝ:: ኢየሩሳሌም ሒልተን ሆቴል ነው ያሳረፉኝ፤ በፊት ለሥራ ስሄድ ይቀበሉኝ በነበረው ሁኔታና ደረጃ ነው የተቀበሉኝ:: እኔ ስወጣ ወያኔ ሥልጣን ይዞ ቢሆን ኖሮ ይሄ ሁሉ የክብር አቀባበል አይደረግልኝም ነበር::

**ግዮን፡- በጊዜው ኮ/ል መንግሥቱ ኃ/ማርያም ሀገር ጥለው ባይሄዱና ከአሜሪካኖች ጋር የተጻጻፉት ደብዳቤና ስምምነት እንዳሉት ተፈርሞ ቢሆን ኖሮ፣ ነገሮች ሊለወጡ ይችሉ ነበር?**

**አምባሳደር ካሳ፡-** ኮ/ል መንግሥቱ ኃ/ማርያም ባይወጡ ኖሮ፣ ሻዕቢያና ወያኔ ወደ ፈለጉበት ግብ የሚደርሱበት ጊዜ፤ ከሆነው በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ይገፋ ወይም ይርቅ እንደነበር ግልጽ ነው:: በርግጥ እነዚህ ሁለት ቡድኖች በእኛ የደህንነት ሰዎች ስለ ጦር ዕቅዳችን በቂ መረጃ ያገኙ ሲሆን፤ የሱዳን መንግሥትም በከፍተኛ ሁኔታ ተባብሯቸው እንደነበር ይታወቃል:: አዲስ አበባን ለመያዝ ሙከራ ማድረጋቸው ባይቀርም፣ በቀላሉ ሊገቡ ግን አይችሉም ነበር::

በአሜሪካኖችም ሆነ በውጭው ዓለም በነበሩት ሌሎች ሀገራት የነበረው ሥጋት 'አዲስ አበባ እገባለሁ፤ አትገቡም' በሚለው ጦርነት፤ ጣልያኖች አዲስ አበባ በገቡ ጊዜ በእሳት እንዳጋየናቸው ያንን የመሰለ ዕልቂት አዲስ አበባ ውስጥ ሊኖር ይችላል የሚል ነበር፤ ግን በመንግሥት በኩልም ቢሆን፣ 'እዚሁ ሆኖ ከመዋጋት ይልቅ፤ ወደ ደቡብ ሄዶ እዚያ ተጠናክሮ ከደቡብ ወደ ሰሜን ማጥቃትና ወያኔን መደምሰስ ይቻላል' የሚል ግምት ነበራቸው - ፕሬዝዳንት መንግሥቱ ኃ/ማርያም:: ያ ግምት መነሻ ሆኖ የመንግሥት መቀመጫ ከአዲስ አበባ ወደ ሀዋሳ ሊዛወር የሚችልበት ጥናትም ተጠንቶ ነበር::

ሊቀ መንበር መንግሥቱ ከሀገር የወጡ ቀን፣ 'አስቸኳይ ስብሰባ አለ' ተብሎ ስንጠራ ወደ ኢትዮጵያ የሚመጡትን እስራኤሎች መቀበል ስለነበረብኝ፣ 'እሳቸው የሚያውቁት አስቸኳይ ሥራ አለብኝ' ብዬ ለመቅረት ስሞክር ኮ/ል መንግሥቱ ገመቹ፣ 'አይቻልም ተብለሃል' ሲለኝ ነው ወደ ስብሰባው የሄድሁት:: በሰዓቱ አዕምሮዬ ውስጥ የነበረው፣ የወያኔ ግፊት ስላየለ፣ 'ወደ ደቡብ እንሂድ' የሚለውን ትዕዛዝ ለመስጠት ነው ፕሬዝዳንቱ የሚሰበስቡን ብዬ ነው የሄድሁት:: ይሄንን ከአሁን አሁን ገብተው ይነግሩናል ስንል ጄኔራል ተስፋዬ ገብረ ኪዳን ገብቶ፣ 'እሳቸው ሀገር ለቀው ሄደዋል፤ እኔ ተክቼ እሠራለሁ' አለን:: ያ ቢሆን ኖሮ ጊዜ መግዛት ይቻል ነበር::

በወቅቱ አሜሪካኖቹን ሙሉ ለሙሉ የጠየቅናቸው ነገሮች ላይሚሉ ይችላሉ፤ ግን ፕሬዝዳንት ቡሽ ቃል በገቡልን መሠረት ኤርትራ እንዳትገነጠል፤ 'ተገነጠልሁ' ብትልም ዕውቅና እንዳታገኝ ለማድረግ የሚቻልበት ሁኔታ ነበር:: ለምሳሌ፡- ሶማሌ ላንዶች፣ 'እኛ የእንግሊዝ ቅኝ ግዢ ስለነበርን ተገንጥለናል፤ ራሳችንን ችለናል' በሚል፤ ደርግ ከመውደቁ በፊት ነው ነፃነታቸውን ያወጁት:: ከኤርትራ በፊት ግን የዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ አልፈቀደም፤ የአፍሪካ ሕብረትም መስማማት አቅቶታል:: ይኸው ሶማሌ ላንድ ከሞላ ጎደል ነፃ መንግሥት ሆኖ ነው የሚንቀሳቀሰው፤ ግን ዕውቅና አልተሰጠውም:: ስለዚህ የኤርትራም ጉዳይ ከዚያ ውጪ ላይሆን የሚችልበት ዕድል ነበር፤ ተባብረን ብንሠራ አንሸነፍም ነበር:: ዋናው ፍርክስክሳችን የወጣው ከውስጣችን ነው::

**ግዮን፡- ኢትዮጵያውያን አይሁዶች ከሀገር ሲወጡ ቀጥተኛ ተጠቃሚ እንዲሆን በተደረገው አየር መንገድ አማካይነት ብዙ ሚሊዮን ዶላር ለኢትዮጵያ መንግሥት ገቢ እንዲሆን ቢደረግም፤ "ህወሓት ገንዘቡን አውጥቶ ለኤፈርት ማቋቋሚያ እንዲውል አድርጓል" ይባላል፤ ይሄን ቢያብራሩልን?**

**አምባሳደር ካሳ፡-** ቀደም ሲል እንደገለፅሁት፣ ኢትዮጵያውያን አይሁዶችን ለመውሰድ እስራኤላውያን ጥያቄ ሲያቀርቡ፤ ፕሬዝዳንት መንግሥቱ ባስቀመጡት ቅድመ ሁኔታ አማካይነት የማጓጓዝ ሥራውን የኢትዮጵያ አየር መንገድ በመሥራት የኢኮኖሚ ተጠቃሚ እንዲሆን የተደረገ ነገር ነበር:: በዚያ መሠረት፣ የጊዜው የኢትዮጵያ አየር መንገድ ሥራ አስኪያጅ ካፒቴን ዘለቀን ጠርቼ ከአሜሪካኖቹና ከእስራኤሎቹ ጋር ስንጋገር ገንዘቡ ከፍ እንዲል አንዳንድ ሰበቦችን ተጠቀምን:: ቀደም ሲል በነበረው የጉዞ አሠራር ከአዲስ አበባ ሮም፣ ከሮም ቴልአቪብ እንደሚሄዱ አድርገን እናስብ በሚለው ተስማማን፤ ሁለተኛ እነዚህ ሰዎች እስራኤል ሄደው ሀገሩን ባይወዱትና 'ሀገራችን እንምጣ' ቢሉ፤ አስቸጋሪ ስለሚሆን ወይ ሶሻል ወርከሮች መድበን፣ ፍላጎታቸውን እየተረዳን፣ ፓስፖርት እየተሰጣቸው እንደማናቸውም ተጓዥ እንዲጓዙ እናድርግ፤ አለበለዚያ በጅምላ እዚያው ሄደው ሀሳባቸውን ሊለውጡ ስለሚችሉ፣ 'የመመለሻ ትኬትም ይገዛላቸው' ብለን ሀሳብ አቅርበን ያንንም ተቀበሉት::

ስለዚህ በሰው የደርሶ መልስ ትኬት ታሳቢ በአንድ ሰው አንድ ሺህ ዘጠኝ መቶ አካባቢ መጣ፤ ተጓዦቹ ከአስራ ስምንት ሺህ እስከ ሃያ ሺህ ይሆናሉ በሚል ግምት ሠላሳ አራት ሚሊየን ዶላር ገደማ ድምር ሂሳብ ደረሰ:: ለኢትዮጵያ አየር መንገድ ግራውንድ፣ 'አንዳንድ ሥራዎች አሉ' ስለተባለ፤ 'ብሩን ትንሽ ከፍ እናድርገው' በሚል ሠላሳ አምስት ሚሊዮን ዶላር ላይ ከስምምነት ደረሰ:: ይሄ ቀደም ሲል ነው ስምምነት ላይ የተደረሰበት፤ ነገሩን ትንሽ ያጓተተው አስቀድሜ የገለጽሁት የደብዳቤ ልውውጥ ጉዳይ ነው::

ይሄ ሠላሳ አምስት ሚሊዮን ዶላር የራሱ ውጣ ውረድ ቢኖረውም፤ ዓርብ ዕለት ኒውዮርክ ሲቲ ባንክ ያለው የኢትዮጵያ መንግሥት አካውንት ገቢ መሆኑ ተረጋግጧል:: የብሔራዊ ባንክ የወቅቱ አስተዳዳሪ አቶ ለገሰ ሞታ እና የገንዘብ ሚኒስትሩ አቶ በቀለ ታምራት ገንዘቡ ገቢ መሆኑን አረጋግጠዋል:: ያ ገንዘብ ገቢ በሆነበት ሰዓት፣ ወያኔ እድለኛ ነው፣ ከሁለት ቀን በኋላ አዲስ አበባ ሲገባ፤ ሰላሳ አምስት ሚሊዮን ዶላር በካሽ ተቀምጦለት ነው:: እንዲያውም አስቀምጬለት ነው የሄድሁት ማለቱ ይቀላል::

ገንዘቡ ኒውዮርክ ሲቲ ባንክ በኢትዮጵያ መንግሥት ስም መቀመጡን ወንበዴዎቹ ተረድተዋል፤ መጀመሪያ ላይ የቀድሞው መንግሥት ያንን ገንዘብ ይዞት እንደሄደ አድርገው ለማስወራት ምክረዋል:: ትልቅ ወሬ ሆኖ ነበር:: ፕሬዝዳንቱ እንደወሰዱ፣ እኔም ያንን ያህል ገንዘብ ይዤ እንደሄድሁ ተደርጎ ተወርቷል:: ገንዘቡን መጀመሪያ የአሜሪካ አይሁዶች ናቸው ለእስራኤሎች የሰጡት:: እነዚያ አይሁዶች ኒውዮርክ ታይምስ ላይ፤ ያ ገንዘብ ባንክ እንደሚገኝና የቀድሞ መንግሥት ማናቸውም ባለሥልጣናት እጅ እንዳልገባ መግለጫ ሰጡ:: ካፒቴን ዘለቀ፣ ገንዘቡ የኢትዮጵያ አየር መንገድ እንደሆነ ስለሚያውቅና እኔም፣ 'ተከታትለህ ጉዳዩን አስጨርስ' የሚል መልዕክት እልክ ስለነበረ፤ በወቅቱ ጠ/ሚኒስትር የነበረው አቶ ታምራት ላይኔ ቢሮ በመመላለስ ቃል እንደተገባለት ነግሮኝ ነበር::

በኋላ ታምራት ላይኔ፣ 'ሙሉ ለሙሉ ገንዘቡ ለኢትዮጵያ አየር መንገድ አይሰጣችሁም፤ ምክንያቱም በኦፕሬሽኑ ላይ የእስራኤል አውሮፕላኖችም አግዘዋችኋል፣ በከፊል ነው የሚሰጣችሁ' የሚል ሐሳብ አመጣ:: ከተወሰነ ጊዜ ቆይታ በኋላ አግኝቼ፣ ካፒቴን ዘለቀን ስጠይቀው፣ 'ይሄን ነገር እንዳታነሣ ተብያለሁ፤ ሰባራ ሳንቲምም አላገኘንም' አለ:: በእኔ በኩል ብዙ ጊዜ ጉዳዩን ለመከታተል ሞክሬያለሁ:: በወቅቱ የማስታወቂያ ሚኒስትር የነበረው አቶ ዲማ ነገዎን ኢየሩሳሌም ለጉብኝት በሄዱበት አጋጣሚ፤ የእስራኤል ጋዜጠኞች ሲያፋጥጡት፣ 'ገንዘቡ ያለው መንግሥት እጅ ነው' ብሎ ነበር:: እዚህም የነበረው የእስራኤል አምባሳደር፣ 'ለአዲሱ መንግሥት ስጦታ እንደተሰጠ ይቆጠር፤ ሌላ ማንም አልወሰደውም' ብሎ ነበር::

የዚያ ገንዘብ ትክክለኛ ባለቤት የኢትዮጵያ አየር መንገድ ነው፤ እኔም እንድደራደር የተነገረኝ ለዚሁ ተቋም ነው:: አብረውኝ የሠሩትም የኢትዮጵያ አየር መንገድ ሰዎች ናቸው:: ግን ገንዘቡን ህወሓት እንደወሰደውና በኋላ ለኤፈርት ለትግራይ ልማት ማኅበር ማቋቋሚያ እንደዋለ በእስራኤሎች በኩል ምላሽ አግኝተናል:: ከዚህ ሠላሳ አምስት ሚሊየን ዶላር በተጨማሪ ከኩዌት የተገኘ ሃያ ሚሊዮን ዶላር በኢትዮጵያ መንግሥት አካውንት ውስጥ ተቀምጦ ነበር፤ እነኚህና ሌሎች ከውጭ የተገኙ የዕርዳታ አካውንቶች በሙሉ ተለቃቅመው ለዚህ ተግባር ውለው ሊሆን ይችላል ብዬ እጠረጥራለሁ:: ግን በኢትዮጵያ አይሁዶች አማካይነት ለአየር መንገዳችን የተከፈለውን ሠላሳ አምስት ሚሊዮን ዶላር ህወሓት ከኢትዮጵያ መንግሥት አካውንት አውጥቶ ለኤፈርት ማቋቋሚያ ደጉሟል::

**ግዮን፡- ይሄ ሠላሳ አምስት ሚሊዮን ዶላር እንዳይወጣ የኢትዮጵያ መንግሥት አስቀድሞ ማድረግ የነበረበት ጥንቃቄ አልነበረም፤ ስህተቱስ የማን ነው?**

*ውድ አንባብያን ለእነዚህና ለሌሎች ወቅታዊና ሀገራዊ ጉዳዮች፤ አምባሳደር ካሳ ከበደ የሰጡንን ምላሽ በሚቀጥለው ሳምንት ዕትማችን ይዘን የምንቀርብ መሆናችንን ከወዲሁ እንገልፃለን::*

# የሴቶች ቀን ከመፈጠሩ ከዘመናት በፊት

በዓለም ላይ ያሉ መንግሥታት ስለ ሴት ልጅ ያላቸው አመለካከት ባልተስተካከለበት ዘመን እምዬ ምኒልክ ግን ሴቶች ከመደበቅና ከማፈር ተላቀው ከቤት ውስጥ ሓላፊነት በተጨማሪ በአደባባይ ያሉ ተግባራትን መከወን እንደሚችሉ ለሚስታቸው ለእቴጌ ጣይቱ በመንግሥት ሥራ ላይ እንዲሳተፉ ዕድል በመስጠት አሳይተዋል:: ከዚህም በተጨማሪ ሴት ልጅ በፈቃድዋ የወደደችውን መርጣ እንድታገባ ዕድል እንዲሰጣት አጼ ምኒልክ በዘመናቸው አዘዋል:: እንግዲህ አፄ ምኒልክ ይህን ሁሉ ያደረጉት የሴቶች ቀን ከመፈጠሩ ከዘመናት በፊት ነው:: እነሆ አሁን በሀገራችን የሴቶች ቀን መከበር ከተጀመረ 42 ዓመታትን አስቆጥሯል፤ ሆኖም ግን ባለፈውም ሆነ አሁን ባለው መንግሥት ሴቶች ለፖለቲካ ማሟያ ግብዓት ከመሆን ውጪ፤ "በኢኮኖሚያዊ፣ በፖለቲካዊና በማሕበራዊ ጉዳዮች ተጠቃሚ ሆነዋል" ለማለት አያስደፍርም:: ዛሬም ላይ የሀገራችን ሴቶች ማገዶ ፍለጋ በጫካ ውስጥ ይንቀሳቀሳሉ፤ ውሃ በጀርባቸው ተሸክመው ረጅም መንገድ ይጓዛሉ፤ በሕክምና እጦት በወሊድ ምክንያት ይሞታሉ፤ በኩሽና ውስጥ ከጭስ ጋር ይታገላሉ፤ ከመቼውም ጊዜ በላይ ስጥቃት ይዳረጋሉ:: በየዓመቱ ለማርች 8 ተብሎ የሚደረገው ድግስና ክብር ከቀኑ ይልቅ ለሴቶች ቢደረግ ስንት ለውጥ በመጣ ነበር::

# "ያ'ለምጣም" ምኒልክ

በአዝማሪ መመስገን የሰለቻቸው አፄ ምኒልክ አንዱን አዝማሪ፣ "እስቲ አሁን ደግሞ ስደበኝ" አሉት:: አዝማሪውም፦

"ይገድሉኝም እንደሁ ይኸው ቆምሁልዎ፣

ያ'ለምጣም ምኒልክ ብዬ ሰደብኩዎ" ብሎ ገጠመ::

"'ለምጣም" በሚለው ቃል ውስጥ "የዓለም ጣዕም" የሚል ሙገሳ እንዳለው የገባቸው የዋሁ ንጉሥም ልባቸው ተነክቶ አለቀሱ::

# እንቆቅልሽ

- እንሶስላ ሞቃ ከዱር ተደብቃ ........................ እንጆሪ
- ረጅም ሴት በጎኗ ልጅ ይዛ ............................ በቆሎ
- ከአባቴ ጓሮ ፍልጥ ተደርድሮ ...................... ጥርስ
- ዛሬ ተጠቅታ ዛሬ ትወልዳለች፣ዛሬ ወልዳ ዛሬ ትነጥፋለች፤ ...................................... ገበያ
- ሁለት ዳቦ ትክክል፣
- አንድ ቀዝቃዛ አንድ ትኩስ፤ ........... ጨረቃና ፀሐይ

# ቅንጭብጭብ እውነታዎች

- የሻይ ቅመም ከ160 በላይ ንጥረ ነገሮችን የያዘ ቅመም ነው።
- አንድ ቃል ለመናገር 74 ጡንቻዎች ይንቀሳቀሳሉ።
- አርባ ሠባት ዓይነት የራስ ምታት በሽታዎች አሉ።
- ከእንስሳት ሁሉ ከፍተኛ ዕድሜ እንዲኖሩ ፀጋ የተሰጣቸው፤ ኤሊ 150፤ ፓሮት 60 እና አዞ 53 ዓመት ናቸው።
- ለመጀመሪያ ጊዜ ኢትዮጵያ ውስጥ ጎማዋ የረገጠው ተሽከርካሪ ታርጋ ቁጥሯ D3130 ነበር።

# በአማርኛ ፊደላት የደመቁት የሩሲያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስተር

የአሌክሳንደር ፑሽኪን የደም ትስስራችን ዳግም በሩሲያው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሰርጌይ ላቭሮቭ ከፍ ብሎ እንዲታይ ሆኗል። የራሳቸው የመጻፊያ ፊደል ካላቸው ጥቂት ሀገራት ውስጥ ኢትዮጵያ አንዷ ናት። ይህ የፊደል ገበታችን በሀገር ውስጥ ትምህርት ቤቶች እንኳን እየተናቀ የፈረንጁ የእንግሊዝኛ አልፋ ቤት መላ ሕዝቡን እንዲወርሰው ሲደረግ፤ በዓይናችን እያየንና እያዘንን ባለበት ወቅት፣ እንዲህ ወደራሳችን መለስ እንድንል የሚያደርግ መልዕክት ጭምር ሊያስተላልፉ፤ ወደ ሀገራችን የመጡት የሩሲያ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር፣ ለሀገራችን ምን ያህል ክብር እንዳላቸው አሳይተውናል:: የሩሲያና የኢትዮጵያ የዲፕሎማሲ ግንኙነት 120 ዓመታት ያስቆጠረ መሆኑን ተከትሎ፣ ወደ ሀገራችን የመጡት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሰርጌይ ላቭሮቭ፤ በየመድረኩ ላይ ያደረጉት ከረባት በአማርኛ ሙሉ ሆሄያት የደመቀ ነበር::

# በ 37 ዓመቷ 44 ልጆችን የወለደችው እናት



ማርያም ናባታንዚ የተባለች ኡጋንዳዊት በ37 ዓመቷ 44 ልጆችን ወልዳ ስሟን በክብር መዝገብ አስፍራለች። ይህች ሴት የ40 ዓመት ጎልማሳ የሆነውንና በአሁኑ ሰዓት ጥሏት የጠፋውን ባሏን ያገባችው ገና ዕድሜዋ 12 ዓመት እያለ ሲሆን፤ ከመጨረሻው ልጇ በስተቀር ሁሉንም ልጆቿን የወለደችው በቤቷ ውስጥ ነበር። በዚህም 6 ጊዜ መንታ፣ 5 ጊዜ ሦስት፣ ሦስት፤ 4 ጊዜ ደግሞ አራት፣ አራት እንደዚሁም በመጨረሻ 1 ልጅ በሆስፒታል በድምሩ 38 ልጆችን ወልዳለች።

ይህች እናት እነዚህን ልጆች ሁሉ በብቸኝነት የምታስተዳድርና የምትመራ ሲሆን፤ እነዚህን ከአብራኳ የተወለዱ ብዙ ልጆቿን ለመቀለብና ለመመገብ እጅግ ፈተና ቢሆንባትም እግዚአብሔር ያስችላልና በአካባቢው ዋነኛ ምግብ የሆኑትን የበቆሎና የእንጨት "ቦዬ" ገንፎ በማዘጋጀት ትቀልባለች።

ከእነዚህ በሕይወት ካሉት 38ቶቹ መካከል ዐሥሩ ሴቶች ሲሆኑ፤ 28 ያህሉ ወንዶች ናቸው፤ ከልጆቹ መካከል ትልቁ 23 ዕድሜ ያለው ሲሆን፤ ትንሹ ደግሞ 4 ወራት ዕድሜ አለው።

# አባባሎች

- አምራለሁ ብላ ቸኩላ፤ ዓይኗን አጠፋች ተኩላ::
- ስለናቁ፣ መላ አያውቁ::
- ስለጨሰ አይነድም፤ ስለዳመነ አይዘንብም::
- ግልጹ ሰው፣ በራሱ ሕሊና ውስጥ ያልተደበቀ ነው::

# ስለ ፍትሕ

ፍርድ ቤቱ ኦና ኡኡ ማያ ብቻ፤
እውነት ተደምስሳ የሐሰት መከማቻ::
ዴሞክራሲ ብለው ዴሞክራሲ አጠፉ፤
ለምን? እንዴት? ባዩ ዘብጥያ ተገፉ::
ሥቃዩም አየለ ሞልቶ ፈሷል በደል፤
ዳኛ በሌለበት ለማን? አቤት እንበል::
ደኅንነት ወንጀሎኝ ዳኛውም ፈረደ፤
እግዜር ምንተስኖት ፈራጁም ወረደ::

# “ኪነ ጥበብ ያልታዩ የሕይወት ገጽታዎችን የምናይበት መነጽር ነው”

ደራሲ ሰአዳ መሐመድ

*ሐምሌ 30 ቀን፣ 2010 በአዲስ አበባ ኤግዚቢሽን ማዕከል፣ ለአራተኛ ጊዜ በተካሄደው ‘**ንባብ ለሕይወት**’ የ2010 የወርቅ ብዕር ተሸላሚ የሆነችው፣ የሥራ ባልደረቦችዋና በቅርብ የሚያውቋት “ስለ ራሷ ማውራት አትወድም፤ ሥራዎችዋ ግን ማንነቷን ይገልፃሉ” ሲሉ ምስክርነታቸውን የሰጡላት ጋዜጠኛና ደራሲ ሰዓዳ መሐመድን ስለ ራስዋና ስለ ሥራዎችዋ ከግዮን ባልደረባ ጋራ ቃለ ምልልስ አድርጋለች፤ ሙሉው ቃለ ምልልስ እንዲህ ተቀናብሯል፡፡*

**ግዮን፡- ኪነ ጥበብ ለአንቺ ምንድን ነው?**

**ሰአዳ፡-** ኪነ ጥበብ የሕይወት ገጽታዎችን የምናይበት፣ በፈጠራ ሥራ ይህች የምንኖርባት ዓለም ልትመስል የማንፈልገውን ገጽታዋን የራሱን ምኞት ጨምሮ የሚያሳይበት መነጽር ነው፡፡ በድርሰትም፣ በድራማም፣ በግጥምም ያሉትን ችግሮች ማመላከት ብቻ ሳይሆን፣ መፍትሔ ሐሳብም በነፃነት የምትሰነዝርበት፤ ደስታን፣ ሐዘንን፣ ንዴትን፣ ለቅሶን፣ ምኞትንና ተስፋን የምትገልጽበት መንገድ ነው ብዬ አምናለሁ፡፡

**ግዮን፡- በቅርቡ ለአራተኛ ጊዜ የተዘጋጀው የ“ንባብ ለሕይወት” ዝግጅት የ2010 ዓ.ም የወርቅ ብዕር ተሸላሚ በመሆንሽ ምን ተሰማሽ?**

**ሰአዳ፡-** ሽልማቱ የሠራሁዋቸው ሥራዎቼ በተደራሲው ዘንድ ዋጋ እንዳገኙ፣ ሰው እንደሚያውቀልኝ ያሳየኝና በቀጣይም የበለጠ ለመሥራት ተጨማሪ ኃይልና ጉልበት ነው የሆነኝ፡፡ በቀጣይ ለመሥራት ያቀድኳቸው ሥራዎቼን የበለጠ በትጋት እንድሠራ እንደመስፈንጠሪያ ምርኩዝ አድርጌ ነው የወሰድሁት፤ እጅግ በጣም ደስ ብሎኛል፡፡

**ግዮን፡- በቅርቡ በቱርክ የኩላሊት ንቅለ ተከላ ሕክምና አድርገሽ ነው የተመለስሽው፤ አሁን እንዴት ነሽ?**

**ሰአዳ፡-** በዚህ አጋጣሚ የገጠመኝ የጤና እክል በመገናኛ ብዙኃን ይፋ መሆኑን ተከትሎ፤ ከመላው ኢትዮጵያ፣ ከኢትዮጵያ ውጭም የሚያውቁኝ ሥራዎቼን ያደመጡና የተመለከቱ አድናቂዎቼ፣ የሙያ አጋሮቼ፣ ጓደኞቼ ባደረጉት ከፍተኛ ርብርብና እርዳታ የኩላሊት ንቅለ ተከላ አድርጌ፤ አሁን ቀጣይ የሕክምና ክትትል በማድረግ ላይ እገኛለሁ፡፡ ለዚህ እንድበቃ በገንዘብ፣ በሐሳብ የረዱኝን፤ ኩላሊታቸውን ለመለገስ ፈቃደኝነታቸውን ያሳዩ በርካታ ወገኖቼን፤ የሕትመት፣ የኤሌክትሮኒክስና የማኅበራዊ ድረ ገጽ አዘጋጆችን፣ ጋዜጠኞችን እንዲሁም ሐኪሞቼን ላመሰግን እወዳለሁ፡፡ አሁን በጥሩ ሁኔታ ላይ እገኛለሁ፡፡

**ግዮን፡- በኪነ ጥበብ አድናቂዎችሽ ዘንድ በምን ሥራዎችሽ ነው የምትታወቂው?**

**ሰዓዳ፡-** የመጀመሪያዬ ሥራዬ በ1992 በሜጋ አሳታሚ ድርጅት የታተመው፣ በአረብ ሀገራት በሚሠሩ ኢትዮጵያውያን እህቶቻችን የስደት እና



ደራሲ ሰአዳ መሐመድ

የእንግልት ሕይወት ላይ የሚያጠነጥን ‘እሾሃማ ወርቆች’ የተሰኘ ልብ ወለድ መጽሐፍ ነው፤ ይህ መጽሐፌ በኢትዮጵያ ሬድዮ ‘ከመጻሕፍት ዓለም’ ፕሮግራም ላይ ተተርኮልኛል፡

በመቀጠልም፣ በፋና ዴሞክራሲ አሳታሚነት በታተሙ የ‘እፍታ’ የወጣትና አንጋፋ ደራስያን ሥራዎች ስብስብ ውስጥ፤ አጫጭር ልብ ወለዶቼና ግጥሞቼ ታትመው ለንባብ በቅተውልኛል፡፡ በቅርቡ ደግሞ ‘ደባሎቼ’ የተሰኘ የአጫጭር ልብ ወለዶች መድብል አሳትሜያለሁ፡፡ ከዚሁ በተጨማሪም በፖፕሌሽን ሚዲያ ሴንተር አሳታሚነት በታተሙ የወጣት አንጋፋ ደራስያን ሥራዎች በተካተቱባቸው መጽሐፎች ላይም ሥራዎቼ ታትመውልኛል፡፡

**ግዮን፡- በተጨማሪስ?**

**ሰአዳ፡-** በኢትዮጵያ ሬድዮ በ‘ቅዳሜ ከሰዓት’ እና በእሁድ ጠዋት ፕሮግራም ላይ፣ ‘ያበቃ ሕልም’፣ ‘የባቡ እግሮች’፣ ‘ሦስቱ መስኮቶች’፣ ‘ጥልፍልፎሽ’፣ ‘ያልተደፈነ ጉድጓድ’ የተሰኙ፤ እንዲሁም በፋና ሬድዮ ደግሞ ‘የወንዝ ድንጋይ’ የተሰኘ ተከታታይ የሬድዮ ድራማዎች ጽፌ ተላልፎልኛል፡፡

በሬድዮ ድራማ ጸሐፊነት በቆየሁባቸው ላለፉት ዘጠኝ ዓመታት፣ በፖፕሌሽን ሚዲያ ሴንተር ከሌሎች ጸሐፍት ጋራ በመሆን፣ በባለ 226 ክፍል ‘ስብራት’ በባለ 130 ክፍል ‘የረገፉ ፈትሎች’ በባለ 190 ክፍል ‘የብርሃን አጽናፋት’ በባለ 180 ክፍል ‘ምዕራፍ’ የተሰኙ የሬድዮ ድራማዎች ላይ በጸሐፊነት ተሳትፌያለሁ፡፡ በነዚህ የሬድዮ ድራማዎች፣ ፖፕሌሽን ሚዲያ ሴንተር፣ በኢንተርናሽናል ግሎባል ሚዲያ አዋርድ አሸናፊ ሆኖባቸዋል፡፡

ላለፉት አምስት ዓመታት በ‘የኛ’ የሬድዮ ድራማ፣ የታሪክና የገፀ ባሕርይ ግንባታ፣ እንዲሁም የድርሰት ጽሑፍ ሥራ ላይ በደራሲነት ተሳትፌያለሁ፡፡

**ግዮን፡- አንዳንዶች፣ “አብዛኛውን የኪነ ጥበብ ዘርፍ የተቆጣጠሩት ወንዶች ናቸው” ይላሉ፤ እናም የሴቶች ተሳትፎ እንዲያድግ ምን መደረግ አለበት ትያለሽ?**

**ሰአዳ፡-** ተግዳሮቶች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ ሴቶች በዘርፉ ያላቸው ሚና እንዲያድግ፣ መድረኩ ክፍት ሊሆንላቸው ይገባል፤ የተሻለ ችሎታ ያላቸው በርካታ ሴቶች መድረክ ለማግኘት ሲመጡ፣ ዕድሉ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ በፆታ እኩልነት ማመን አንዱ የሥልጣኔ ምልክት ነው፡፡ እኩልነትን ለማረጋጥ መጣር፣ ብቃትን፣ ችሎታን ማሳየት ያስፈልጋል፡፡ ይህን በማድረግ ነው ክፍተቱን መሙላት ይቻላል ብዬ ነው የማምነው፡፡

**ግዮን፡- የሠራሻቸው ሥራዎች በአብዛኛው በማኅበረሰቡ ውስጥ ያሉ ማኅበራዊ ችግሮች ላይ ያነጣጠሩ ናቸው፤ የሀገራችን ኪነ ጥበብ የማኅበረሰቡን የዕለት ተዕለት ኑሮ እና ማኅበራዊ መስተጋብር ለማመላከት የሚያስችል ቁመና ላይ ነው?**

**ሰአዳ፡-** አይደለም፡፡ ገና ምኑ ተነካና! ባለፉት ዓመታት በተለያዩ የሀገራችን ክፍሎች እየተዘዋወርን የማኅበረሰቡን ችግሮችና ጎጂ ባህሎች በተመለከተ ብዙ እንቅስቃሴዎች ተደርገዋል፡፡ በነዚህ እንቅስቃሴዎች የተረዳሁት ነገር ቢኖር፣ በማኅበረሰባችን ውስጥ እጅግ አስገራሚ የሆኑ፤ በዘመን ተሻጋሪ ቱባ ባህሎች የታጨቀ፣ በአብሮነት ላይ የተመሠረተ፤ እንደ ደራሲና ጸሐፊ ያልተነኩ፣ ያልታዩ፤ ግን ሊያስተምሩና በየጊዜው ለሚያጋጥሙን ችግሮች እንደመፍትሔ ሊወሰዱ የሚችሉ ትርክቶችና ተሞክሮዎች ያሉ መሆኑን ለመመልከት ችያለሁ፡፡ እናም ገና ብዙ ሊያሠራን የሚችል እምቅ ታሪክና እሴት ባለቤቶች ነንና ብዙ መሥራት ይጠበቅብናል፡፡

**ግዮን፡- ከደራሲነትሽ በተጨማሪ ጋዜጠኛ ነሽ፤ እንዴት ወደ ሙያው ገባሽ?**

**ሰአዳ፡-** ጋዜጠኝነትን የጀመርሁት በተለያዩ የግል ጋዜጦችና መጽሔቶች ላይ ጽሑፍ በማቅረብ ነው፡፡ በጋዜጠኝነት ሙያ፣ በምኅዳር የጋዜጠኝነት ማሰልጠኛ ተቋም የጋዜጠኝነት ትምህርት ተከታትያለሁ፡፡ ከዚያም በ‘እፎይታ’ ጋዜጣና መጽሔት በፍሪላንሰርነት፤ በመቀጠልም በዩኒቲ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ አሳታሚነት ያዘጋጅ በነበረው በ‘ዕለታዊ አዲስ’ ጋዜጣ በሪፖርተርነት፤ ከዚያም በዩሪካ ፕሬስ አሳታሚነት ይታተም በነበረው ‘ሩሕ’ መጽሔትና ጋዜጣ በምክትል አዘጋጅነት፤ እንዲሁም በ‘ብሩህ ተስፋ’ ሬድዮ በአዘጋጅነት ሠርቼያለሁ፡፡

**ግዮን፡- ከሕትመትና ከሬድዮ ድራማዎች ደራሲነት በተጨማሪ ምን ምን ሥራዎችን ሠርተሻል?**

**ሰአዳ፡-** በቴሌቪዥን ድራማ ደራሲነትም ሠርቼያለሁ፤ በኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ሲተላለፍ በነበረው ‘የቤት ሥራ’ ተከታታይ የቴሌቪዥን ድራማ 32 ክፍሎች በጥምር ደራሲነት ተሳትፌያለሁ፤ በ‘ዘመን’ የቴሌቪዥን ድራማ የመጀመሪያ ምዕራፍ በታየ የስደት ታሪክ ላይም በጸሐፊነት ተሳትፌያለሁ፡፡

**ግዮን፡- ወደፊትስ ምን እንጠብቅ?**

**ሰአዳ፡-** ወደፊት የተለያዩ አዳዲስ ሥራዎችን ይገፔ ለመቅረብ የሚያስችሉ እንቅስቃሴዎችን በማድረግ ላይ ነኝ፡፡ የግዮን መጽሔት ዝግጅት ክፍል ይህንን ዕድል ስለሰጠኝ በዚህ አጋጣሚ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡ ‘ይህንን ሠርቼ ለአድናቂዎቼ አቀርባለሁ’ ከማለት ይልቅ፤ ሥራዎቼ ለተደራስያን ሲደርሱ ማየትን እመርጣለሁ፤ የዚያ ሰው ይበለን፡፡

**ግዮን፡- እናመሰግናለን፡፡**



"መለያችን ኢትዮጵያዊነታችን"

ግዮን መፅሔት
በየሳምንቱ
ገበያ ላይ ትውላለች!

የማስታወቂያ ባለሙያ
በተለያየ የሕትመት ውጤት
ላይ ለረጅም ጊዜ የሰራ
/የሰራች/ የማስታወቂያ
ባለሙያ እንፈልጋለን



በአጭር ጊዜ ገበያ ውስጥ ለመግባት የቻለችው ግዮን የእርስዎ መፅሔት፤
በልዩ አቀራረብ፣ በአዳዲስ አምዶችና በሳል ፀሃፊያን በመታገዝ በየሳምንቱ
ቅዳሜ ከእጅዎ ትደርሳለች።

ቢጨመር ፣ ቢሻሻል የሚሉትን ከወዲሁ ይጠቁሙን!

+251 911 227661
+251 912 165606
+251 118 122333

Facebook
Gihon-meg Fekadu
ኢ-ሜይል:
enqu2013@gmail.com

# የአንዱዓለም አራጌ
## አዲስ መጽሐፍ ገበያ ላይ ውሏል!

በኢትዮጵያ ፖለቲካ ከ20 ዓመት በላይ ያሳለፈውና በፖለቲካ
አመለካከቱ ከ8 ዓመት በላይ በእስር የቀቆየው አቶ
አንዱዓለም አራጌ በእስር ቤት በነበረበትና ከእስር ከወጣ በኋላ
ያዘጋጀው መጽሐፍ በቅርቡ በገበያ ላይ ውሏል።
ለ2ኛ ጊዜ ታትሞ በገበያ ላይ በዋለው መጽሐፍ
ምስክርነታቸውን የሰጡት፤ ፖለቲከኛ ዶ/ር ያዕቆብ
ኃ/ማርያም፣ ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ እና ጋዜጠኛ ተመስገን
ደሳለኝ እንዲሁም የመጽሐፉ ደራሲ አንዱዓለም አራጌ
ያቀረቧቸው አስተያየቶች ተካትተውበታል።




ለበለጠ መረጃ
0932 17 73 07

በሁሉም መጽሐፍ መደብር ያገኙታል!
በአ.አ እና በክፍለ ሀገር በመጽሐፍ አዟሪዎች ያገኙታል